# ሀ

**ሀ** በአማርኛ የፊደል ገበታ መጀመሪያ ላይ የሚገኝ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)።

**ሁ** የ "ሀ" ፊደል ካእብ ዘር።

**-ሁ(-ኩ)** በግስ መድረሻ በኩል እየተጨመረ "እኔ"የሚለውን የግሱን ባለቤት የሚወክል ምእላድ። *ሄድሁ (ሄድኩ)።*

**ሁለመና** ስ ሁለንተና፤ ጠቅላላ አካል።

**ሁለት** ስ 1. በአንድና በሶስት መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ፤ በአሃዝ ሲፃፍ"፪"፥ "2" ነው። ቅ 2. በአንድና በሶስት መካከል ያለ ብዛትን የሚያሳይ። *ሁለት መፃህፍት፡*

**ሁለት ሆነ** ተገመሰ፥ ተከፈለ፡፡

**ሁለት ሆነች** ወለደች፥ ተገላገለች።

**ሁለት ልብ ሆነ** አመነታ፥ ወላወለ፥ ሃሳቡ በአንድ አልፀና አለ።

**ሁለት መልክ አወጣ** ተጎሳቆለ፥ ከሳ፥ ጠቆረ።

**ሁለት ፀጉር አወጣ/ አበቀለ** ሸመገለ፥ በእድሜ ገፋ።

**ሁለተኛ** ቅ 1. ዳግመኛ። 2.ሌላ፥ ተጨማሪ። 3. በተራ ከመጀመሪያው ቀጥሎ የሚመጣ፥ የመጀመሪያው ተከታይ። 4. በደረጃ ወይም በማእረግ ከአንደኛው ዝቅ ያለ። 5. በደረጃ ወይም በማእረግ ከአንደኛው የሚበልጥ። *የሁለተኛ ዓመት ዩኒቨርሲቲ ተማሪ።*

**ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት** ስ ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት በሂላ የቀለም ወይም የቀለምና የሙያ ትምህርት የሚሰጥበት ትምህርት ቤት።

**ሁለት ምላስ/አፍ** ዋሾ፥ በፊት የተናገረውን ሽሮ ሌላ የሚናገር።

**ሁለት ባህርይ** ስ ኢየሱስ ክርስቶስ በአካላዊ ተዋህዶ የአምላክነትና የሰውነት ባህርያት አሉት የሚል ትምህርተ ሃይማኖት።

**ሁለት ነጥብ** ስ በእጅ ፅሁፍ ውስጥ ቃልን ከቃል ለመለየት በሁለት ቃላት መካከል ላይና ታች በመሆን የሚቀመጥ የስርአተ ነጥብ አይነት(:)።

**ሁለት አፍ ሰይፍ** በሁለቱም ጎኑ ስለት ያለው ሰይፍ።

**ሁለት እጅ** እጥፍ።

**ሁለት ፊት** በሁለት በኩል፥ ሁለት ወገን።

**ሁለንተና** ስ ጠቅላላ አካል።

**ሁለንተናዊ** ቅ አጠቃላይ።

**ሁሉ** ቅ መላው፥ ጠቅላላው።

**ሁሉ በሁሉ** በጠቅላላው፥ በድምሩ። *ሁሉ በሁሉ መቶ ብር ይሸጣል።*

**ከሁሉ ከሁሉ** በይበልጥ።

**ሁለገብ (ሁልገብ)** ቅ 1. በሁሉ ቦታ ሊገባ፥ ሊሰራ፥ ሊያገለግል የሚችል። ስ 2. ቁመቱ በጣም አነስተኛ የሆነ፥ ለምችና ለሌሎችም በሽታዎች በመድሃኒትነት ያገለግላል የሚባል ቅጠለ ሻካራ የእፅዋት አይነት።

**ሁሉም** ቅ በሙሉ፥ በጠቅላላ።

**ሁሉን አቀፍ (ሁልአቀፍ)** ቅ በሙሉ፥ ሁሉን የሚያካትት፥የሚያጠቃልል።

**ሁልቀን** ተው.ግ በእየቀኑ፥ ዘወትር፥ ሁልጊዜ።

**ሁልጊዜ (ሁሌ)** ተው.ግ ዘወትር።

**ሁልቆ መሳፍርት (እልቆ መሳፍርት)**

**ሁልቆ መሳፍርት የለውም** ስፍር ቁጥር የለውም፥ እጅግ በጣም ብዙ ነው።

**ሁር**

**ሁር ወጣ** 1. ነፃ ወጣ። 2. ባዶውን ቀረ፥ ሙልጭ ወጣ።

**ሁት (ውሃ)** "ኩት (ውሃ)" ን ተመ.

**ሁነኛ** "ሆነ" ስር ተመ.

**ሁናቴ** "ሆነ" ስር "ሁኔታ"ን ተመ.

**ሁኔታ** "ሆነ" ስር "ሁኔታ" ን ተመ.

**ሁከት** "አወከ" ስር ተመ.

**ሁዳዴ(ኩዳዴ)** ስ ክርስቲያኖች ከፋሲካ በፊት የሚፆሙት የኢየሱስ ፆም፤ አቢይ ፆም።

**ሁዳድ** "ሆደደ[1]" ስር ተመ.

**ሂ** የ "ሀ" ፊደል ሳልስ ዘር።

**ሂሰኛ** "ሂስ" ስር ተመ.

**ሂሳብ** ስ 1. በአሃዞች አማካይነት እየተሰላ የሚቀመር የአራቱ መደቦች (መደመር ፥ መቀነስ፥ ማብዛት፥ ማካፈል) የስሌት ዘዴ፥በግልፅ በተወሰኑ ፅንሰ ሃሳቦችና ምልክቶች አማካይነት የብዛትን፥ የቅርፅን፥ የቅንብርንና የመጠንን ትክክለኛ ጠባይና ግንኙነት ለመግለፅ የሚያስችል የስሌት ሳይንስ። 2. ለተገዛ ወይም ለተሸጠ ነገር ወይም ለአገልግሎት የሚከፈል ገንዘብ። *ያለበትን ሂሳብ አልከፈለም።*

**ሂሳቡን አስረከበ** በልዩ ልዩ ምክንያት የተቀበለውን ወይም በእጁ የነበረውን ገንዘብ ለሚመለከተው ሰጠ።

**ሂሳቡን አወራረደ** የወጪና የቀሪን ሂሳብ በማስረጃ ተሳሰበ።

**ሂሳቡን አገኘ** 1. ቅጣቱን አገኘ። 2.

ድርሻውን አገኘ።

**ሂሳብ አደረገ** ወጪና ገቢን አመሳከረ፣ አሰላ፣ ተሳሰበ።

**ሂሳብ አጣራ** ገቢና ወጪውን አመሳክሮ ትክክለኛነቱን አረጋገጠ።

**ሂሳብ ከፈተ** ባንክ ቤት ውስጥ ገንዘብ ለማስቀመጥ የሚያስችለውን ፎርማሊቲ አሟልቶ ባንኩ ለደንበኞቹ ከሚሰጠው አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነ።

**ሂሳብ ዘጋ** 1. በተወሰነ ጊዜ ለተወሰነ ስራ የተመደበን የገንዘብ ገቢና ወጪ በማመዛዘን ሂሳቡን አጠቃለለ። 2. የሚፈለግበትን እዳ ከፍሎ ጨረሰ። 3. በባንክ ውስጥ ያስቀመጠውን ገንዘብ በሙሉ ወሰደ።

**በ ____ሂሳብ** በ ___ዋጋ። *በ5 ብር ሂሳብ ገዛሁት።*

**በምን ሂሳብ** በምን ምክንያት።

**በእገሌ ሂሳብ** እገሌ በሚከፍለው፣ በእገሌ ገንዘብ።

**ሂሳብ መርማሪ** ስ በመንግስታዊ ወይም በህዝባዊ ድርጅት ውስጥ በተወሰነ ወቅት ገቢና ወጪ የሆነው ገንዘብ በህጉ መሰረት በትክክል በስራ ላይ መዋሉን መርምሮ አስፈላጊውን ሪፖርት ለሚመለከተው ክፍል እንዲያቀርብ ህጋዊ መብት የተሰጠው ግለሰብ ወይም ቡድን፣ ኦዲተር።

**ሂሳብ ተቆጣጣሪ** ስ በአንድ ድርጅት ውስጥ ተመድቦ የድርጅቱ የእለት ተእለት የገንዘብ ነክ እንቅስቃሴ በትክክል መካሄዱን የሚከታተልና የሚያረጋግጥ ሰራተኛ።

**ሂሳብ ክፍል** ስ የአንድ ድርጅት አጠቃላይ ሂሳብ ነክ እንቅስቃሴ የሚካሄድበትና ገንዘብ ነክ አገልግሎት የሚሰጥበት የአስተዳደር ዘርፍ።

**[የ] ሂሳብ መኪና** ስ አሃዛዊ ስሌቶችን (መደመር÷መቀነስ÷ማብዛት÷ማካፈል) በተቀላጠፈ ሁኔታና በትክክል ለማስላት የሚያስችል ዘመናዊ መሳሪያ።

**[የ] ሂሳብ መዝገብ** ስ የገንዘብ ወጪና ገቢ መጠን የሚሰፍርበት ደብተር፣ መዝገብ።

**[የ] ሂሳብ መዝገብ አያያዝ** ስ 1. የገቢና የወጪ ሂሳብ አመዘጋገብና አያያዝ ዘዴ። 2. የገቢና የወጪ ሂሳብ አመዘጋገብና አያያዝ ዘዴን የሚመለከት የትምህርት ዘርፍ።

**[የ] ሂሳብ ሰራተኛ** ስ ሂሳብ ነክ የሆኑ ጉዳዮችን የሚያከናውን ሰራተኛ።

**[የ] ሂሳብ ሹም** ስ የአንድን ድርጅት ገቢና ወጪ እንዲሁም ሌላ ሂሳብ ነክ እንቅስቃሴን በበላይነት የሚመራ ሃላፊ።

**ሂስ** ስ 1. በደካማ ጎን ላይ የሚያተኩር አስተያየትና ነቀፋ። 2. በአንድ የስራ ውጤት÷ በተለይም በስነ ጥበብ ስራዎች (ስነፅሁፍ÷ ቲያትር፣ ሙዚቃ፣ ስእል÷...) ላይ የሚሰነዘር መዛኝ አስተያየት ። 3. ድክመትን ወይም ስህተትን ለማረም ሲባል በተሳሳተው ወገን ላይ የሚቀርብ ቂም በቀል የሌለበት ትችት።

**ሂሱን ዋጠ** የተሰነዘረበትን ሂስ አምኖ ተቀበለ።

**ሂሰኛ** ቅ ተቺ፣ አቃቂር አውጪ።

**ሃያሲ** ስ አንድን የስራ ውጤት በተለይም ስነፅሁፍንና ሌሎችንም የስነጥበብ ስራዎች በተወሰኑ መመዘኛዎች እየለካና እየገመገመ አስተያየት የመስጠት ችሎታ ያለው ሰው።

**ሂና** ስ ሴቶች እጅና እግራቸውን እነደዚሁም ፀጉራቸውን የሚያቀሉበት የእንሶስላ አይነት።

**ሂያጅ** " **ሄደ**" ስር ተመ.

**ሂደት** ዝ.ከ.

**ሂድ** ዝ.ከ.

**ሂጃ** ዝ.ከ

**ሃ** የ "**ሀ**" ፊደል ራብእ ዘር።

**ሃ ብሎ ጀመረ** ከመነሻው÷ ከመጀመሪያው ጀመረ።

**ሃ አለ** 1. ፊደል ቆጠረ። *ሃ ሳይሉ ፅሁፈት ውል ሳይዙ ሙግት።* 2.ጀመረ። *ገና ሃ ከማለቱ ስራውን ጠላው።*

**ከሃ እስከ ፐ** ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ። *ጉዳዩን ከ ሃ እስከ ፐ አውቀዋለሁ።*

**ሃሁ** ስ 1. ፊደል ቆጠራ÷ የፊደል ትምህርት። 2. የመጀመሪያ ደረጃ እውቀት። *የቴክኖሎጂ ሃሁ።*

**ሃሁ አለ** 1. ፊደል ቆጠረ÷ ተማረ። 2.መጠነኛ የሆነ ትምህርት አገኘ።

**ሃላፊ** "**አለፈ**" ስር ተመ.

**ሃላፊነት** ዝ.ከ.

**ሃሎ (አሎ)** በስልክ ጥሪ ጊዜ መልእክት ለመቀበል ወይም አድማጩ መስማቱን ለማረጋገጥ የሚባል ቃል።

**ሃመል [እሳት]** ስ በመጋቢት ወር የሚወጣ የኮከብ አይነት። በተጨማሪ "**ኮከብ ቆጠራ**"ን ተመ.

**ሃመልማል** ስ ልምላሜ÷ አረንጓዴነት።

**ሃመር** ቅ ቀይነት ያለው። *ሃመር ፈረስ።*

**ሃምራዊ** ቅ 1. ቀይነት ያለው። 2. ወይንማ።

**ሃሙስ** ስ በረቡእና በአርብ መካከል ያለው ቀን ስም፣ ከእሁድ ጀምሮ ሲቆጠር የሳምንቱ አምስተኛ ቀን።

**ሃሚተኛ** " **አማ** " ስር ተመ.

**ሃሚና** የ"ሳሊበሳ"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

**ሃማል** ስ ተሸካሚ፥ ኩሊ።

**ሃሜታ** "**አማ**" ስር "**ሃሜት**"ን ተመ.

**ሃሜት** "**አማ**" ስር ተመ.

**ሃምሌ** ስ ከሰኔ ቀጥሎ የሚመጣ የአመቱ 11ኛ ወር ስም።

**ሃምራዊ** "**ሃመር**" ስር ተመ.

**ሃምሳ** "**አምሳ**" ን ተመ.

**ሃምስ** ስ እንደ " ሄ "፥ "ሌ " ፥ "ሜ" ፥ ... ያሉ በራብእና በሳድስ መካከል የሚገኙ የአምስተኛዎቹ ፊደላት ዘሮች መጠሪያ ወይም የድምፅ ምልክቶች።

**ሃምበርገር** ስ የተፈጨ ወይም በስሱ የተቆረጠ ስጋ ከተጠበሰ በሗላ እሁለት በተሰነጠቀ ዳቦ ውስጥ ተጨምሮ የሚዘጋጅ ምግብ።

**ሃሞት (አሞት)** ስ ከጉበት ውስጥ የሚመነጭና በሆድ እቃ ውስጥ ምግብን ለማላም የሚረዳ ቅጠልማ ቀለም ያለው መራራ ፈሳሽ።

**ሃሞቱ ፈሰሰ** ተስፋ ቆረጠ፥ ደከመ፥ ዛለ።

**ሃሞተ መራራ ቅ** ኀበዝ፥ ቆራጥ፥ ወኔ ያለው፥ ኮስታራ።

**ሃሞተ ቢስ ቅ** ወኔ ቢስ፥ መንፈስ ደካማ፡ ፈሪ።

**ሃረግ** ስ 1. ከአጠገቡ በሚገኙ ዛፎችና ቋሚ ነገሮች ላይ እየተጠመጠመ ወይንም መሬት ለመሬት እየተሳበ የሚያድግ እንደ አዞ፥ ጠሮ፡ ሃረግ ራሳ ያለ የእፅዋት አይነት። 2. ለጌጥ ሲባል በጥርብ እንጨት፥ በመፃህፍት፥ በሃውልቶችና በልዩ ልዩ ነገሮች ላይ እንደ ሃረግ እየተጠላለፈ የሚሰራ ንድፍ። 3. ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ ቃላት የሚገኙበት፥ ማሰሪያ አንቀፅ የሌለው የአረፍተ ነገር ክፋይ። ምሳ. የሆነው ሆኖ /ወደ ቤቱ፥ ...።

**ሃረጉን ቆጠረ /መዘዘ** የዘር ሃረጉን ዘረዘረ፡ ትውልዱን ቆጠረ።

**ሃረግ ጣለ** የሃረግ ንድፍ ሰራ።

**ሃረግ ሬሳ (አረግ ሬሳ)** ስ ሰዎች ለምች መድሃኒትነት የሚጠቀሙበት የሃረግ ወገን የሆነ የእፅዋት አይነት።

**ሃሩር** ስ 1. ከፍተኛ የፀሃይ ሙቀት፥ ቃጠሎ። 2. ቀም ፀሃፊዎች ጭማቂውን ለጥቁር ቀለም መበጥበጫ የሚጠቀሙበት እስኪያር ድረስ ተቆልቶ የተቀቀለ የስንዴ ወይም የገብስ ውሃ።

**ሃራ ዘመን** ስ አንድ ሰው በየአመቱ ስለሚያጋጥመው መጥፎም ሆነ ጥሩ ነገር በቅድሚያ ለማወቅ የሚደረግ በኮከብ ቆጠራ ላይ የተመሰረተ ትንበያ።

**ሃራም** ስ ክልክል፥ ግዝት፥ እርም የሆነ ነገር (ብዙውን ጊዜ በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች አካባቢ የሚነገር)።

**ሃራራ** ስ የቡና፥ የጫት፥ የትንባሆ ሱስ፤ ፍላጎት።

**ሃራጅ** ስ እንዲሸጥ የተወሰነ ንብረት በጨረታ ወይም ገበያ ላይ በተገኘው ዋጋ የሚሸጥበት መንገድ።

**በሃራጅ ሸጠ** በአንድ ጨረታ ወይም ገበያ ላይ በተገኘው ዋጋ ሸጠ።

**ሃር** ስ 1. ለስላስ የሆነ፥ እንደሸረሪት ድር ያለና ከሃር ትል የሚገኝ ነጭ ፈትል። 2. ከሃር ወይም ሃርን ከመሰለ ፈትል የሚሰራ፥ እንደአስፈላጊነቱ በልዩ ልዩ ቀለማት የሚዘጋጅ ለስላሳ ጨርቅ፥ ልብስ።

**የሃር ትል** ስ የሃር ድር የምትሰራ ትል።

**ሃርሞኒካ** ስ በትንፋሽ ወይንም በንፋስ የሚሰራ ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያ(ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።

**ሃር አምባ**

**ሃርአምባና ቆቦ** የተራራቀ፥ የማይገናኝ፥ የማይመሳሰል (ሁኔታ፥ ነገር፥ ቦታ)።

**ሃሰት** ስ 1. ውሸት፥ እብለት፥ ቅጥፈት። ቅ 2. ትክክለኛ ወይም እውነተኛ ያልሆነ። *የሃሰት ምስክር።*

**ሃሰተኛ** ቅ 1. ውሸታም። 2. ትክክለኛና እውነተኛ ያልሆነ። *ሃሰተኛ የገንዘብ ኖት።*

**ሃሳብ (አሳብ)** ስ 1. በአእምሮ ውስጥ የሚቀረፅ፥ የሚታቀድ፥ የሚመላለስ ፅንሰ ነገር፥ ግንዛቤ። 2. ስጋት፥ ጭንቀት። *ሃሳብ የሆነብኝ የልጄ ነገር ነው።* 3. አላማ፥ እቅድ፥ ፍላጎት። 4. አስተያየት። *በዚህ ጉዳይ ላይ ሃሳብህ ምንድን ነው?*

**ሃሳቡ ተቃለለ** ጭንቀቱ፥ ችግሩ ተወገደ።

**ሃሳቡ ተከፈለ** 1. አመነታ፥ ሁለት ልብ ሆነ። 2. ሃሳቡ ተቃለለ።

**ሃሳቡን ለወጠ** ውሳኔውን ሻረ።

**ሃሳቡን ቆረጠ** ወሰነ፤ አንድ ልብ ሆነ።

**ሃሳቡን አነሳ** 1. ያቀረበውን ሃሳብ ተወ። 2. ሃሳብ አመነጨ፥ አቀረበ።

**ሃሳቡን ጣለ** ደንታ ቢስ ሆነ፤ ስለችግሩ ማሰብ ተወ፤ አረፈ፥ ተደላደለ።

**ሃሳቡን ፈፀመ** አላማውን ከግቡ አደረሰ፥ አሳካ።

**ሃሳብ ተቀበለ** አስተያየት፥ ምክር ጠየቀ፥ ሰማ ወይም ተቀበለ።

**ሃሳብ አቀረበ** አስተያየት ሰጠ።

**ሃሳብ አካፈለ** አስተያየት ወይም ምክር ሰጠ

**ሃሳብየለውም/የለበትም**1.ችግር

የለበትም። 2. ለምንም ነገር አይጨነቅም፥ደንታ ቢስ ነው።

**ሃሳብ የለሽ** ቅ የሚያሳስበው፥ የሚያስጨንቀው ነገር የሌለበት።

**ሃሳብ ያዘው /ገባው** የሚያሳስብ ነገር አጋጠመው፥ ጨነቀው።

**በሃሳብ ተዋጠ** ስለአንድ ነገር በማሰላሰል አእምሮው ተያዘ፥ ተከዘ።

**በሃሳብ ተግባቡ** በአላማ፥ በፍላጎት ተስማሙ።

**ሃሳበ ቢስ** ቅ ግድ የለሽ፥ ደንታ የሌለው።

**ሃሳበ ብኩን** ቅ የረጋ ሃሳብ የሌለው።

**ሃሳበ ውሱን** ቅ ጠባብ አመለካከት ያለው፥ አርቆ የማያስተውል።

**ሃሳበ ግትር** ቅ እኔ ያልኩት ካልሆነ የሚል፤ ስህተት መሆኑን ቢያውቅም አንድ ጊዜ የያዘውን አስተያየት ለመለወጥ የማይሻ፤ መንቻካ።

**ሃሳባዊ** (ብ.ቁ. **ሃሳባውያን**) ስ 1.የሃሳባዊነት ፍልስፍና ተከታይ። ቅ 2. በሃሳባዊ ፍልስፍና ላይ የተመሰረተ (አመለካከት)።

**ሃሳባዊነት** ስ ሃሳብን ከቁስ አካል የሚያስቀድም የፍልስፍና አመለካከት ወይም ሃሳብ የቁስ አካል መገኛ ነው የሚል የፍልስፍና ዘርፍ።

**ሃሳዊ** ቅ ዋሾ፥ ቀጣፊ፥ ሃሰተኛ።

**ሃሳዊ መሲህ** ስ 1. ያልሆነውን ነኝ የሚል አታላይ፥ አሳሳች ነቢይ። ቅ 2. አሳሳች፥ ሃሰተኛ (ሰው)።

**ሃሴት** ስ ደስታ።

**ሃሴት አደረገ** ተደሰተ፥ ፈንጠዝያ አደረገ።

**ሃሺሽ** ስ ሱስ የሚያሲዝና አእምሮን የሚያስት አደንዛዥ እፅ።

**ሃቅ**[1] ስ 1. እውነት፥ ትክክል የሆነ፥ የተረጋገጠ ነገር ። 2. የራስ ድርሻ፥ አንጡራ ንብረት።

**ሃቀኛ** ቅ እውነተኛ፥ ትክክለኛ።

**ሃቅ**[2] (**አቅ**) ስ ሶስት ክንድ ርዝመት ያለው የብትን ልብስ ወይም የሸማ መጠን፥ ልክ።

**ሃበሻ (አበሻ)** ስ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚጠራበት አጠቃላይ ስም።

**[የ] ሃበሻ ልብስ** ስ ከጥጥ ፈትል በሸማኔ የሚዘጋጅ የኢትዮጵያውያን ልብስ።

**[የ] ሃበሻ ቀሚስ** ስ ነጠላና ቀሚስ ሆኖ የተዘጋጀ የሃበሻ ልብስ።

**[የ] ሃበሻ ጎመን** ስ በአንድ ላይ እጅብ ብሎ የሚበቅልና ቁመቱ አጠር ብሎ ቅጠሉ አነስ አነስ ያለ የጎመን አይነት።

**ሃብሃብ** ስ ቅርፁ ሞላላ ወይም ክብ የሆነ፥ ዱባ የሚመስል፥ ውስጡ ቀይ ሆኖ ጥቋቁር ፍሬዎች ያሉትና ጣፋጭ ውሃ በብዛት የያዘ የፍራፍሬ አይነት፤ ተክሉም ሃብሃብ ይባላል፤

**ሃብል** ስ አንገት ላይ ለጌጥ የሚደረግ ከብር ወይም ከወርቅና ከመሳሰሉት ማእድናት የሚሰራ ቀጭን ሰንሰለት።

**ሃብት** ስ 1.ንብረት፥ ጥሪት። 2. እድል፥ እጣ።

**ሃብቷ ቀና** እድሏ አማረላት፥ ተሳካላት፤ አገባች (ልጃገረድ)።

**ሃብተ ቀና** ቅ እድለኛ።

**ሃብተ ሰባራ/ ስንኩል** ቅ እድለ ቢስ።

**ሃብተ ስጋ** ስ ምድራዊ ፀጋ፥ ሃብት።

**ሃብተ ቢስ** ቅ እድለ ቢስ።

**ሃብትሽ በሃብቴ** ስ ባልና ሚስት ከተጋቡ በሂላ የሚያፈሩት ንብረት የሁለቱም የጋራ እንዲሆን የሚያደርግ የጋብቻ ውል፥ ስምምነት።

**ሃብታም** ቅ 1. ባለፀጋ፥ ባለብዙ ንብረት፥ ከበርቴ። 2.(ዘይ.) እድለኛ።

**ሃቤየስ ኮርፐስ** ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ ሳልተወሰነ ጊዜ መታሰርን የመቃወም መብት ወይም አንድን ሰው በእስር ለማቆየትም ሆነ ላለማቆየት ብይን ይሰጥበት ዘንድ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ የሚያደርግ የፅሁፍ ትእዛዝ።

**ሃተታ** "**አተተ**" ስር ተመ.

**ሃች አምና (ታች አምና፥ ካች አምና)** ስ ከአምና በፊት የነበረው አመት።

**ሃኔ** ስ ለማረጃና ለማወራረጃ የሚያገለግል እንደ ደጋን የጎበጠ ሰፊ ጎራዴ።



ሃኔ

**ሃኪም** ስ የህሙማንን በሽታ አይቶና መርምሮ አስፈላጊውን እርዳታ የሚሰጥና መድሃኒት የሚያዝ፥የሚያክም የጤና ባለሙያ።

**ሃኪም ቤት** ስ የጤና ምርመራና የህክምና ተግባር የሚከናወንበት ተቋም።

**የሃኪም እረፍት** ስ ሃኪም የሚሰጠው ወይም የሚያዘው እረፍት።

**የሃኪም ወረቀት** ስ ሃኪም መድሃኒት ያዘዘበት ወይም ስለህመሙ የተናገረበትና አስተያየት የሰጠበት ፅሁፍ።

**ሃካይ** ቅ ክፉ፥ ተንኮለኛ።

**ሃኬት** ስ ተንኮል፥ ክፋት።

**ሃኬተኛ** ቅ ተንኮለኛ፥ ክፉ።

**ሃዋላ** ስ በባንክ ወይም በፖስታ ቤት አማካይነት ገንዘብ የሚላክበት መንገድ፥ ዘዴ።


**ሃዋርያ** (ብ.ቁ. **ሃዋርያት**) ስ 1. ወንጌልን ለማስተማር በክርስቶስ ተመርጦ የነበረ አስተማሪ ወይም መምህር (ተመርጠው የነበሩት 12 ሃዋርያት ናቸው)። 2. የአንድ የተወሰነ ኣይነት እምነት ወይም ትምህርት ግንባር ቀደም ሰባኪ፥ አስተማሪ።

**ሃውልት** ስ በሰው ወይም በሌላ አምሳል ከድንጋይ ወይም ከነሃስ፥... የተሰራ መታሰቢያ

**ሃውልትየሆን ስራ ሰራ** ቋሚና ጠቃሚ የሆነ ስራ ሰራ።

**ሃውዛ** "**አውዛ**"ን ተመ.

**ሃዘን** (**አዘን**) ስ 1.ለቅሶ፥ ዋይታ። 2. ትካዜ፥ መከፋት።



ሃውልት

**ሃዘኑን ገለፀ** ያዘነ መሆኑን አሳወቀ።

**ሃዘን ላይ ነው** 1. ለቅሶ ላይ ነው። 2. ትካዜ ላይ ነው፥ ተከፍቷል።

**ሃዘን ገባው** በጣም አዘነ፥ ተከዘ፥ ተከፋ።

[የ] **ሃዘን ተካፋይ** ለቅሶ ወይም ሃዘን ባለበት ቦታ በመገኘት አለዚያም የተሰማውን ሃዘን በተለያየ መንገድ (በደብዳቤ፥ በስልክ፥...)በመግለፅ የሚችን ቤተሰብ የሚያፅናና ወዳጅ፥ ዘመድ።

**ሃዜታ** "**አዘን**" ስር "**አዜታ**" ን ተመ.

**ሃዘንተኛ** ቅ ዘመድ ወይም ወዳጅ የሞተበትና በለቅሶ ላይ ያለ።

[የ] **ሃዘን ልብስ** ስ በሃዘን ጊዜ የሚለበስ ጥቁር ልብስ፤ ከል።

[የ] **ሃዘን ቤት** ስ ለቅሶ ቤት።

**ሃያ** ስ 1. በአስራ ዘጠኝና በሃያ አንድ መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ፤ በአሃዝ ሲፃፍ "፳" ፥ "20" ነው። ቅ 2. ብዛቱ ሁለት አስሮችን የሚያህል። *ሃያ ሰዎች።*

**ሃያል** (ብ.ቁ. **ሃያላን**) ቅ 1. ብርቱ፥ ጠንካራ፥ ጉልበታም፥ ሃይለኛ። 2. ሁሉን ማድረግ የሚችል። *ሃያሉ እግዚአብሄር።*

**ሃያላን መንግስታት** ስ በባህል፥ በፖለቲካና በኢኮኖሚ የበለፀጉና በሌሎች አገሮች ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ተፅእኖ ለማድረግ የሚችሉ አገሮች (ሩሲያ፥ ቻይና፥ አሜሪካ፥ እንግሊዝና ፈረንሳይ)።

**ሃያሲ** "**ሂስ**" ስር ተመ.

**ሃይ**[1]

**ሃይ አለ** ግ ከለከለ፤ አገደ፤ ተቆጣጠረ፤ ገላገለ።

**ሃይ**[2]

**ሃይ በል (ሃይ በሌ) አለ** ግ አጣደፈ፥ አፋጠነ (ስራን፥ መንገድን፥ ...)።

**ሃይል** ስ 1. ብርታት፥ ጥንካሬ፥ ጉልበት፥ አቅም። 2. አንድን ተግባር የሚፈፅም ቡድን። 3. ዘዴን ያልተከተለ አስገዳጅ ግፊት።

**በሃይል** ተው.ግ. 1. በብዛት፥ ከመጠን በላይ፥ በጣም። *በሃይል መጠጣት ሰውነትን ይጎዳል።* 2. በጠና፥ እጅግ በጣም። *በሃይል ታሟል።* 3. ጉልበትን በመጠቀም፤ በማስገደድ።

**ሃይለ ቃል** ስ 1. የሃይል፥ የቁጣ ንግግር። 2. በአንድ ፅሁፍ ወይም ንግግር ውስጥ ዋናውን ሃሳብ ወይም ፍሬ ነገር የያዘ ቃል፥ ሃረግ፥ አረፍተ ነገር።

**የሃይል ሚዛን** ስ ከሌላው ወገን ጋር ሲነፃፀር በመብለጥ ወይም በማነስ የሚታይ የሃይል፥ የጉልበት፥ የአቅም መጠን።

**የሃይል ስራ** ስ በዘዴ፥ በብልሃት ያልሆነ፥ የጉልበት ስራ።

**ሃይለኛ** ቅ 1. ጎበዝ፥ ብርቱ፥ ጉልበተኛ፥ ጠንካራ። 2. ከባድ። *ሃይለኛ ዝናም*። 3. ቁጡ፥ የማይበገር፤ ግልፍተኛ ኮስታራ።

**ሃይማኖት** ስ አለምን የፈጠረና ተፈጥሮን በበላይነት የሚቆጣጠር መለኮታዊ ሃይል እንዳለ የሚቀበል በእምነት ላይ የተመሰረተ አመለካከት፤ እምነት።

**ሃይማኖቱን ለወጠ** የነበረውን (ይዞት የቆየውን) ሃይማኖት ትቶ የሌላ ሃይማኖት ተከታይ ወይም አማኝ ሆነ።

**ሃይማኖት ያውርድ** አውደማ ተጥሎ ወይም ማእድ ቀርቦ ሳለ የሚደርስ እንግዳ ምርቱ ይበርክት፥ ማእዱ ይባረክ ለማለት የሚናገረው የመልካም ምኞት መግለጫ ቃል።

**ሃይማኖተኛ** ቅ 1. የተቀበለውን ወይም የሚከተለውን ሃይማኖት ትእዛዝና ስርአት በፅኑ የሚያከብር አማኝ። 2. ጠንካራ፤ ቃሉን የማያጥፍ ታማኝ።

**ሃይማኖተ ቢስ** ቅ በቃሉ የማይፀና፥ ከሃዲ።

**ሃይማኖተ አበው** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ቀደምት የሆኑ የክርስትና ሃይማኖት ሊቃውንት ያዘጋጁት ሃይማኖታዊ ትምህርትን የያዘ መፅሃፍ።

**ሃይማኖታዊ** ቅ ሃይማኖት ነክ የሆነ፤ በእምነት ላይ የተመሰረተ።

**ሃይቅ** ስ ዙሪያውን በመሬት የተከበበ ስፋትና ጥልቀት ያለው የውሃ ክምችት።

**ሃይድሮጅን** ስ ከንጥረ ነገሮች ሁሉ ቀላል

የሆነና ከኦክስጂን ጋር ሲዋሃድ ውሃን የሚያስገኝ፥ ቀለምና ሽታ የሌለው በቀላሉ የሚነድ ጋዝ።

**ሃይድሮጅን ቦንብ** ስ ከፍተኛ የሃይድሮጅን ክምችት የያዘና እጅግ በጣም ታላቅ ጥፋት ሊያደርስ የሚችል ቦንብ።

**ሃይጅን** ስ የጤና አጠባበቅ ትምህርት።

**ሃዲስ ኪዳን** "አደሰ" ስር "አዲስ ኪዳን"ን ተመ.

**ሃዲድ** ስ ለባቡር መሄጃ በመሬት ላይ የተዘረጋ የተጋደመ መሰላል የሚመስል የብረት ንጣፍ።

**ሃዲድ ብረት** ስ ጠንካራ የሆነ የብረት አይነት።

**ሃጅ**[1] ስ ወደ መካ መዲና የሚደረግ የእስልምና ሃይማኖታዊ ጉዞ።

**ሃጂ** ስ መካ መዲና ደርሰው የተመለሱ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች የሚጠሩበት የአክብሮት ስም።

**ሃጅ**[2] "ሄደ" ስር "ሂያጅ"ን ተመ.

**ሃገር (አገር)** ስ 1. በውስጡ ህዘቦች የሚኖሩበት፥ የተወሰነ ጂኦግራፊያዊ ክልል ያለውና በአንድ መንግስታዊ አስተዳደር ስር የሚገኝ ግዛት። 2. በተወሰነ ጂኦግራፊያዊ ክልል ውስጥ ያለ መሬት። 3. የትውልድ ስፍራ ወይም አካባቢ። 4. (ዘይ.) በተወሰነ ክልል ውስጥ የሚኖር ህዝብ። *ሰውየውን አገር ይወደዋል።*

**ሃገሩን ሽጠ** ለግል ጥቅሙ ሲል የሃገሩን ጥቅም ለሌላ ወገን አሳልፎ ሰጠ።

**አገር ነው** 1. ብዙ ነው። *የገዛሁት ቡና አገር ነው።* 2. ሰፊ ነው። *አዳራሹ አገር ነው።*

**አገር አጠፋ** ህገወጥ ስራ ሰራ፥ ጥፋት አደረሰ።

**አገር አጥፊ** ቅ ስርአት የለሽ፥ ባለጌ።

**አገር ፈታ** አወከ፥ አስቸገረ።

**አገሬው** ህዘቡ።

**ሃገረሰብ** ቅ 1. ባህላዊ ወይም የባህል። *የሀገርሰብ መድሃኒት።* ስ 2. ገጠር፥ አገር ቤት። 3. ያገር ቤት ሰው።

**አገረ ገዢ** ስ በንጉስ ይሾም የነበረ አገር አስተዳዳሪ።

**አገር ምድሩ** 1. ስፍራው፥ አካባቢው ሁሉ። 2. ሁሉም፥ ጠቅላላው።

**አገር ቂጥ** ቅ በጣም ሩቅ።

**አገር በቀል** ቅ ሃገር ውስጥ የተገኘ፥ የተቋቋመ።

**አገር ቤት** ስ ከከተማ ውጭ የሆነ አካባቢ፥ ገጠር፥ ባላገር።

**አገር አቋራጭ** ቅ ረጅም ርቀት ያለው፤ ረጅም ርቀት የሚጓዝ። *አገር አቋራጭ ውድድር /አገር አቋራጭ አውቶቡስ ።*

**አገር ወዳድ** ቅ ሃገሩንና ወገኑን የሚወድ፤ ብሄራዊ ስሜት ያለው።

**አገር ወገብ** ስ በቆላና በደጋ መካከል የሚገኝ ቦታ፤ ወይና ደጋ።

**አገር ጎብኚ** ስ የተለያዩ ቦታዎችን፥ ታሪካዊ ስፍራዎችን፥...እየተዘዋወረ የሚጎበኝ ሰው፤ ቱሪስት።

**[የ] ሃገር ልብስ** ስ 1. በአንድ ሃገር ወይም በተወሰነ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች የሚለብሱት ባህላዊ ልብስ። 2. ሃበሻ ልብስ።

**የሃገር ልጅ/ሰው** ስ የአንድ ሃገር ወይም የአንድ አካባቢ ተወላጅ።

**የሃገር ሽማግሌ** ስ ህዝብ የሚያከብረው፥ ወግንና ስርአትን የሚያውቅ አዛውንት።

**የሃገር ቀንድ** ስ ታዋቂ፥ ዋንኛ ሰው።

**የሃገር ባህል** ስ ባህላዊ የሆነ፥ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣና የተለመደ ወግ፥ ስርአት፥...።

**የአገር አባት** ስ የተጣላ የሚያስታርቅ ሽማግሌ፥ አዛውንት።

**ሃገርኛ** ቅ የሃገር ውስጥ የሆነ።

**ሃጋይ** ስ ከታህሳስ 26 እስከ መጋቢት 25 ያለውና ከመፀው ቀጥሎ የሚመጣ፥ ሙቀትና ድርቅ የሚታይበት የበጋ ወቅት፤ አጋይ።

**ሃግ**

**ሃግ አለ** ግ ገሰፀ፥ ተቆጣ፥ መከረ።

**ሃጢአት** ስ 1. ሃይማኖት የማይፈቅደው ስራ ወይም ድርጊት 2. ክፉ ስራ፥ ጥፋት፥ ወንጀል። 3. በፍትወተ ስጋ ግንኙነት ጊዜ ከወንድ ብልት የሚወጣ ፈሳሽ ዘር።

**ሃጢአት ገባ /ሰራ** ሃይማኖቱ የማይፈቅድለትን መጥፎ ስራ ሰራ ወይም አደረገ።

**ሃጢአተኛ** ቅ 1. ሃይማኖቱ የማይፈቅድለትን ስራ የሰራ። 2. ወንጀለኛ፥ በደለኛ፥ ክፉ ሰሪ።

**ሃጥእ (ብ.ቁ. ሃጥአን)** ስ ሃጢአተኛ ሰው።

**ሃጫ** ቅ ነጭ፤ በረዶ የሚመስል።

**ሃጫ በረዶ** ስ ደቃቅ በረዶ።

**ሃፍረት** "አፈረ" ስር "እፍረት"ን ተመ.

**ሄ** የ"ሀ" ፊደል ሃምስ ዘር።

**ሄሄ** " አሄሄ"ን ተመ.

**ሄሊኮፕተር** ስ በላይዋ ላይ ባሉት ጠፍጠፍ ያሉ ተሽከርካሪ ዘንጎች አማካኝነት ለመብረርና በትንሽ ቦታ ላይ ለማረፍ የምትችል የአውሮፕላን አይነት።

**ሄደ** ግ 1. ተጓዘ፥ ገሰገሰ፥ ተራመደ። 2. ስፍራን

ለቀቀ። *ከዚህ አካባቢ ሄዷል።* 3. (ዘይ.) ግብረስጋ ፈፀመ። *ከሴት መሄድ ጀምሯል።* 4. በዛ፥ ናረ፥ ባለማቋረጥ ቀጠለ። *የህዝቡ ቁጥር ሄደ።* 5. ተሸጠ። *እቃው በስንት ብር ሄደ?* 6. ተስማማ። *ሸሚዙ ከኮቱ ጋር ይሄዳል።*

**ሂያጅ (ሃጅ)** ቅ 1. መንገደኛ፥ ተጓዥ። 2. ገስጋሽ። 3. የማይቆይ፥ የማይሰነብት። 4. (ዘይ.) ሴሰኛ።

**ሂደት** ስ ወደ ውጤት የሚያመራ፥ የተከታተለና የተያያዘ ድርጊት፥ ክንዋኔ፥ እንቅስቃሴ።

**ሂያጅ** ስ አሂዶ

**መሄጃ** ስ 1. መራመጃ፥ መተላለፊያ መንገድ። 2. መጠጊያ ዘመድ፥ ረዳት። 3. መሸሻ። 4. መሳፈሪያ ገንዘብ። 5. መጓጓዣ (መኪና፥ በቅሎ፥...)።

**ተካሄደ** ግ ተከናወነ፥ ተሰራ።

**አሄደ** ግ 1. የእህልን ክምር በአውድማ ላይ ዘርግፎ በከብቶች እግር አበራዩ፥ እህሉን ወቃ። 2. የትርጓሜ መምህር ምስጢረ መፃህፍትን በአንድምታ ትርጓሜ እየተነተነ አስተማረ፥ አስረዳ። 3. የትርጓሜ ተማሪ ምስጢረ መፃህፍትን በአንድምታ ትርጓሜ ተማረ፥ አወቀ። 4. በሃይል መታ፥ ደበደበ።

**አሂዶ** ስ በከብቶች አማካይነት በአውድማ ላይ እህል የመውቃት ወይም የማበራየት ስራ፤ ሂያጅ።

**አህያጅ** ስ ለእህል ውቂያ በአውድማ ላይ የሚዞሩ ከብቶችን ከሂላ ከሂላቸው እየሄደ የሚነዳ ሰው።

**አካሄደ** ግ 1. አንቀሳቀሰ፥ መራ፥ ሰራ (ስራን)። 2. አጠናቀቀ፥ አከናወነ፥ ፈፀመ። 3. በአውድማ ላይ የአሂዶን ስራ አገዘ ወይም ረዳ።

**ማካሄጃ** ስ ማንቀሳቀሻ፥ ማከናወኛ። *ለስራው ማካሄጃ ገንዘብ ተገኝቷል።*

**አካሄድ** ስ 1. አረማመድ። 2. ሁኔታ፥ አኳኋን፥ አዝማሚያ፥ አቅጣጫ። *የነገሩ አካሄድ አላማረኝም።*

**አስሄደ** ግ አቀላጠፈ፥ ቶሎ ቶሎ ሰራ።

**ያስኬዳል** 1. ያስችላል፥ ያዋጣል። *እሱ ያለውም ዘዴ ያስኬዳል።* 2. ይወስዳል፥ ያደርሳል። *ይህ መንገድ ወደ ባቡር ጣቢያ ያስኬዳል።* 3. ለመሄድ ወይም ለመራመድ ወይም ለማለፍ ያስችላል፥ ያመቻል። *ይህ መንገድ በመኪና ያስኬዳል?* 4. ይወስዳል፥ ይፈጃል። *ከአዲስ አበባ ናዝሬት በመኪና ሁለት ሰአት ያህል ያስኬዳል።*

**ሀ** የ "ሀ" ፊደል ሳድስ ዘር።

**-ሀ$^{1}$** 1. በግስ መጨረሻ እየገባ የሁለተኛ መደብ፥ ነጠላ ቁጥር ፥ ተባእታይ ፆታ ባለቤትን የሚያመለክት ምእላድ (ለምሳሌ "መቼ መጣህ" በሚለው ግስ ውስጥ "-ህ" "አንተ" የሚለውን ባለቤት አመልካች ምእላድ ነው)።

**-ሀ$^{2}$** በግስ መጨረሻ እየገባ የሁለተኛ መደብ፥ ነጠላ ቁጥር፥ የተባእታይ ፆታን ተሳቢነት የሚያመለክት ምእላድ (ለምሳሌ " አስተማረህ" በሚለው ግስ ውስጥ " -ህ" "አንተን" የሚለውን ተሳቢ አመልካች ምእላድ ነው)።

**-ሀ$^{3}$** 1. በስም ላይ እየተጨመረ የሁለተኛ መደብ ባለቤትነትን ወይም ባለ ገንዘብነትን የሚያመለክት ምእላድ። (ለምሳሌ " መፅሃፍህ " በሚለው ቃል ውስጥ " -ህ " " ያንተ " የሚለውን የባለገንዘብነት ሁኔታ የሚያመለክት ምእላድ ነው።) 2. አድራጊን ወይም ድርጊት ተቀባዩን የሚያመለክት ምእላድ። *መሄድህ በጄ/ መታሰርህ ተሰምቷል።*

**ሀለተ ወርቅ** ስ በትረ መንግስት፥ የወርቅ ዘንግ።

**ሀሊና** ስ ክፉና ደግን ለመለየት የሚያስችል አእምሮ ወይም ልቦና።

**ሀሊናውን ሳተ** አእምሮውን አጣ፥ ሳተ።

**ሀሊና ቢስ** ቅ የማያመዛዝን፥ የማያገናዝብ፤ ይሉኝታ የሌለው።

**የሀሊና ወቀሳ** ስ በሰሩት ጥፋት ወይም ስህተት የሚመጣ ፀፀት።

**የሀሊና ፀሎት** ስ ድምፅ ሳያሰሙ የሚደረግ ፀሎት።

**የሀሊና ፍርድ** ስ በራስ አእምሮ ሁኔታን በማመዛዘን የሚሰጥ ፍርድ።

**ሀልም** ስ 1. በእንቅልፍ ልብ ወይም በእንቅልፍ ላይ እንዳሉ የሚታይ ሃሳብ፥ ድርጊት ወይም ራእይ። 2. (ዘይ.) የማይሳካ፥ ከንቱ ምኞት።

**ሀልም ሀልም (እልም እልም) አለ** በጣም ጥቂት ወይም ትንሽ ተሰማ። (ለማጣፋጫ የሚጨመር ጨው፥ ስኳር፥....)።

**ሀልም ሆኖ ቀረ** ሳይፈፀም፥ ሳይሳካ፥ ተግባራዊ ሳይሆን ቀረ።

**ሀልም ያርገው/ይሁን** የተባለው ክፉ ወይም መጥፎ ነገር ውሸት ይሁን፥ አይፈፀም፥ አይድረስ ለማለት የሚነገር የምኞት መግለጫ አባባል።

**ሀልመ ሌሊት** ስ በእንቅልፍ ልብ በተመሰሉ የሚፈፀም የፍትወተ ስጋ ግንኙነት።

**የሀልም ሩጫ** የማይሳካ፥ ከንቱ፥ ዋጋ ቢስ ልፋት።

**የሀልም እንጀራ** የማይገኝ፥ ባዶ፥ በተስፋ ብቻ ያለ፤ ከንቱ ምኞት።

**ሀልመኛ** ቅ ሊያገኝ ከሚችለው በላይ የሚመኝ።

**ሀልውና** ስ ኑሮ፥ የመኖር ባህሪ።

**ህልውና አገኘ** 1. ተመሰረተ፥ ተቋቋመ። 2. መኖሩ ታወቀ፥ ህጋዊ ሰውነት አገኘ።

**ህልውናው ተጠበቀ** የመኖር መብቱ ተጠበቀ።

**የህልውና ጥያቄ** የመኖር ወይም ያለመኖር ጥያቄ። *ስራ ማግኘትና አለማግኘት የህልውና ጥያቄ ነው።*

**ህልፈት** "**አለፈ**" ስር "**እልፈት**"ን ተመ.

**ህመም** ስ 1. በሽታ፥ ደዌ፥ ጤና ማጣት። 2. ከበሽታ የተነሳ የሚሰማ ስሜት፥ ስቃይ።

**ህመምተኛ** ቅ በሽተኛ፥ ጤንነቱ የተጓደለ።

**ህሙማን** (ነጠ.ቁ **ህሙም**) ስ. ህመምተኞች።

**ህማማት** (**ማማት**) ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ ) ከሆሳእና ማግስት ጀምሮ እስከ ቅዳሜ ስኡር ያለው ጊዜ።

**ህማማተ መስቀል** ስ በወንጌል እንደተፃፈው ኢየሱስ ክርስቶስ በእለተ አርብ የተቀበላቸው 14ቱ ስቃያት (መያዝ፥ መታሰር፥ በጥፊ መመታት፥ መገረፍ፥...)።

**ህም ህም አለ** ግ 1. ህም ህም የሚል ድምፅ አሰማ። 2. አጉተመተመ።

**ህቅ**

**ህቅታ** ስ ስርቅታ።

**ህቅ አለ** ግ ሞተ፥ አረፈ።

**ህቡእ** ቅ ድብቅ፥ ስውር፥ ምስጢራዊ።

**ህቡእ ድርጅት** ስ አባሎቹ እነማን እንደሆኑ እንዳይታወቅ በማድረግ ተግባሩን በምስጢር የሚያከናውን የፖለቲካ ድርጅት ወይም ሌላ ማህበር።

**ህብር** ቅ 1. በጠባይ ወይም በግብር ተመሳሳይነት ያለው። 2. ላዩን ሲያዩት ባለ አንድ ትርጉም ብቻ የሚመስልና ሲመሰጠር ግን ከአንድ በላይ የሆነ ትርጉም ያለው ቃል፥ ሃረግ።

**ህብረ ቀለም** ስ የልዩ ልዩ ቀለማት ቅንብር፥ ቅንጅት።

**ህብረ ትርኢት** ስ እንደዘፈን፥ ውዝዋዜ፥ ድራማ፥ አስቂኝ ቀልዶች፥... የመሳሰሉ ልዩ ልዩ መዝናኛዎች የሚቀርብበት የቴሌቪዥን ዝግጅት።

**ህብር ቅኔ** ስ በአንድ ቃል ወይም ሃረግ አማካይነት ሰምና ወርቁ ተቀናብሮ የሚገኝበት የቅኔ አይነት።

**ህብረት** ስ የተለያዩ ሰዎች ወይም ወገኖች ሃይላቸውን፥ እውቀታቸውን፥ ተግባራቸውን አስተባብረው ወይም አቀናጅተው በአንድነት የሚሰሩበት የመረዳዳት ሁኔታ፤ ስምምነት።

**በህብረት** ተው.ግ በጋራ፥ በአንድነት፥ በመደጋገፍ፥...።

**ህበረተሰብ** ስ 1. በተወሰነ አካባቢ አንድ አይነት ስርአትን፥ ህግን፥... እየተከተለ የሚኖር ህዝብ። 2. የስራቸው ወይም የኑሮአቸው ቦታና ሁኔታ የሚያገናኛቸው ሰዎች ባጠቃላይ። *የዩኒቨርሲቲ ህብረተሰብ።*

**ህብረተሰባዊነት** ስ በላብአደሩ የበላይ ገገርነት የሚመሰረት፥ የማምረቻ መሳሪያዎች በህዝብ ቁጥጥር ስር የሚሆኑበት ስርአተ ማህበር ወይም የዚህን ስርአተ ማህበር አይቀሬነትና ትክክለኛነት የሚያስተምር ርእዮተ አለም።

**[የ] ህብረት ሱቅ** ስ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን ሸቀጣሸቀጥና የፍጆታ እቃዎች በቀላሉ ለማግኘትና በተመጣጠነ ዋጋ መግዛት እንዲችሉ በማሰብ በጋራ የሚያቋቁሙት ሱቅ፥ መደብር።

**[ የ ] ህብረት ስምምነት** ስ በአንድ ድርጅት አሰሪና በድርጅቱ ሰራተኞች መካከል የሚደረግ ውል፥ ስምምነት።

**[የ] ህብረት ስራ ማህበር** ስ ሰዎች የኢኮኖሚ፥ የፖለቲካና የማህበራዊ ኑሮ ፍላጎታቸውን ለማሟላት እንዲረዳቸው በሙያቸው አንፃር ወይም ለአንድ አይነት ተግባር የሚመሰርቱት ማህበር፥ ድርጅት። (ለምሳሌ የገበሬዎች አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር፥ የእደጥበባት ባለሙያዎች አምራቾች የህብረት ስራ ማህበር፥ የመኖሪያ ቤት የህብረት ስራ ማህበር፥...)።

**ህብስት** ስ 1. ለዝክር፥ ለማህበር፥... የሚጋገር ዳቦ፥ ፀዲቅ። 2. እንደ ድፎ ወፈር ሳይል የተጋገረ ክብ ዳቦ።

**ህብስተ መና** ስ መልኩ ያማረ፥ ጣእሙ የሚጣፍጥና ነጭ የሆነ ክብ ዳቦ።

**ህትመት** "**አተመ**" ስር ተመ.

**ህንፃ** ስ ለመኖሪያም ሆነ ለሌላ ስራ አገልግሎት እንዲሆን ከድንጋይ፥ ከሸክላ፥ ከብረትና ከመሳሰሉት ነገሮች የሚሰራ ፎቅ ያለው ወይም የሌለው ቤት።

**ህንፃ ተቋራጭ** ስ የኮንትራት ውል ተዋውሎ እንደ ህንፃና ድልድይ የመሳሰሉትን የግንባታ ስራዎች የሚሰራ ግለሰብ ወይም ድርጅት።

**ህክምና** ስ ህሙማንን ለማዳን (ለማከም) በሃኪሞች የሚደረግ እርዳታ፥ ክትትል።

**ህዋ** ስ ከምድር ከባቢ አየር ክልል ውጪ የሆነ ባዶ ቦታ።

**ህዋስ** (ብ.ቁ.**ህዋሳት**) ስ 1. ረቂቅ የሆነ አንድ አይነት ተግባር የሚያከናውንና ህይወት ያለው የማንኛውም አካል መሰረተ ነገር። 2. ለአንድ አይነት አላማ በተቋቋመ ማህበር ወይም የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ የሚገኝ፥ የተወሰኑ አባላትን የሚይዝና እንቅስቃሴዎችን የሚያደርግ የድርጅት

አነስተኛ ክፍል::

**ሀውከት "አወከ"** ስር **"ሁከት"**ን ተመ.

**ሀዝባር** ስ ፊደላትን፥ ቃላትን፥ ቁጥሮችን ፥...ለያይቶ፥ ከፋፍሎ፥ ከልሎ ለማስቀመጥ የሚያገለግል ወደቀኝ ዘንበል ያለ ቀጥተኛ መስመር(/)::

**ሀዝብ** ስ 1. በተወሰነ መልክአምድራዊ ክልል ውስጥ የሚገኙና በአንድ መንግስት ስር የሚተዳደሩ ጠቅላላ ሰዎች:: 2.የአንድ ብሄር ወይም ብሄረሰብ፥ጎሳ፥... አባል የሆኑ ሰዎች:: 3. በአንድ አካባቢ በብዛት የሚታዩ፥ የሚገኙ ወይም የሚኖሩ ሰዎች ባጠቃላይ:: 4. በመንግስት ስልጣን ውስጥ የሌሉ ተራ ሰዎች::

**ሀዝብ አዳም** ስ (ተራ አነ.) ሰው ሁሉ::

**ሀዝበ ክርስቲያን** ስ የክርስትና እምነት ተከታዮች፥ ምእመናን::

**[የ] ሀዝብ ቆጠራ** ስ የአንድን ሃገር ሀዝብ ብዛት ለማወቅ የሚደረግ የሰዎች ምዝገባ::

**ሀዝባዊ** ቅ የሀዝብ ወይም የሀዝብ ወገን::

**ሀዝባዊ መንግስት** ስ ለሀዝብ ጥቅም የቆመ፥ መሪዎቹ በሀዝብ እየተመረጡ ሀዝብን የሚያገለግሉበት መንግስት::

**ሀዝባዊ ሰራዊት** ስ የመደበኛ ሰራዊት አባል ያልሆነ፥ ከሀዝብ ተውጣጥቶ የጦር ትምህርት የተከታተለና አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ወታደራዊ አገልግሎት የሚሰጥ ሃይል::

**ሀዝባዊ አመፅ** ስ የተጨቆነ ሀዝብ በጨቋኝ ገገር መደብ ላይ የሚያካሂደው የአልገዛም ባይነት ትግል::

**ሀዝባዊ ድርጅት** ስ በሙያ፥ በስራ፥ በፆታ፥ በእድሜ፥ በአካባቢ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ማህበራዊ ግንኙነት ባላቸው ሰዎች የሚመሰረት ማህበር::

**ሀያው** ቅ 1. በሀይወት ያለ:: 2. ዘላለማዊ::

**ሀይወት** ስ 1. ለመራባት፥ ለማደግ፥ ለመንቀሳቀስ የሚያስችል ሃይል፤ ነፍስ:: 2. የሰው ነፍስ:: *በአደጋው ብዙ ሀይወት ጠፋ::* 3.እድሜ፥ የኑሮ ዘመን:: *በሀይወቴ እንደዚሀ ያለ ነገር አላየሁም::* 4- የአኗኗር ሁኔታ:: *ሀይወቱን በገዛ እጁ አበላሸ::*

**ሀይወቱን ሰጠ** ራሱን መስዋእት አደረገ::

**ለ__ ሀይወቱን ሰጠ** ለ____ ጊዜውን፥ ጉልበቱን ወዘተ. አዋለ::

**ሀይወቱን አጠፋ** ራሱን ገደለ::

**የሀይወት ታሪክ** ስ አንድ ሰው በሀይወቱ ዘመን ውስጥ ያለፈበት የኑሮ ሁኔታ፥ የፈፀመው ድርጊትና ያጋጠመው ነገር ዝርዝር::

**የሀይወት ዋስትና** ስ የሀይወት መድን፤ የሞት አደጋ በሚደርስበት ጊዜ በውሉ መሰረት ክፍያ እንዲደረግ የሚያስችል፥ ከመድን ድርጅት ጋር ግለሰብ ወይም ድርጅት የሚያደርገው ስምምነት::

**ሀዳር** ስ ከጥቅምት ቀጥሎ የሚመጣ የአመቱ ሶስተኛ ወር::

**ሀዳር ታጠነ** እንደወረርሽኝ ያሉ በሽታዎችን ለማጥፋት ሲባል በየአመቱ ሀዳር 12 ቀን በየቀየው ጭስ ተጨሰ::

**ሀዳግ** ስ በአንድ ፅሁፍ ራስጌና ግርጌ እንዲሁም ጎንና ጎን ላይ የሚገኝ የማይፃፍበት ባዶ ቦታ::

**ሀግ (ብ.ቁ.ሀግጋት)** ስ 1.የመንግስት ጥበቃ የሚደረግለትና ሲጣስ ቅጣትን የሚያስከትል የማሀበራዊ ግንኙነት መመሪያ፥ ደንብ:: 2. አንድ ድርጊት የሚካሄድበት ስርአት፥ደንብ:: *የእግር ኳስ ጨዋታ ሀግ::* 3. ክብረንፅሀና፥ ድንግልና::

**ሀግ አደረሰ** ክብረንፅሀናዋን ገሰሰ (በሚስትነት ያገባትን ልጃገረድ)::

**ሀግ ወጣ** ደንብ ወይም ስርአት ወጣ፥ ታወጀ፥ ተደነገገ::

**ሀግ አወጣ** ደንብ ወይም ስርአት አወጣ፤ ደነገገ፥ አወጀ::

**ሀግ አውጪ** ስ ያንድን ሃገር ሀግ ለማውጣት ስልጣን የተሰጠው የመንግስት አካል::

**ሀግ ይጠብቅሀ /ያግድሀ** ስነስርአት ይኑርሀ፥ ለሀግ ተገዛ::

**ሀግ ገባ** 1 ቃል ኪዳን አሰረ፤ አጨ:: 2- በሀግ አገባ::

**ሀግ ጣሰ** ደንብ ወይም ስርአት ተላለፈ::

**ሀግ ፊት ቆመ** በሰራው ጥፋት ተከሰሰ፥ ለፍርድ ቀረበ::

**ሀጓን ወሰደ** ክብረ ንፅሀናዋን ገሰሰ::

**በሀግ አምላክ** አድራጎትሀ ትክክል አይደለምና ሀግ ያግድሀ፥ የምታድርገውን አቁም ለማለት የሚነገር ቃል::

**በሀግ አገባ** በሀጋዊ መንገድ ልጃገረድ አገባ::

**ሀገ መንግስት** ስ አንድ ሃገር የምትተዳደርበትና ሀዝቦቿ ለሚያከናውኗቸው ተግባሮች ሁሉ መርሀ የሚሆናቸው የሁሉም የበላይ የሆነ ሀግ::

**ሀገ ወጥ** ቅ 1. በሀግ ያልተፈቀደ:: 2. ስነስርአት የሌለው፥ ሀግ አፍራሽ፤ ወንበዴ::

**ሀግ መምሪያ [ምክር ቤት]** የሀግ ረቂቅ የሚወጣበት የፓርላማ ክፍል::

**ሀግ መወሰኛ [ምክር ቤት]** ስ የሀግ ረቂቅን የማፅደቅ ወይም የመሻር ወይም የመወሰን፥.... መብት ያለው የፓርላማ አካል::

**ሀግ ማመንጪት** ለሚመለከተው ባለስልጣን ቀርበው እንዲመከርባቸውና በሀግ መልክ

እንዲወጡ በማለት መብት በተሰጠው አካል የህግ ሃሳብ ማፍለቅ::

**የህግ ሚስት** ስ 1. ውል በመፈራረም ወይም ባህሉ በሚፈቅደው ስርአትና ደንብ መሰረት የተገባች ሴት፤ የሰማኒያ ሚስት::2. በልጃገረድነቷ የተገባች የመጀመሪያ ሚስት::

**የህግ ረቂቅ (ረቂቅ ህግ)** ስ ህግ ሆኖ እንዲወጣ ለህግ አውጪው ክፍል የሚቀርብ የህግ ንድፍ::

**የህግ ባል** ስ 1. ውል በመፈራረም ወይም ባህሉ በሚፈቅደው ስርአትና ደንብ መሰረት የተገባ ባል:: 2. የመጀመሪያ ባል::

**[የ] ህግ አማካሪ** ስ አንድን ድርጅት ወይም ግለሰብ በሚመለከት ለሚነሳ ክርክር ወይም ጉዳይ የህግ አስተያየት የሚሰጥ፥ የሚያማክር የህግ ባለሙያ::

**የህግ ጠበቃ** "ጠበቀ²" ስር "ጠበቃ"ን ተመ.

**ህጋዊ** ቅ በህግ የተፈቀደ::

**ህጋዊ ሰውነት** ስ ለአንድ ድርጅት ፥ማህበር፥... በመንግስት የሚሰጥ የህልውና ፈቃድ ወይም እውቅና::

**ህጥር** ስ ሽቶ:: *በህጥር በስንቡል መች እጠኑኝ ይላል፥ እመር ያለው ገላ እንዲያው ደርሶ ያምራል::*

**ህፀፅ** ስ እንከን፥ ጉድለት::

**ህፃን (ብ.ቁ.ህፃናት)** ስ 1. እድሜው እስከ አምስት አመት አካባቢ የሚደርስ ልጅ፤ ጨቅላ:: 2. (ዘይ.) ከእድሜው ጋር ሲነፃፀር አስተሳሰቡ ያልበሰለ፥ ጨቅላ የሆነ::

**ህፈረት "አፈረ" ስር "እፍረት"ን ተመ.**

**ሆ¹** የ "ህ" ፊደል ሳብእ ዘር::

**ሆ²** በቡሄ በሉ ጭፈራ ላይ በሆታ ተቀባዮች የሚባል:: ለምሳሌ ቡሄ በሉ ሆ! ልጆች ሁሉ ሆ!...::

**ሆታ** ስ በህብረት የሚካሄድ የጭፈራ ዘፈን::

**ሆሆታ** ስ ሁካታ፥ ግርግር፥ የብዙ ሰዎች ድምፅ::

**ሆ አለ** ግ 1. ዘፈነ፥ ጨፈረ:: 2. ንብን ለማስፈር ሆ የሚል ድምፅ አሰማ::

**ሆ ብሎ ተነሳ** በወኔና በአንድነት ተነሳ::

**ሆሄ (ብ.ቁ ሆህያት)** ስ ከግእዝ እስከ ሳብዕ (ለምሳሌ ከ ሀ-ሆ ወይም ከ ሀ-ፐ ) ያለው የፊደላት ስምና መልክ ወይም ቅርፅ::

**ሆሆ (ሆሆይ)** ቃ.አ. የእንክሮ፥ የማድነቅ፥ የማጋነን ቃል ወይም አነጋገር:: *ሆሆይ! እውነት ሰው ጨረቃ ላይ ወጣ?*

**ሆመር "ሮቃ"** ን ተመ.

**ሆመጠጠ "ኮመጠጠ"** ን ተመ.

**ሆማ " አሆማ"** ን ተመ.

**ሆምጣጣ "ኮመጠጠ"** ስር **"ኮምጣጣ"** ን ተመ.

**ሆረጠ (ኮረጠ)** ግ ኮስተር፥ ክሽን ብሎ ጣፈጠ (ቀይ ወጥ)::

**ሆሳእና** ስ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም በአህያ ተቀምጦ ሲገባ ሰዎች ዘንባባ ይዘው የተቀበሉበትን እለት በማስታወስ የሚከበር፤ ከፋሲካ በፊት በሚገኘው እሁድ የሚውል በአል::

**ሆስቴል** ስ የመኖሪያ ወይም የመኖሪያና የምግብ አገልግሎት የሚሰጥ፥ ብዙ ክፍሎች ያሉትና ብዙ ሰዎችን ሊያስተናግድ የሚችል የኪራይ ቤት::

**ሆስቴስ** ስ በአውሮፕላን ውስጥ የምታገለግል የሴት አስተናጋጅ::

**ሆስፒታል** ስ በይዘቱ ከክሊኒክና ከጤና ጣቢያ የሚሰፋ፥ በተመላላሽነት ወይም በሆስፒታሉ ተኝተው የሚታከሙ ህሙማንን እየተቀበለ አስፈላጊውን የጤና አገልግሎት የሚሰጥ የህክምና ተቋም::

**ሆቴል** ስ የመኝታና የምግብ አገልግሎት የሚሰጥ የንግድ ድርጅት::

**ሆነ** ግ 1. ተፈፀመ፥ ተደረገ፥ ተከናወነ:: *ያልኩት ሆነ* :: 2. በጀ፥ ረባ፥ ጠቀመ፥ ፈየደ:: *ሲጃራ የምታጨሰው ምን ይሆነኝ ብለህ ነው?* 3. ቀና፤ ተሳካ፥ ተሟላ:: 4. ተስማማ:: *አገሩ ሆኖታል::* 5. *ልክ መጣ፥ በቃ:: ልብሱ ሆኖኛል::* 6. አንድን አይነት፥ መጠን፥ መልክ፥ ባህርይ፤ ግብር፥ ስራ ያዘ::*ቀይ ሆነ/ትልቅ ሆነ / ደግ ሆነ /አስተማሪ ሆነ፥...::* 7. ተቀመጠ፥ ኖረ:: *ከአክስቱ ዘንድ ሆኖ ትምህርቱን ይማራል::* 8. በአካል ተገኘ:: ጉዳዩን በመካከላችን ሆኖ ገለፀልን::

**-ም ሆነ-** 1.ወይም:: *እሱም ሆነ እሷ መልእክቱን ሊያደርሱ ይችላሉ::* 2. እና፥ ሁሉም:: *እሱም ሆነ እሷ መማር አለባቸው::*

**ሆነ ብሎ** (ሆነኝ ብሎ፥ ሆን ብሎ፥ ይሆነኝ ብሎ) አውቆ፤ አስቀድሞ አስቦበት:: *ሆነ ብሎ ነው ይህን ያደረገው::*

**ሆኖም** መፃ. ግን፥ ነገር ግን::

**ለመሆኑ** እንዲያው ለነገሩ፥ የሆነውስ ሆነና::

**ለማይሆን ነገር /ጉዳይ** ለማይረባ ወይም ለማይጠቅም ነገር (ጉዳይ) *ለማይሆን ነገር ገንዘብህን አታባክን::*

**ሲሆን [ ሲሆን]** 1. ቢቻል:: *ሲሆን አንተ ራስህ እንድትመጣ::* 2. እንደእውነቱ ከሆነ:: *ሲሆን ወላጆችህን መርዳት ነበረብህ::*

**ስለሆነ [ ም]** መፃ. ስለዚህ፥ በዚህ ምክንያት::

**በሆነ ባልሆነ[ው]** በሚረባ በማይረባው፤ በትልቁ በትንሹ:: *በሆነ ባልሆነው አትጨቃጨቁ::*

**በመሆኑ [ ም]** መፃ. በዚህ ምክንያት፥ በዚህ የተነሳ።

**ቢሆን** 1. ቢያሻ፥ ቢያስፈልግ። *ልቅሶ የሚደርስ ቢሆን እነግራችሁ ነበር።* 2. ሲባል። *ላንተ ቢሆን ይሰጡህ ነበር።*

**ቢሆንም (ቢሆንም ቅሉ፥ ቢሆንም እንኳ)** ያም ቢባል፥ ያም ቢደረግ። *ላልሰጥህም ሊሉኝ ነበር፤ ቢሆንም መጠየቄ አይቀርም።*

**ቢሆንም ባይሆንም** ለሁሉም፥ ለማንኛውም፤ ቢሳካም ባይሳካም።

**ባይሆን** ሌላው ቢቀር። *ዝም ብለህ ኣትቀር፤ ባይሆን ስልክ ደውል።*

**ኣይሆንም** እምቢ ኣይቻልም፥ ኣይደረግም።

**እንደሆነ ይሁን** ባወጣ ያውጣው፥ እንዳሻው ይሁን።

**እንዳልሆነ ሆነ** እንዳልነበረ ሆነ፥ ተበላሸ፥ ተጎሳቀለ።

**ከመሆኑም በላይ** ከዚህም ሌላ፤ በተጨማሪ።

**የሆኖ ሆኖ** 1. ለማንኛውም። *ስራውን ተከታተልልኝ፤ የሆና ሆና እኔም እመጣለሁ።* 2. ነገር ግን። *መድሃኒት እየወሰደ ነው፤ የሆና ሆና ኣልተሻለውም።*

**የሆነ ነገር** እንዲገለጥ ያልተፈለገ ወይም ያልታወቀ ኣንዳች ነገር። *ስለ እሱ የሆነ ነገር ሰምቻለሁ/ በእጁ የሆነ ነገር ይዟል።*

**የሆነውን** 1. የተገኘውን። *ከቋም ሳጥን ውስጥ የሆነውን ልብስ ስጠኝ።* 2. የነካውን፥ የኣጋጠመውን። *የሆነውን ኣላውቅም ተከዟል።*

**የሆነው ይሁን** 1. የፈለገው ይሁን፥ የመጣው ይምጣ። **የሆነው ይሁን** መሄዴ ኣይቀርም። 2. የተገኘውን። *የሆነው ይሁን ብቻ ግዛልኝ።*

**የሚሆኑ** የሚደርሱ፥ የሚያህሉ። *ሃያ የሚሆኑ....።*

**የማይሆን ነገር** የማይታመን፥ የማይመስል ነገር።

**ያም ሆነ ይህ** ለማንኛውም፥ በማንኛውም መንገድ።

**ይሁን** እሺ።

**ይሁንና** መፃ. ነገር ግን፥ ሆኖም።

**ይሁን እንጂ** መፃ. ይሁንና፥ ነገር ግን።

**ይሆናል** ሳይሆን ኣይቀርም። *ገንዘቡን የወሰደው እሱ ይሆናል።*

**ሁነኛ** ቅ 1.ቋም ነገረኛ፥ ታማኝ። 2. ኣይነተኛ፥ ተስማሚ፥ ጠቃሚ።

**ሁኔታ (ሁናቴ)** ስ 1. ኣኳኋን፥ ኣዝማሚያ። *የጊዜው ሁኔታ ኣላማረኝም።* 2. ሁለንተና፥ ነገረ ስራ። *ሁኔታዋ እናቷን ትመስላለች።* 3. ነገር፥ ጉዳይ፥ ድርጊት። *ጠቅላላ ሁኔታውን ግለፅልኝ።* 4.ምክንያት። *በምን ሁኔታ ነው ትምህርቱን ያቋረጠው።* 5. ይዞታ። *መጀመሪያ የቤቱን ሁኔታ ልየውና ስለ ኪራዩ እንነጋገራለን።*

**ተሣሣነ** ግ ተስማማ፥ ተግባባ። *እኔና እሱ ኣልተሣሣንም።*

**ኣኳሿነ** ግ ኣስማማ ፥ ኣግባባ።

**ኣኳሿን** ስ ኣዝማሚያ፥ ኣስተያየት፥ ኣመለካከት፥ ኣደራረግ።

**ሆናና** ቅ ሞኝ፥ ቂል።

**ሆያ ሆዬ** ስ በቡሄ ፥ በዘመን መለወጫና በመስቀል በኣል ጊዜ ወንዶች ልጆች የሚዘፍኑት የጭፈራ ዘፈን።

**ሆይ**[1] አክብሮትን፥ ፍቅርን፥.... ለመግለፅ ከስም ጋር እየተጣመረ የሚነገር ቃል። *ኣባታችን ሆይ/ ወንድሜ ሆይ፥ ...።*

**ሆይ**[2]

**ሆይ ሆይ ኣለ** ግ 1. ኣበረታታ፥ በል በል ኣለ፥ ገፋፋ። 2. ኣዋከበ፥ ኣቻኮለ። 3. ኣሸቃበጠ፥ ኣጫፈረ። *ከመጣው ሁሉ ጋር ሆይ ሆይ ማለት ይወዳል።*

**ሆደደ**[1] ግ በሰፊው ኣረሰ።

**ሁዳድ (ኩዳድ)** ስ ገባሮች እየተገደዱ የሚያርሱት የንጉስ፥ የመልከኛ፥... ይዞታ የነበረ ሰፊ የእርሻ መሬት።

**የሁዳድ ፈሪ** ስ ሁዳድን ሳያርስ በቀረ ገበሬ ላይ የሚጣል ቅጣት።

**ሁዳደኛ** ስ ሁዳድ ኣራሽ።

**ሆዳጅ** ስ ገባር፥ ጭሰኛ።

**ተሆደደ** ግ ታረሰ፥ ተዘራ፥ ታረመ፥ ታጨደ፥ ተወቃ (የሁዳድ እርሻ) ።

**ሆደደ**[2] ግ ሁዳዴን ፆመ።

**ሁዳዴ** በፊደል ተራው ተመ.

**ሆድ** ስ እንደ ጨጓራ፥ ጉበት፥ ኩላሊት፥ ኣንጀት፥..... የመሳሰሉት የሚገኙበት የሰውነት ክፍል(ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)።

**ሆደ መርዝ** ቅ ክፉ፤ ቂመኛ።

**ሆዱ መረዘ** ቂም ያዘ፤ ጥላቻ ኣደረበት።

**ሆዱ ራሰ /ቅቤ ጠጣ** የልቡ ደረሰ፥ የፈለገው ነገር ስለሆነለት ተደሰተ።

**ሆዱ/ልቡ ሻከረ** ተቀየመ፤ ቅር ተሰኘ።

**ሆዱ/ኣንጀቱ ቆረጠ** እርግፍ ኣድርጎ፥ ጨከኖ ተወ።

**ሆዱ/ኣንጀቱ ቡጭ ቡጭ ኣለ** የማዘን፥ የመራራት ስሜት ተሰማው።

**ሆዱ ኣረረ/ቆሰለ/ተቃጠለ** ተናደደ።

**ሆዱ/ልቡ/ አንጀቱ ነፈረ** በጣም ተናደደ፥ ተበሳጨ።

**ሆዱ አይታወቅም/አይገኝም** አመሉ፥ ጠባዩ፥ ሃሳቡ አይታወቅም።

**ሆዱ/ልቡ አይጠራም** ቂም ይይዛል፥ ልቡ ንፁህ አይደለም።

**ሆዱ ጎሸ** ተቀየመ።

**ሆዱ ጎደለ** ተራበ።

**ሆዱ/ ልቡ ጠራ** ከተንኮል ወይም ከቂም በቀል ራቀ፥ ልበ ንፁህ ሆነ።

**ሆዱ ጠቡቷል** ከመወፈር የተነሳ ምግብ አይደፍርም፥ አይበላም።

**ሆዱን/ ልቡን ሰጠ** ያለውን ሃሳብ፥ ምስጢር ገለፀ፥ አካፈለ።

**ሆዱን/ልቡን ቆረቆረው** ከነከነው፤ ቅር አለው።

**ሆዱን ቆረጠው** ቆረቆረው፤ ከነከነው።

**ሆዱን በላው** 1. አሳዘነው። 2. ከነከነው፣ ቆረቆረው።

**ሆዱን ባር ባር አለው** ፍርሃት ፍርሃት አለው።

**ሆዴ** ወዳጄ፤ አንጀቴ፥... ለማለት የሚነገር ቃል።

**ሆዴን ጋጠኝ** ራበኝ፤ ሞረሞረኝ።

**ሆድ ለቀቀበት** አልጠግብ አለ፤ ብዙ ምግብ አስፈለገው።

**ሆድ ባሰው** በትንሽ ነገር ተከፋ፤ አዘነ።

**ሆድ የለውም** ብዙ አይበላም፥ በትንሽ ምግብ ይጠግባል።

**ሆድ ይፍጀው** ሆድ ይቻለው፥ ስለሁኔታው መናገር አያስፈልግም።

**ሆድና ጀርባ ሆኑ** ተቃቃሩ፤ ተቀያየሙ።

**በሆዱ/በልቡ አሰበ** ሳይናገር በዝምታ አሰበ፥ አሰላሰለ።

**በሆዱ አነበበ** ድምፅ ሳያሰማ በዝምታ አነበበ።

**የሆዱን አውጥቶ ተናገረ** ያሰበውን፥ ምስጢሩን አወጣ ወይም ተናገረ።

**ሆደ /ልበ ሰፊ ቅ** ቻይ፥ ታጋሽ።

**ሆደ ቡቡ ቅ** 1. አዛኝ፥ ርህሩህ። 2. ሆደ ባሻ።

**ሆደ ባሻ ቅ** ለማዘን፥ ለማልቀስ ትንሽ ምክንያት የሚበቃው።

**ሆደ /ልበ ገር ቅ** ርህሩህ፥ የዋህ፤ ገራገር።

**ሆዱ/ልቡ አይጠራ ቅ** ቂመኛ፥ በቀለኛ።

**ሆዱ ዘመዱ ቅ** ብቻውን የሚበላ፥ ለሌላ የማያካፍል፥ ንፉግ።

**ሆድ ሆዱን ስ** ስትጮህ "ሆድ ሆዱን" ያለች የምትመስልና ከሆዷ ዘርጠጥ ያለች ርግብ መሳይ የቆላ ወፍ።

**ሆድ ቁርጠት ስ** የሆድ ውስጥ ህመም።

**ሆድ አምላኩ ቅ** ለሆዱ የሚገዛ፥ ስግብግብ።

**ሆድ እቃ ስ** በሆድ ውስጥ የሚገኙ እንደ ጨጓራ፥ ጉበት፥ አንጀት፥... የመሳሰሉ ብልቶች።

**ሆድ ዝማ ስ** የተቅማጥ በሽታ።

**ሆድ ድርቀት ስ** በተገቢው መጠን፥ ጊዜና ሁኔታ አይነምድር (ሰገራ) ከሆድ እንዳይወገድ ችግር የሚያስከትል የሆድ በሽታ።

**ሆዳም ቅ** ጠገብኩን የማያውቅ፤ ስግብግብ።

**ሆጃ ስ** በሻይ መልክ ተፈልቶ የሚጠጣ ቁጢ ወይም የቡና ገለፈት።

**ሆጭ(ሆጨጭ)**

**ሆጭ(ሆጨጭ) አለ ግ** የጠርሙስ ስብርባሪዎች፥ ሳንቲሞች የመሳሰሉ ነገሮች ሲወድቁ ወይም ሲጋጩ የሚሰጡትን አይነት ድምፅ ሰጠ፥ አሰማ።

**ሆጭ(ሆጨጭ) አደረገ ግ** 1. አቀረበ፥ ዘረገፈ፥ ሰጠ (ጠገራ ብርን)። 2. ሰበረ፥ አረገፈ(መስተዋትን)።

**ሂ** "ሀ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር።

**ሂላ** ተው.ግ 1. ቆየት ብሎ ወይም ወደፊት የሚመጣ ሰአት፥ ጊዜ፥ ወቅት፥ ወዘተ. *አሁን ልሂድና ሂላ እመለሳለሁ።* 2. በመጨረሻ። *በሂላ ከሚቆጭህ አሁኑኑ ጥንቃቄ አድርግ።* 3. ከወደ ጀርባ ያለ ቦታ። *ከእኔ ሂላ ተቀምጦ ነበር።* 4 ታዲያ፥ እንግዲያው። *የማትሰራ ከሆነ ሂላ ለምን መጣህ?*

**ሂለኛው ቅ** 1.በስተጀርባ በኩል ያለ። 2.ዘግይቶ የመጣ፤ ከአንድ ነገር ቀጥሎ የሆነ። *የሂለኛው ስራ አድካሚ ነበር።*

**ሂላቀር ቅ** 1. ከጊዜው ሁኔታ ጋር የማይራመድ፥ ጊዜው ያለፈበት። 2. ያልሰለጠነ።

**የሂሊት** ተው.ግ ወደ ጀርባ፥ ወደ ሂላ አቅጣጫ። *ልጁ የሂሊት ሲሄድ ወደቀ።*

**የሂላ ሂላ** ተው.ግ ቆይቶ ቆይቶ፥ በመጨረሻ። *የሂላ ሂላ እውነት ማሸነፉ አይቀርም።*

# ለ

**ለ** ከ"ሀ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)::

**ለ___** 1. ቀጥተኛ ያልሆነ (ኢ.ር.ቱ.እ) ተሳቢ ላይ የሚያርፍና ድርጊት ተቀባዩን የሚያመለክት ምእላድ:: *መፅሃፉን ለሰውየው ሰጠሁት*::2.በ___ ላይ፣ በ_____ውስጥ:: *ገደል ለገደል አትሂድ*:: 3. በየ_______::*አገር ለአገር ሲዞር ከርሞ መጣ*::4_ እና ______÷ _____ከ______ጋር:: *አሀያ ለአሀያ ቢራገጥ ጥርስ አይባበርም*:: 5. በ_______ ምክንያት፣ ለ___ሲል:: *ለትምህርት ሄደ /ለሃገሩ ተሰዋ*::6.አንድን ነገር ለማድረግ÷ ለመስራት÷...:: *ለመፃፍ ወረቀት ያስፈልጋል*:: 7. ሲካፈል:: *አራት ለሁለት ሁለት ጊዜ ይደርሳል*:: 8. ሁለት ነገሮች የሚገኙበትን ሁኔታ÷ አቀማመጥ፣ ውጤት÷... በማነፃፀር ለመግለፅ የሚያገለግል ምእላድ:: *ልብ ለልብ ተዋውቀዋል /ጎን ለጎን ተቀምጠዋል /ተጋጣሚዎቹ ሁለት ለአንድ ተለያዩ*:: 9. ጊዜን ከሚጠቁሙ ቃላት ጋር እየተጣመረ የጊዜውን ርዝመት፣ መጠን÷ ሁኔታ፣... ለመግለፅ የሚያገለግል:: *ለነገ÷ ለጊዜው፣ ለመጀመሪያ ጊዜ÷ ለጥቂት ጊዜ÷ ...*::

**ለሃጭ** ስ እየተጎተተ÷ እየተዝረበረበ ከአፍ ውስጥ የሚወጣ ምራቅ፣ ልጋግ::

**ለሃጫም** ቅ (ስድብ) 1. ሲናገር÷ ሲበላ÷... ምራቁ የሚዝረበረብ:: 2. (ዘይ.) ቂላቂል::

**ለሆሳስ**

**በለሆሳስ** ተው.ግ. በሹክሹክታ:: *በለሆሳስ ተናገረ*::

**ለሆቴ** ስ ስለት ለማውጣት እንደሞረድ የሚያገለግል ድንጋይ፣ መሳል::

**ለመለመ[1]** ግ 1. ቅጠል አወጣ÷ አቆጠቆጠ÷ አጀፈጀፈ÷ ጨበጨበ:: 2. አረንጓዴ ሆነ÷ ልምላሜ ተላበሰ:: *አካባቢው ለምልሟል*::

**ለምለም** ቅ አረንጓዴ÷ ርጥብ÷ ሊጋ:: *ለምለም ሳር*::

**ለምለም እንጀራ** ስ ወጥ ወይም ማባያ የሌለው እንጀራ::

**ለምለም ጆሮ** ስ ወደታች ያለውና ጉትቻ የሚንጠለጠልበት የጆሮ ክፍል::

**ልምላሜ** ስ አረንጓዴነት፣ ርጥብ÷ ሊጋ÷ ለምለም መሆን::

**አለመለመ** ግ ለመለመ::

**ለመለመ[2]** ግ የዛፍን÷ የአትክልትን ቅጠል ወይም ቅርንጫፍ በብዛት ቆረጠ÷ ቀጠፈ÷ መለመለ::

**ለመመ** ግ አደፈ፤ ንፅህና ካለመጠበቅ የተነሳ ቆሸሸ(ጥርስ÷ ድድ)::

**ልማም** ስ 1.ቢጫነት ያለውና ጥርስ ላይ የሚታይ ቆሻሻ÷ እድፍ:: 2.እርሻ በሚታረስበት ጊዜ በማረሻ ላይ የሚለደፍ ጭቃ::

**ለመሰሰ** ግ አጋደመ÷ አስተኛ÷ ለሽ አደረገ÷ ለመሸሸ (ሳርን÷ ሰብልን÷...)::

**ተለመሰሰ** ግ ተኛ÷ ተለሸለሸ::

**ለመሸሸ** ስ አጋደመ፣ አስተኛ÷ ለሽ አደረገ÷ ለመሰሰ (ሳርን÷ ሰብልን÷...)

**ለመሸቀ** ግ ራሰ÷ ረጠበ::

**ለመነ** ግ 1.ችሮታ÷ እርዳታ አድርጉልኝ አለ፤ ምፅዋት ጠየቀ:: 2. ፀለየ÷ ተማጠነ:: 3. (አንድን ነገር) እባክህ አድርግ ወይም አታድርግ ብሎ ጠየቀ፣ አግባባ::

**ለማኝ** ስ መንገድ ዳር ተቀምጦ ወይም ከቤት ወደ ቤት በመዘዋወር ጉዳቱን አስተዛዝኖ እየተናገረ ምፅዋት የሚጠይቅ ድሃ፣ የኔ ቢጤ::

**ለማኝ ሳያራ** በጠዋት÷ በማለዳ:: *ለማኝ ሳያራ ተነስቼ ስራዬን ጀመርኩ*::

**ልመና** ስ 1. ምልጃ÷ ፀሎት:: 2. ችሮታ÷ እርዳታ፣ ምፅዋት ጥየቃ::

**ልመና አቀረበ** ለመነ::

**የልመና እህል** ስ የተለያዩ የእህል አይነቶች ድብልቅ፣ ውጥንቅጥ እህል::

**ተለመነ** ግ 1. ተጠየቀ÷ እባክህ ተባለ:: 2. የተጠየቀውን አደረገ÷ ፈፀመ÷ ፈቃድ ሞላ:: *መድሃኔአለም ተለምኖኛል*::

**ተለማኝ** ቅ ርህሩህ÷ እሽ ባይ:: *አምላካችን እግዚአብሔር ተለማኝ ነው*::

**ተለማመነ** ግ ዛርን ወይም ውቃቢን ለመነ÷ ተለማመጠ::

**መለማመኛ** ስ ለተለማኙ ዛር ወይም ውቃቢ የሚቀርብ ስጦታ፣ ምስ::

**አለመነ** ግ ለጠየቀ ወይም ለለመነ ሰው ሰጠ÷ ቸረ::

**አስለመነ** ግ ደጅ አስጠና÷ ብዙ ተለመነ::

**ለመከከ** ግ ቀባ÷ ላከከ::

***ለመዘመዘ**

**ተልመዘመዘ** ግ ታሸ÷ ተፍተለተለ::

**አልመዘመዘ** ግ አሸ÷ አፍተለተለ::

**ለመዘገ(መዘለገ)** ግ በሃይል አጥብቆ ቆነጠጠ::

**ለመደ** ግ 1. አብሮ ከመቆየት ወይም ከማዘውተር የተነሳ የአንድን ነገር ጠባይ፣ ሁኔታ፥ አሰራር፥...አወቀ:: *ስራውን ለመደው::* 2. አንድን ነገር መስራት፥ ማድረግ ተማረ፥ ሰለጠነ:: *መኪና መንዳት ለመደ::* 3. ከአካባቢው ጋር ተስማማ፥ ተዋወቀ:: *አገሩን ለመደው::* 4. አዘውተረ፥ ደጋገመ:: *የስራ ሰአት ማሳለፍ ለመደ::* 5. አመል አወጣ፥ ሱሰኛ ሆነ:: *መጠጥ ለመደ::* 6. ለዘበ፥ ገራም ሆነ:: *ላሚቱ እያደር ለመደች::*

**እንዳይለምድህ** ሁለተኛ፥ ዳግመኛ እንዳታደርግ::

**ለማዳ(ለማድ)** ቅ 1. ገራም፣ በተፈጥሮ የነበረውን የአውሬነት፥ የበርጋኒነት ባህርይውን የተወ:: 2. በቀላሉ የሚለምድ::

**ለማጅ** ቅ 1. አንድን ነገር በመስራት ወይም በማድረግ ለማወቅ በመማር ላይ ያለ:: 2.አንድን ነገር መስራት፥ ማድረግ፥ ...ጠንቅቆ የማያውቅ፣ ጀማሪ::

**ልማድ** ስ 1. ዘወትር በተደጋጋሚ የሚደረግ፥ የሚሰራ:: *ስፖርት የመስራት ልማድ አለኝ::* 2. ሱስ:: *የመጠጥ ልማድ አለበት::* 3. ባህርይ፥ አመል:: *መሳደብ ልማዱ ነው::* 4. ዘወትር፥ በተደጋጋሚ በመሰራቱ ወይም በመደረጉ እንደ ደንብ፥ እንደ ህግ የተወሰደ:: *በጠዋት መነሳቱን እንደ ልማድ ይዞታል::* 5. አንድ ማህበረሰብ የሚከተለው፥ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ የመጣ ወግ፥ ስርአት፥ ባህል::

**በዘልማድ** ተው.ግ. በተለምዶ::

**እንደልማዱ** ከዚህ ቀደም ሲያደርግ እነደነበረው::

**ልማደኛ** ቅ (ብዙውን ጊዜ መጥፎ ድርጊትን) በተደጋጋሚ የሚፈፅም፥ የሚያደርግ::

**ልማዳዊ** ቅ የተለመደ፥ ያልተለወጠ፣ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ:: *ልማዳዊ የአስተራረስ ዘዴ::*

**ልምድ** ስ 1. ከማየት፥ ከመስማት፥ ከማድረግ፥... የሚገኝ እውቀት፣ ገጠመኝ:: *ካለፈው ስራ ጥሩ ልምድ አገኘ::* 2.በማዘውተር የሚፈፀም ድርጊት:: *ከእንቅልፌ ጠዋት የመንቃት ልምድ አለኝ::*

**የልምድ ልውውጥ** ስ በስራ ሂደት ውስጥ የተገኘን እውቀት ለሌላ ማካፈልና በአንፃሩም ሌላው ካገኘው ልምድ መማር::

**መልመጃ** ስ እውቀትን፥ ብቃትን፥ ችሎታን ለማየት የሚሰጥ የሙከራ ጥያቄ::

**ልምምድ** ስ የችሎታ ብቃትን ለማግኘት በተደጋጋሚ የሚደረግ ክንውን::

**ተለመደ** ግ በመዘውተሩ ወይም በመደጋገሙ የተነሳ አዲስ ወይም እንግዳ መሆኑ ቀረ::

**አይለመድም** 1.ሊለመድ ባለመቻሉ ሁልጊዜ አዲስ፥ እንግዳ ነው:: *ምት አይለመድም/ስራው ከባድ ነው፥ በቀላሉ አይለመድም::* 2.ሁለተኛ አይደገምም:: *እንዲህ አይነት ጥፋት አይለመደኝም::*

**እንደተለመደው** ከዚህ በፊት እንደሚደረገው እንደሚሰራው፥ እንደሚታወቀው::

**በተለምዶ** ተው.ግ. በነበረው፣በቆየው ልማድ፥ ወይም ስርአት መሰረት ፣ በዘልማድ:: *ጊዜ የፈጠረው ሳይሆን በተለምዶ ሲደረግ የቆየ ነው::*

**ተለማመደ** ግ 1. አንድን ነገር በጥራት ወይም በብቃት የማከናወን ችሎታ ለማግኘት አስፈላጊውን ልምምድ አደረገ:: *መኪና መንዳት እየተለማመድኩ ነው::* 2. አንድን ነገር በጥራት ወይም በብቃት የማከናወን ችሎታ አገኘ:: *ቢስክሌት መንዳት ተለማምዷል::*

**መለማመጃ** ስ ሙከራ ማድረጊያ ጊዜ፥ ስፍራ፥ እቃ::

**ተለማማጅ** ቅ በልምምድ ላይ ያለ (ሰው)::

**ተላመደ** ግ 1. ተቀራረበ፥ ተግባባ:: *አብረውት ከሚሰሩት ሰዎች ጋር ተላመደ::* 2.እየቻለ፥ እያወቀ መጣ:: *አዲሱን ስራ ተላመደው::* 3. የ"**ለመደ**"ን ሶስተኛ ፍቺ ተመ.

**አለመደ** ግ ገራም፥ ለማዳ አደረገ::

**አለማመደ** ግ 1. አስተማረ፥ አሰለጠነ፥ አሳወቀ:: *መኪና መንዳት አለማመደ::* 2.አላመደ፥ እንግድነት እንዳይሰማው ከእንግዳው ጋር አብሮ ሆነ::

**አለማማጅ** ስ አሰልጣኝ::

**አላመደ** ግ እንግዳውን ከአካባቢው ጋር አስተዋወቀ፣ አብሮ በመሆን ብቸኝነት እንዳይሰማው አደረገ::

**አስለመደ** ግ 1. አስተማረ፥ አሳወቀ፥ አሰለጠነ:: 2. ሱሰኛ፥ ልማደኛ አደረገ (የሲጋራ፥ የመጠጥ፥...)::

**ለመገገ**[1] ግ ሳበ፥ መጠመጠ፥ ጠባ (ጡትን)::

**ለመገገ**[2] ግ ጎፈነነ፥ ጎመዘዘ::

**ለመጠ**[1] ግ 1. አጎበጠ፣ አስጎነበሰ:: 2. በዱላ መታ፥ ጠለዘ፥ ዠለጠ:: 3. ረግጦ ገዛ:: *አምባገነኑ መሪ ህዝቡን ለምጦ ገዛው::*

**ምን ይለምጥሃል** ምን ይለጥጥሃል፥ ምን ይጀንንሃል፥ ምን ያኮራሃል::

**ለማጣ** ቅ 1. በቀላሉ የሚጎብጥ፥ የሚታጠፍ:: 2. አቅመቢስ፥ ልፍስፍስ:: 3. (ዘይ.) ጠንካራ አቋም የሌለው፥ ባህርየ ደካማ::

**ልምጭ** ስ አርጩሜ፥ ለበቅ::

**ልምጭ አይነካሽ** ስ ጡንቻ ወይም ነብሮ::

**ለመጥማጣ** ቅ 1. ለማጣ:: 2. ተለማማጭ::

**ልምጥምጥ** ዝ.ከ.

**ተለመጠ** ግ ታጠፈ፥ ጎበጠ።

**ተለማመጠ** ግ በትህትና ለመነ፥ አግባባ፥ አባበለ።

**ተለማማጭ** ቅ ከመፍራት፥ አቅም ከማጣት፥... የተነሳ ሌላውን የሚለምን።

**ተልመጠመጠ** ግ 1. ሰውነቱ ረገደ፥ ተብረከረከ፥ አቅም አጣ። 2. የሚታጠፍ አይነት ሆነ፤ ረገብ ረገብ አለ። 3- እየተቅለሰለሰ ለመነ፥ አግባባ፥ አባበለ።

**አለማመጠ** ግ ደጅ አስጠና፥ አሽቀጠቀጠ። *ለማይሆን ነገር ምን አለማመጠው።*

**ለመጠ**[2] ግ እህልን በምጣድ አመሰ፥ ሞቅ ሞቅ አደረገ።

**ለመጠ**[3] ግ ምላጭን በጠፍር ሳለ ወይም ሞረደ።

**ለመጠ**[4] ግ በብዛት ጠጣ። *ጠላውን ሲለምጥ ዋለ።*

***ለመጠ**

**ልሙጥ** ቅ ሸንትራት፥ መስመር፥ ሰንበር፥ ጥልፍ፥ ሽልማት፥ ጌጥ፥ ...የሌለው አንድ ወጥ የሆነ መልክ የያዘ፤ ልስልስ።

**ልሙጥ ሽማ** ስ ጥለት የሌለው ሽማ።

**ልሙጥ ብርሌ** ስ ሽልማት ሸንትራት የሌለው ብርሌ።

**ልሙጥ ወረቀት** ስ መስመር የሌለው ወረቀት።

**ልሙጥ የበቅሎ እቃ** ስ ቆዳው ላይ ሽልማት ወይም ሸንትራት የሌለው የበቅሎ እቃ።

**ልሙጥ ጥለት** ስ ጥበብ ያልሆነ ጥለት

**ልሙጥ ጨርቅ** ስ የሃረግ፤ የአበባ፥... ዲዛይን ያልተሳለበት አንድ መልክ የሆነ ጨርቅ።

**ለመጠጠ**[1] ግ 1. ፈጀ፥ አቃጠለ። 2. ገረፈ፥ ሸነቆጠ።

**ለመጠጠ**[2] ግ ለጥ አደረገ፥ አስተኛ።

**ልምጥጥ አለ** ግ 1. ተኛ፥ ለጥ አለ(ፀጉር)። 2. አይን የሌለው ወይም ልሙጥ ሆነ (እንጀራ)።

**ለመጨቀ** ግ 1. ላቆጠ፥ ሞቀሞቀ። 2.ጨቀየ፥ ጭቃ ሆነ።

**ለመጨጨ** ግ 1. አስተኛ፥ ለሸ አደረገ (ፀጉርን በቅባት)። 2. ተኛ፤ ለሸ አለ (ቅባት የበዛበት ፀጉር)። 3. ሞቀሞቀ፤ ጭምልቅ አለ።

**ለማ** ግ 1. ለመለመ፤ ፀደቀ (ተክል)። 2. ቀና፥ ለመረ፥ በእርሻ ዳበረ (መሬት)። 3. አደገ፤ በለፀገ (በኢኮኖሚ፥ በኢንዱስትሪ፥...)። *አገሩ ለምቷል።* 4. በጀ፥ ጠቀመ። *ከፋም ለማም እሱ ይሻላል።* 5. ነደደ፥ ተቀጣጠለ (እሳት)። 6. ዳበረ፥ ወፈረ። *ሰውነቱ ለምቷል።*

**በመልማት ላይ ያሉ አገሮች** ስ በአፍሪካ፥ በላቲን አሜሪካ፥ በእስያ የሚገኙና ኋላ ቀር ኢኮኖሚያቸውን ለማሳደግ ጥረት በማድረግ ላይ ያሉ አገሮች።

**የለሙ አገሮች** ስ በኢኮኖሚ፥ በቴክኖሎጂ፥... የበለፀጉ ወይም ያደጉ አገሮች።

**ለም** ቅ 1. የቀና፥ ምርታማ (መሬት)። 2. ቢታረስ ጥሩ ምርት ሊሰጥ የሚችል (መሬት)።

**ለም ከጠፍ** ቅ 1. በከፊል የቀና በከፊል ያልቀና (መሬት)። 2. በከፊል ብቻ መልማት የሚችል (መሬት)።

**የለም ጠፍ መሬት** ስ በተፈጥሮው ለም ሆኖ ሳለ ያልታረሰ መሬት።

**ልማት** ስ 1.ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት፥ ብልፅግና፥ ግንባታ። 2. ጥሩ፥ መልካም ተግባር። *ከልማቱ ጥፋቱ።*

**አለማ** ግ 1. (መሬትን፥ አካባቢውን)አርሶ፥ ዘርቶ አበቀለበት። 2. በኢኮኖሚ አሳደገ፥ አዳበረ።

**አልሚ ምግብ** ስ ለአካል ግንባታና ለእድገት የሚበጅ ምግብ።

**ለማኝ "ለመነ"** ስር ተመ.


**ለማዳ "ለመደ"** ስር ተመ.

**ለምለም "ለመለመ**[1]**"**ስር ተመ.

**ለምባዳ "ለንባዳ"** ን ተመ.

**ለምቦጭ "ለንቦጭ"** ን ተመ.

**ለምድ** ስ 1. ከግምጃ ወይም ከሃር ወይም ከተለፋ የአንበሳ ወይም የነብር ወይም የግስላ ቆዳ ተሰፍቶ የተዘጋጀ የቀድሞ የጦር አለቆች የሚለብሱት የማእረግ ልብስ፤ ወይም ከግምጃ፥ ከሃር የተዘጋጀና በበአል ቀን ዲያቆናት የሚለብሱት የቤተክርስቲያን ልብስ። 2. ከበግ ወይም ከፍየል ቆዳ የሚዘጋጅ ገበሬ ወይም እረኛ የሚለብሰው ደበሎ።



**ለምድ**

**ለምድ ለበሰ** ማድረግ የሚገባውን ባለማድረጉ (ለምሳሌ ለቅሶ ባለመድረስ) አፈረ።

**ለምድ አወጣ** ለምድ እንዲሆን አድርጎ የበግ ቆዳን ገፈፈ።

**ለምፅ (ለምጥ)** ስ የቆዳን የተፈጥሮ ቀለም ለውጦ ነጭ የሚያደርግ የቆዳ በሽታ።

**ለምፃም** ቅ ለምፅ ያለበት (ሰው)።

**ለሰለሰ** ግ 1. ተልጎ ወይም ተፍቆ ሻካራነቱን ተወ፤ ለዘበ። 2. ላመ። 3. ተደጋግሞ ታረሰ።

*እርሻው ለሰለሰ::* 4.ሃይሉን፥ ኮስታራነቱን ቀነሰ:: *ጠላው ለሰለሰ::* 5. ሃይለኛነቱን ተወ፥ ገራም ሆነ (ለጠባይ)::

**ለስላሳ** ቅ 1. የማይሻክር፥ ልዝብ:: 2. ሃይል የሌለው፥ የማያሰክር የአልኮል መጠጥ::

**ለስላሳ [መጠጥ]** አልኮልነት የሌለው ጣፋጭ የሆነ መጠጥ::

**ለስላሳ ሙዚቃ** ስ ፍጥነት ያልበዛበት፥ ዝግ ያለ ምት ያለው የሙዚቃ ቅንብር::

**ልስልስ** ቅ 1. ሻካራነት የሌለው፥ ከርዳዳ ያልሆነ:: 2. (ዘይ.) አመሉ ጥሩ የሆነ:: *እገሌ ኣመሉ ልስልስ ነው::*

**ተለሳለሰ** ግ 1. ተቅለሰለሰ:: 2. ስራ ተወ፥ ተቀምጦ ዋለ:: 3. ይዞት የነበረውን ጠንከር ያለ አቋም (አመለካከት፥ ጥያቄ፥ ውሳኔ፥...) ለዘብ አደረገ፤ በረድ፥ ቀዝቀዝ አለ::

**አለሰለሰ** ግ ባዘተ፥ ቦጨቀ (ጥጥን)::

**አለሳለሰ** ግ 1. አዋዛ፥ ያዝ ተወት አደረገ (ህመም):: 2. ቀስ፥ ረጋ፥ ለዘብ አደረገ:: ችግርህን *ለሃላፊው ኣለሳልሰህ ንገረው::* 3. ላላ፥ ረገብ አደረገ (ግትር አቋምን)::

**ለሰሰ** ግ ለብ አለ፥ በጥቂቱ ሞቀ (ውሃ)::

**ለሰስታ** ስ መጠነኛ ሙቀት፥ ለብታ::

**ለስታ** ዝ.ክ.

**ለስታ ቅቤ** ስ 1. ከወተት መናጫው ወዲያው የወጣ ትኩስ ቅቤ:: 2. ያልተነጠረ ቅቤ::

**ለሰስ አለ** ግ ለብ፥ ሞቅ አለ (ውሃ)::

**ለስ አለ** ዝ.ክ.

**ለሰቀ** ግ 1. እንዲጠጋ፥ ለጥ ቀጥ ወይም ልክክ እንዲል ተደረገ ወይም አደረገ:: *ጨፌቃውን ለስቀህ እሰረው::* 2. ተጠጋ፥ ልክክ አለ::

**ልስቅ አለ** ግ ልክክ፥ ልጥቅ አለ፤ ተጠጋ::

**ተለሰቀ** ግ ተያያዘ፥ ተጣበቀ፥ ተጠጋጋ::


**ለሰነ** ግ ልጥፍን፥ ምርግን ላላ ባለ ጭቃና ጭድ እየቀባ ተመተመ፥ ለቀለቀ፤ ኣባጣ ጎባጣውን ኣስተካከለ::

**ለሰነበት** በጥፊ መታው::

**ለሳኝ** ስ የመለሰን ስራ የሚሰራ ባለሙያ::

**ልስን** ስ 1.ልጥፉ በጭድና ላላ ባለ ጭቃ በመለሰኛ የተስተካከለና የለሰለሰ ምርግ:: 2.የመለሰን ስራ:: *የቤቱ ምርግ ልስን ይቀረዋል::*

**መለሰኛ** ስ ለልስን ስራ የሚያገለግል ጠፍጣፋ እንጨት::



መለሰኛ

**ለሴ** ስ ለከት፤ ሙልሙል፤ ጥቢኛ::

**ለሸለሸ** ግ ጣለ፥ ኣጋደመ፥ አስተኛ፥ረፈረፈ::

**ለሽ አለ** ግ ተኛ፥ ተጋደመ፥ ወደቀ::

**ተለሸለሸ** ግ ተኛ፥ ተጋደመ፥ ተረፈረፈ::

**ለቀለቀ** ግ 1. ቀባ (በቅባት ወይም በቀለም፥ ወይም በእበት፥...):: 2. በሳሙና ወይም በኦሞ፥ ወይም በእንዶድ፥...የታሸውን በውሃ ኣጠራ:: 3. ኣጠበ፥ አፀዳ:: 4. በብዛት ወይም በስፋት ሰራ፥ ገጠገጠ (ቤትን፥ ድንኳንን፥ ...):: 5. ፃፈ (በብዛት)::

**ልቅላቂ** ስ 1. እጣቢ:: 2.(ዘይ.፥ ስድብ) የማይረባ፥ ተልካሻ፥ ልክስክስ::

**ተለቃለቀ** ግ 1.ተጣጠበ:: 2. (ዘይ.) ተነካካ፥ ኣንዱ ሌላውን በከለ:: (ለምሳሌ በነገር)::

**ኣለቀለቀ** ግ ኣጠበ፥ በውሃ ኣጣራ::

**ኣለቅላቂ** ቅ (ዘይ.፥ ስድብ) ኣጎብዳጅ፥ እወደድ ባይ፥ ኣሳባቂ::

**ኣለቃለቀ** ግ ኣነካካ፥ በከለ:: (ለምሳሌ በነገር)::

**ለቀመ** ግ 1. ኣነሳ፥ ብድግ ብድግ አደረገ:: 2. ሰበሰበ:: *ማገዶ ለቀመ::* 3. ፊደሎችን በተገቢ ቦታቸው በመደርደር ለህትመት ኣዘጋጀ (ማተሚያ ቤት):: 4. ለየ፥ ነቀሰ:: *ከስንዴ ውስጥ የተደባለቀውን በቆሎ እየለቀመ ኣወጣ::* 5. የመቃ ልቅም ጥበብ ሰራ:: 6. ሳር ጋጠ፥ በላ:: *በጎቹ ሳር ይለቅማሉ::* 7. በላ:: *የተዘራውን ወፍ ለቅሞ ጨረሰው::* 8. ያዘ:: *በከተማው ውስጥ ያሉትን ሌቦች ፖሊሶች ለቀሟቸው::* 9. ገደለ፥ ፈጀ፥ ጨረሰ:: *ጠላቶቹን በጥይት ለቀማቸው::*

**ለቀም (ለቅም)** ስ ግጦሽ::

**ልቃሚ** ቅ 1. ከእህል ውስጥ ተለይቶ የሚወጣ ጉድፍ፤ ብጣሪ:: 2.(ዘይ.፥ ስድብ) የማይረባ ልክስክስ፥ ተልካሻ፥ ጥርቃሚ::

**ልቃሞ** ዝ.ክ.

**ልቅሞሽ** ስ ልጆች ኣምስት ወይም ሰባት ጠጠር ይዘው ሽቅብ እየወረወሩና እየቀለቡ የሚጫወቱት ጨዋታ፤ ቅልቦሽ::

**መልቀሚያ** ስ በሸማ ጥበብ ስራ ጊዜ ሃሩን (ጥለቱን) ለማወሳሰብ የሚያገለግል ከወደ ጫፉ ሾል ያለ ጥርብ እንጨት ወይም ሸንበቆ::

**ለቀም ኣደረገ** ግ ያዘ፥ ኣፈፍ ኣደረገ::

**ለቃቀመ** ግ ምንም ሳይቀር ሁሉንም ያዘ፥ ወሰደ::

**ለቃቃሚ** ቅ (ስድብ) ልክስክስ::

**ልቅምቃሚ** ቅ 1. ትርፍራፊ፥ ጥርቅምቃሚ፥ የወዳደቀ:: 2. (ዘይ፥ ስድብ) የማይረባ፥ ተልካሻ::

**ልቅምቅም (ልቅምቃሞ)** ዝ.ክ.

**አለቀመ** ግ ሳር አጋጠ፥ አበላ (ከብቶችን)።

***ለቀሰ**

**ለቀስተኛ** ስ የሬሳ አጃቢ፣ ለቅሶ የሚደርስ፣ የሚያስተዛዝን ሰው።

**ለቅሶ (ልቅሶ)** ስ 1. ሃዘን። 2. ሙሾ፣ ዋይ ዋይታ። 3. መጮህ፣ ማንባት። 4. የእንባ መመንጨት፣ መውረድ፣ መፍሰስ።

**ለቅሶ ተቀመጠ** ዘመድ ወይም ወዳጅ ስለሞተበት ሃዘን ላይ ሆነ (በተወሰነ ቦታ ተቀምጦ አስተዛዛኞችን ወይም ለቅሶ ደራሾችን ለመቀበል)።

**ለቅሶ ደረሰ** ዘመድ ወዳጅ የሞተበት ሰው ዘንድ ሄደ (ለማስተዛዘን)።

**ለቅሶ ቤት** ስ ለቅሶ ወይም ሃዘን ያለበት ቤት (ሰው በመሞቱ ምክንያት)።

**ለቅሰኛ** ስ ለቀስተኛ።

**ተለቀሰ** ግ እንባ በማፍሰስ፣ በመጮህ፣ ዋይ ዋይ በማለት ታዘነ፥ ሃዘን ተገለፀ።

**መለቀሻ** ስ በለቅሶ ጊዜ ሟች እየታወሰ የሚለቀስበት የሟች ምስል፥ አጎበር፥ ፎቶግራፍ፥ የወግ የማእረግ ልብስ፥ ወዘተ.

**ተለቃሽ** ስ የሟች ቤተዘመድ።

**ተላቀሰ** ግ 1. በአንድነት ተሰባስቦ በእንባ ሃዘኑን ገለፀ። 2. ተማረረ፥ እሮሮ አሰማ።

**አለቀሰ** ግ 1. በሃዘን፥ በብስጭት፥ በደስታ፥...ስሜቱ ስለተነካ እንባውን አፈሰሰ፥ አነባ። 2.እንባ አፈሰሰ (አይን በጭስ፥ በህመም፥... ምክንያት)። 3. አማረረ፥ እሮሮ አሰማ።

**ማልቀሻ** ስ መለቀሻ።

**አልቃሻ** ቅ ነጭናጫ፥ ሆደባሻ፥ በሆነ ባልሆነ ነገር የሚያለቅስ።

**አልቃሽ** ስ 1. ለቀስተኛ። 2. በለቅሶ ጊዜ ሙሾ በማውረድ የሚያስለቅስ ሰው (ብዙውን ጊዜ ሴት)።

**አልቃሽ ቆመ** ሙሾ እያወረደና የሟችን ስም በግጥም እያነሳሳ ሃዘንተኞችን ለማስለቀስ አልቃሹ በለቅሶ መካከል ተገኘ።

**አለቃቀሰ** ግ ተነጫነጨ።

**አላቀሰ** ግ ከሟች ቤተሰብ ጋር አብሮ አለቀሰ፥ አስተዛዘነ።

**አስለቀሰ** ግ 1. እንዲያለቅስ፥ እንባ እንዲያፈስ አደረገ። 2. ሙሾ በማውረድ እንዲለቀስ አደረገ። 3. አበሳጨ፥ አስከፋ።

**ማስለቀሻ** ስ መለቀሻ።

**አስለቃሽ** ስ የ "**አልቃሽ**" 2ኛ ፍቺን ተመ.

**አስለቃሽ ጋዝ** ስ እንባ አስመጪ ጋዝ።

**ለቀቀ** ግ 1. ተወ። *በሽታው ለቀቀው።* 2. ነፃ አደረገ፥ ፈታ። *እስረኞቹን ለቀቃቸው።* 3. ፈታ፥ ሰደደ፥ አሰማራ። *ከብቶቹን ለቀቃቸው።* 4. (መኖሪያን፥ መስሪያ ቤትን፥ ...) ትቶ ሄደ። 5. ጠፋ፥ ተወገደ። *ብርዱ ለቀቀ።* 6. መረን ሰደደ፥ ያለ ቁጥጥር ተወ። 7. ተተረተረ። *ስፌቱ ለቀቀ።* 8. (የተጣበቀው፥ የተያያዘው፥ ...) ተለያየ። 9.(ቀለሙ፥ መልኩ፥ ...) ቀየረ፥ ደበዘዘ፥ ጠፋ። 10. (ቆሻሻው) ተወገደ። 11. ዋጋ ቀንሶ ሸጠ። 12. አንድን ድርጊት በስፋት፥ በብዛት፥ ያለገደብ ወይም ከቁጥጥር ውጪ በሆነ መንገድ አከናወነ፥ ፈፀመ። *ውሀቱን/ሳቁን ለቀቀው።* 13. ጥጥን ፈትሎ ልቃቂት አወጣ፤ አለቀቀ።

**ለቃቃ** ቅ ሰፊ። *ለቃቃ ቤት /አፈ ለቃቃ እንስራ።*

**ልቃቂት (ልቅ)** ስ ጥጥን በመፍተል እንዝርቱ ከሞላ በሂላ የሚወጣው ማግ፥ ፈትል።

**ልቃቂት**



**ልቅ** ቅ 1. ሰፊ። *አዳራሹ ልቅ ነው።* 2. ስድ፥ ባለጌ። ስ 3. "**ልቃቂት**" ን ተመ.

**ልቅ ወጣ** 1.ሙልጭ ወጣ፥ ምንም ሳይከፈል፥ ሳያገኝ፥ ሳይዝ ባዶ እጁን ቀረ። 2. ስድ፥ ባለጌ ሆነ፤ ተቆጣጣሪ አጣ።

**ልቅ ቀሚስ** ስ ወገቡ ላይ ሽንሽን የሌለው ሰፊ ቀሚስ።

**መልቀቂያ** ስ መሰናበቻ ደብዳቤ (ከስራ፥ ከትምህርት )።

**ተለቀቀ** ግ 1. ተፈታ (እስረኛ)። 2.ባዶ፥ ነፃ ሆነ (ቤት)። 3. ተተወ፥ ቀረ (እገዳ)።

**ተለቀቀበት** 1. (በብዛት፥ በስፋት) ተሰማራበት፥ ፋሽን እድርጎ ያዘው።*በሆቴል ንግድ ሰዉ ተለቀቀበት/ በአዲሱ ፋሽን ልብስ ሰው ሁሉ ተለቀቀበት።* 2. በብዛት ታየ፥ ተከሰተ። *በሰፈሩ በሽታ ተለቀቀበት።* 3. ስድብ አወረደበት።

**ተላቀቀ** ግ 1. ተለያየ፥ ተነጣጠለ፥ ተገነጠለ። 2. አረፈ፥ ተገላገለ፥ ነፃ ሆነ።

**መላቀቂያ** ስ መጋጠሚያ (ለሰውነት ክፍል)።

**አለቀቀ** ግ የ"**ለቀቀ**" ን 13ኛ ፍቺ ተመ.

**አላቀቀ** ግ 1. ለያየ፥ ነጣጠለ። 2. አፋሸገ፥ አዛጋ። 3. ገላገለ።

**ማላቀቂያ** ስ ሁለት ነገሮችን ለመለያየት የሚረዳ ነገር ወይም መሳሪያ::

**አስለቀቀ** ግ 1. ነፃ አወጣ:: *ምሽጉን አስለቀቀ::* 2. አስወጣ:: (ለምሳሌ ተከራዩን ከቤት):: 3. አፀዳ፥ ንፁህ አደረገ:: 4. አስመለሰ (ተይዞበት የነበረውን):: 5. ርኩስ መንፈስን በፀሎትና በጠበል በማስወጣት የታመመውን አዳነ፥ ፈወሰ::

**ማስለቀቂያ** ስ 1.ማስጣያ:: 2. ማስወገጃ:: 3.ማስመለሻ (ተይዞ የነበረውን):: 4.ማስፈቻ:: 5. ማፅጃ::

**ለቀተ** ግ አበደረ፥ አለቀተ::

**ተለቀተ** ግ ተበደረ::

**አለቀተ** ግ አበደረ፥ ለቀተ::

***ለቃ**

**ልቆ** ስ ብድር::

**ልቆኛ** ቅ ተበዳሪ፥ ሁልጊዜ ከብድር የማይወጣ::

**ተለቃ** ግ ተበደረ::

**አለቃ** ግ አበደረ::

**ለቅም** "**ለቀመ**" ስር "**ለቀም**" ን ተመ.

**ለቅሶ** "**ለቀሰ**" ስር ተመ.

**ለቆ** ስ 1. ከበጋ ቀጥሎ የሚመጣ የበልግ ወቅት:: 2. በበልግ ወቅት የሚበቅል ለምለም ሳር:: 3.ከድርቅ በሂላ የሚበቅል ለምለም ሳርን የበላ ከብት ቅዘን::

**ለቆታ** ስ ስልቻ፥ ቀልቀሎ::

**ለበለበ** ግ 1. በእሳት ጠበሰ፥ አሞቀ:: *ሞፈሩን ለማረቅ በእሳት ለበለበው::* 2.አቃጠለ፥ ፈጀ (ቃሪያ፥ በርበሬ፥ ሳማ፥ ...):: 3. መታ፥ ገረፈ፥ ሸነቆጠ (በአርጩሜ፥ በለበቅ፥ በአለንጋ፥ ...):: 4. ቆጠቆጠ፥ አመመ፥ አንጣጣ (ቁስል):: 5. ነዘነዘ፥ ጨቀጨቀ፥ ነተረከ፥ አንገበገበ (በነገር):: 6. (የአራዳ አነ.) በብዛት ጠጣ (አልኮልን):: 7. አንድን ድርጊት በብዛት አከናወነ:: *ጥናቱን ሲለበልብ ዋለ::*

**ለብላቢ** ቅ (የአራዳ አነ.) ጠጪ፥ ሰካራም::

**መለብለቢያ** ስ ቀጭን የመቀነቻ ጠፍር፤ መጥለፊያ፥ ማሰሪያ::

**ተለባለበ** ግ አቃጠለ፥ ተፋጀ (ቃሪያ፥ በርበሬ፥ ...)::

**አለብላቢት (ለብላቢት)** ስ 1. ሲነኳት እንደ ሳማ የምታቃጥል እፅ:: 2. (ዘይ.፥ ስድብ) ምላሰኛ፥ ለፍላፊ::

**ለበሰ** ግ 1. ሸፈነ (ሰውነቱን በልብስ፥ በቆዳ፥ ...):: 2. ተሸፈነ:: *ላካባቢው ጉም ስለ ለበሰ ከሩቅ ማየት አይቻልም::* 3. ጠጣ፥ ከለበሰ:: *ሁለት ብርሌ ጠጅ ከለበሰ ሰው አያናግርም::*

**ለብሰህ ፍጀው** አዲስ ልብስ የለበሰን ሰው ልብሱን ለብሰህ ጨርሰው ለማለት የሚነገር ምርቃት::

**ለባሽ** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) የእለቱ ተረኛ ቀዳሽ::

**ልባስ** ስ ሽፋን፥ መሸፈኛ::

**ልብስ** ስ ከሃር፥ ከፀጉር፥ ከጥጥ፥..የሚሰራ የሰውነት መሸፈኛ

**ልብስ አስቀደደ/አስለካ** ልብስ ለማሰፋት በልኩ አስቀረጠ::

**ልብሰ መንግስት** ስ ንጉስ በዙፋን ሲቀመጥ የሚለብሰው የማእረግ ልብስ::

**ልብሰ ማርያም** ስ በሰማያዊና በቀይ ከፋይ ቀለም የሚሳል የማርያም ስእል ካባ::

**ልብሰ ተክህኖ** ስ በመንፈሳዊ አገልግሎት ጊዜ ቀሳውስትና ዲያቆናት በቤተክርስቲያን የሚለብሱት ልብስ::

**ልብስ መስቀያ** ስ ከብረት፥ ከእንጨት፥ ... የሚሰራ የልብስ ማንጠልጠያ::

**ልብስ ሰፊ** ስ እንደ ኮት፥ ሸሚዝ፥ ቀሚስ፥ ... ያሉ ልብሶችን በልብስ ስፌት መኪና እየሰፋ የሚተዳደር ባለሙያ::

**ልብስ አጣቢ** ስ ልብስ በማጠብና በመተኮስ በሚያገኘው ገቢ የሚተዳደር ሰው::

**የልብስ ሳሙና** ስ በተለይ ለልብስ ማፅጃ ወይም ማጠቢያ እንዲያገለግል የተዘጋጀ ሳሙና::

**የልብስ ንፅህና መስጫ** ስ በዘመናዊ የልብስ ማጠቢያ መሳሪያ ልብሶችን የሚያጥብ ወይም የሚያፀዳ ድርጅት፤ ላውንድሪ::

**ልቧስ (ልባሽ)** ስ አዲስ ያልሆነ፥ የተለበሰ ልብስ፤ ውራጅ::

**መልበሻ ክፍል** ስ ለተወሰነ ስራ አስፈላጊ የሚሆነው የሙያ ልብስ የሚቀየርበት ክፍል (ለምሳሌ ቲያትር ቤት ውስጥ፥...)::

**ለበስ አለ** ግ ወፈር አለ::

**ተለባበሰ** ግ 1.ተድበሰበሰ፥ ተሸፋፈነ:: 2.አንዱ የሌላውን ምስጢር ወይም ገመና ሸሸገ፥ ደበቀ::

**ተላበሰ** ግ 1. ኩታውን መስቀለኛ ለበሰ፥ አደገደገ (ካህን፥ ዲያቆን፥ ...):: 2. ተዋሃደ:: *ተዋናዩ የሚወክለውን ገፀባህርይ ተላብሶታል::* 3. አገኘ:: *ግርማ ሞገስ ተላበሰ::*

**አለበሰ** ግ 1. በብዛት ሸፈነ:: *አዝመራው አገሩን አልብሶታል::* 2. ልብስ ሰጠ፥ ገዛ:: *አጎቴ ለጥምቀት አዲስ ልብስ አለበሰኝ::*

**አልብሺኝ አንተርሺኝ** የጣጣ ብዛት፥ ሰበብ አስባብ:: *የዛሬው ቀን በአልብሺኝ አንተርሺኝ መሸ::*

**አልባሽ** ስ (ለንጉስ፥ ለልእልት፥...) ልብስ የሚያቀርብ፥ የሚያለብስ ባለሟል።
**አለባበሰ** ግ 1. ነካ ነካ አድርጎ ተወ፥ በሚገባ ሳይሰራ ቀረ። *ለለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ።* 2. አድበሰበሰ፥ ሸፋፈነ፥ ግልፅ እንዳይሆን አደረገ።
**ማላበሻ** ስ አላባሽ።
**አላባሽ** ስ አብሮ የሚለበስ፥ ማሟያ ልብስ። *ሱሪው አላባሽ ኮት የለውም።*
**ለበቀ** ግ 1.ለማስታወክ ወይም ለማስመለስ ተናነቀ። 2. አስታወከ፥ አስመለሰ።
**ለበቅ** ስ መግረፊያ ነገር፥ ጨንገር፥ አርጩሜ፥ ልምጭ።
**ለበን**[1] ስ ለምቦጭ፥ የታችኛ ከንፈር።
**ለበኑን ጣለ** አኮረፈ።
**ለበናም** ቅ (ስድብ) ለምቦጫም።
**ለበን**[2] ስ የጠመንጃ አይነት።
**ለበደ** ግ 1. የአንድን ነገር አካል በቆዳ፥ በወርቅ፥... ሸፈነ፥ ጠረዘ፥ አሸገ። *ግድግዳውን በጋዜጣ ለበደ።* 2. ሽንቁርን ወይም ቀዳዳን ደፈነ፥ ሸፈነ።
**መለበጃ** ስ መሸፈኛ (የደብተር፥ የመፅሃፍ)።
**ለበጠ** ግ በመፅሃፍ፥ በጋሻ፥ ... ላይ ብርን፥ ወርቅን በመለጠፍ አስጌጠ፥ አስዋበ።
**ለበጣ** ስ ሽሙጥ፣ ሽርደዳ፣ ምፀት።
**የለበጣ ስራ** ስ ከልብ ያልሆነ፥ የልግም ስራ።
**ለብ**
**ለብታ** ስ 1. መጠነኛ ሙቀት፥ ለሰስታ (የውሃ)። 2. (ዘይ.) ሞቅታ፥ መጠነኛ ስካር።
**ለብታ ውሃ** ስ ሞቅ፥ ለሰስ ያለ ውሃ።
**ለብ አለ** ግ ሞቅ፥ ለሰስ አለ።
**ለብ አለው** በመጠኑ ሰከረ፥ ሞቅ አለው።
**ለብ አደረገ** ግ በመጠኑ አሞቀ።
**ለብ አደረገው** በመጠኑ አሰከረው።
**ለብ ለብ** ስ ሞቅ ሞቅ የተደረገ ወይም እሳት ያልገባው ክትፎ፥ ዱለት፥ ...።
**ለተለተ** ግ 1. ወዲያና ወዲህ አለ። 2. ተንከወከወ፥ ተንጠለጠለ፥ ዞረ፥ ተቅበዘበዘ።
**ለትላታ (ለተለት)** ቅ ከውካዋ።
**ልትለታ** ስ መወዝወዝ፥ መቅበዝበዝ፥ ወዲያና ወዲህ መባከን።
**አለተለተ** ግ ሰውነቱን አወዛወዘ።
**ለተመ** ግ 1. በሃይል መታ፥ ገጨ፥ ደቃ። 2. ወጋ (በግ)።
**ተላተመ** ግ ከአንድ ነገር ጋር ተጋጨ።
**አላተመ** ግ አጋጨ። *መኪናውን ከግንድ ጋር አላተመው።*
**ለተተ** ግ 1. ለፋ፥ ለሰለሰ። 2. ለዘዘ፥ ረጠበ።
**ለት "እለት"**ን ተመ.
**-ለት** (በየመደቡ ሲዘረዘር -ልኝ፥ -ልሀ፥ -ልሽ፥ -ላት፥ -ልን፥ -ላችሁ፥ -ላቸው፥ ይሆናል) በግስ መድረሻ ላይ እየተቀጠለ ለእሱ የሚለውን የድርጊት ተጠቃሚ የሚያሳይ ምእላድ። *ገንዘብ ላከለት /ደብዳቤ ፃፈላት።*
**ለነቀጠ** ግ የተገረደፈውንና በውሃ የራሰውን በቆሎ፥ ማሽላ፥... በእጅ ወፍጮ አልሞ ፈጨ፥ ደቆሰ።
**ልንቅጥ** ስ የተለነቀጠ እህል ሊጥ።
**መለንቀጫ** ስ ለመለንቀጥ የሚያገለግል የእጅ ወፍጮ።
**ለንቋጣ** ስ 1. በወይና ደጋና በቆላ የሚበቅል ልጡ ማላጋ የሆነ አነስተኛ የእፅዋት አይነት። 2. (ዘ.ይ) አቅመ ቢስ፥ ለዋሳ።
**ለንባዳ (ለምባዳ)** ቅ ኮልታፋ፥ ምላሰ ጎልዳፋ።
**ለንቦጭ (ለምቦጭ)** ስ ወፈርና ዘርበብ ያለ የታች ከንፈር።
**ለንቦጩን ጣለ** አኮረፈ።
**ለንቦጫም** ቅ (ስድብ) ለንቦጩ ትልቅ የሆነ።
**ለንጨጭ** ስ የጋማ ከብት ከንፈር።
**ለንጨጫም** ቅ (ስድብ) ትልቅ ወይም ከመጠን በላይ የወፈረ ከንፈር ያለው (ሰው)።
**ለከለከ**[1] ግ 1. በምላሱ እየጨለፈ ጠጣ (ውሻ፥ ድመት፥...)። 2. ጠባ (ወተትን)። 3. በብዛት ጠጣ።
**አለከለከ** ግ በፀሃይ ሙቀት፥ በሩጫ፥ ...ምክንያት ከሚመጣ ድካም የተነሳ ቶሎ ቶሎ ተነፈሰ።
**አስለከለከ** ግ በማስሮጥ፥ በማራወጥ አደከመ፥ ቁና ቁና አስተነፈሰ።
**ለከለከ**[2] **"ሉከሉክ"**ን ተመ.
***ለክስክስ**
**ልክስካሽ** ስ ከብቶች ሲበሉ የሚያዝረከርኩት ገለባ፥ ሳር፥...።
**ልክስክስ (ለክስካሳ)** ቅ (ስድብ)1. ምናምንቴ፥ የማይረባ። 2. ለቃቃሚ፥ ልክፍክፍ። 3. አመንዝራ።
**ተልከሰከሰ** ግ 1.ቅጥ አጣ፥ ተዝረከረከ። 2. የማይረባ፥ ልክስክስ ሆነ። 3. በተወሰነ አካባቢ ብቻ መለስ ቀለስ አለ፥ ተመላለሰ። 4.ተድበሰበሰ፥ ተሸፋፈነ (ለነገር)። 5. (ዘይ.) አመነዘረ፥ ሸረሞጠ።

**ተልከስካሽ [ሰይጣን]** ስ በየቆሻሻው ላይ ይገኛል የሚባል ሰይጣን::

**አልከሰከሰ** ግ 1. ቅጥ አሳጣ፥ አዝረከረከ፥ በታተነ:: 2. ጀምሮ፥ ነካ ነካ አድርጎ ተወ፡ (ምግብን፥ ስራን፥ ...):: 3. ልክስክስ አደረገ:: 4. መለስ ቀለስ እንዲል አደረገ:: *እዚህ አካባቢ ምን ያልከሰከሰሃል::*

**ለከት**[1] ስ 1. ክዳን ወይም ግጣም:: 2. ወሰን፥ ወይም ገደብ:: *ለአነጋገሩ ለከት የለውም::*

**ለከት**[2] ስ ጥቢኛ፥ አነስተኛ ዳቦ::

**ለከከ "ላከከ"** ን ተመ.

**ለከፈ** ግ 1. በመቅመስ፥ በመንካት፥ በመላስ አረከሰ (ውሻ፥ ድመት፥ ...):: 2. ነካ፥ በሽታ አስተላለፈ (የታመመ ውሻ):: 3. ጀመረ፥ ያዘ (በሽታ):: *የዛሬ ላመት የለከፈው በሽታ አሁንም አልለቀቀውም::* 4- ጀመር አድርጎ ተወ:: *ምነው ለከፈህ ትተወዋለህ፥ ጨርሰህ ብላው እንጂ::* 5. ነገር ፈለገ፥ ተነኮሰ::

**ለከፋ** ስ ነገር ፍለጋ፥ ትንኮሳ::

**ለካፊ** ቅ ነገር ጫሪ፥ ተንኳሽ::

**ልክፍት** ስ 1. በርኩስ መንፈስ ምክንያት የሚመጣ በሽታ:: 2. የበሽታ መነሾ:: 3. የቆዳ በሽታ አይነት (ክፍቱን ባደረ ወይም ንፁህ ባልሆነ ውሃ በመታጠብ ይመጣል ተብሎ የሚታመን)::

**ልክፍታም** ቅ ወፈፌ::

**ለካከፈ** ግ 1. ቀመስ ቀመስ አድርጎ ተወ (ምግብን):: 2.ሁሉንም ለከፈ፥ ነካካ፥ አዳረሰ::

**ልክፍክፍ (ለከፍካፋ)** ቅ (ስድብ) ልክስክስ፥ የማይረባ፥ ለቃቃሚ::

**ተለከፈ** ግ በበሽታ ተያዘ፥ ታመመ::

**በ ______ ተለከፈ** 1. በ ______ ተያዘ፥ ተጠመደ:: *በፍቅር ተለከፈ::* 2.በ_ ምክንያት በሽታ ያዘው፤ ለበሽታ ተጋለጠ:: *በብርድ ተለከፎ ለሞት በቃ::*

**ተለካከፈ** ግ 1. ተጣላ፥ ተሰዳደበ:: 2. ተነካካ::

**ተላከፈ** ግ 1.ተቃመሰ፥ ተካፈለ (ምግብን):: 2. ተጣላ፥ ተተናኮሰ::

**ተላካፊ** ቅ ነገረኛ፥ ተሳዳቢ::

**ተልከፈከፈ** ግ ተልከሰከሰ፥ ልክስክስ ሆነ::

**አለከፈ** ግ አቀመሰ (ምግብን)::

**አላከፈ** ግ አቃመሰ፥ አዳረሰ (ምግብን)::

**አልከፈከፈ** ግ አልከሰከሰ::

***ለከፈ**

**ለካፋ(ልክፍ)** ቅ ከሚጠላበት (ከማይፈለግበት) ቦታ የማይታጣ፥ ሳይጠሩት የሚመጣ፥ ልክስክስ፣ ቀላዋጭ::

**ተለከፈ** ግ ተገተረ፥ ተደቀነ:: *እፊቴ አትለከፍ::*

**ለካ**[1] ግ 1. ቁመትን፥ ስፋትን፥ ክብደትን፥ ... በተወሰነ መለኪያ መጠነ፥ ሰፈረ፥ መዘነ:: 2. ልብስን፥ ጫማን፥ ... ልክ ይሆነው እንደሆን በመልበስ፥ በማድረግ ሞከረ::

**ልክ** ስ 1.መጠን፤ ብዛት:: 2. ትክክል፥ እርግጥ፥ እውነት:: 3. ሳይተርፍ ወይም ሳይጎድል በትክክል:: *ልክ ሰባት ሰአት ላይ::* ቅ 4. ተስማሚ፤ ያልሰፋ፥ ያልጠበበ፥ ያላጠረ፥ ያልረዘመ (ልብስ፥ ጫማ፥ ...)::

**ልኩን አገኘ** 1. ተገቢውን ቅጣት አገኘ:: 2. አቻውን አገኘ (ለጋብቻ)::

**ልኩን የማያውቅ** አቅሙን የማያውቅ፥ ያለ አቅሙ የሚንጠራራ::

**ልክ ልኩን ነገረው** ሙልጭ አድርጎ ሰደበው::

**ልክ መጣ** ተስማማ፥ ልክ ሆነ::

**ልክና መልክ የለውም** ቅጥ ያጣ ነው::

**ልክ የለውም** ብዙ፥ አያሌ ነው::

**ልክ ገባ** ተስተካከለ፥ ልክ ሆነ::

**በልክ ሁን** ስርአት ያዝ፥ ታረም፥ ተቆጠብ::

**ከልክ ያለፈ** ከመጠን በላይ የሆነ፥ በጣም ብዙ::

**ያለ ልክ** ከመጠን በላይ::

**ልከኛ** ቅ የተስተካከለ፤ ያላጠረ፥ ያልረዘመ፥ ያልቀጠነ፥ ያልወፈረ::

**መለኪያ** ስ ከቀንድ ወይም ከብርጭቆ፥... በትንሹ የተሰራ የአረቄ መጠጫ::

**ተለካ** ግ ልብስ ለማሰፋት ልኩን አሳወቀ::

**ተለካካ** ግ ተነፃፀረ፥ ተወዳደረ (ለምሳሌ ቁመት፥...)::

**አለካካ** ግ መጠንን፥ ክብደትን፥ ስፋትን አነፃፀረ፥ አወዳደረ::

**ለካ**[2] **(ለካስ፥ ለካን)** ቃ. አ. ያልጠበቁት ነገር ሆኖ ሲገኝ " አሁን ገና አወቅሁ፥ እንደዚህ ነበር ወይ" የሚል አድናቆትን፥ መገረምን፥... የሚገልፁበት ቃል::

**ለኮ**[1] ስ ከልባብ ጋር የተያያዘ ወይም የተቋጠረ የፈረስና የበቅሎ መሳቢያ ጠፍር ወይም ገመድ::

**ለኮ**[2] ስ ከመሬት ገና ብቅ ያለ ሳር፤ ጨሌ::

**ለኮሰ** ግ 1. እሳትን አቀጣጠለ፥ አያያዘ:: 2. ተኮሰ፥ ፈጀ፥ አቃጠለ:: 3. አበራ (ችቦን፥ ሻማን፥ ...):: 4. አያያዘ፥ አቀጣጠለ (የኤሌክትሪክ ምድጃን፥ ምጣድን፥...):: 5. (ዘይ.) ጀመረ፥ ጫረ (ጠብን)::

**መለኮሻ** ስ የእሳት ማያያዣ (ላይተር፥

ክብሪት፥...)።

**አለኳኮሰ** ግ አላኮሰ።

**አላኮሰ** ግ አጣላ፥ አፋጀ፥ በነገር አጋጨ።

**አላኳሽ** ቅ ነገር እየቆሰቆሰ የሚያጣላ።

***ለኮሰ**

**ለኳሳ (ልኩስ)** ቅ ለዋሳ፥ አቅመቢስ፥ ደካማ።

**ልኩስ አለ** ግ ውሽቅ፥ ውትፍ አለ። *ሰው ቤት ምን ወስዶ ልኩስ አደረገህ።*

**ልኩስኩስ (ለኮስኳሳ)** ቅ 1. የማይረባ፥ ውትፍትፍ። 2. ንፅህናውን የማይጠብቅ፥ ፅዳት የሌለው፥ እርምጥምጥ።

**ልኩስኩስ አለ** ግ ተልኮሰኮሰ።

**ልኩስኩስ አደረገ** ግ አልኮሰኮሰ።

**ተለኮሰ** ግ ተወሸቀ፥ ተወተፈ።

**ተልኮሰኮሰ** ግ 1. ተርመጠመጠ፥ ተበላሸ፥ ቆሸሸ። 2. ተድበሰበሰ።

**አልኮሰኮሰ** ግ 1. አርመጠመጠ፥ አበለሻሸ፥ አቆሸሸ። 2. አድበሰበሰ።

**ለኮፈ** ግ በትንሹ መታ፥ ነካ አደረገ።

**ልኩፍኩፍ (ለኮፍኳፋ)** ቅ 1.በደንብ ያልተሰራ፥ ውሽልሽል። 2. ጥራት ያለው ስራ የማይሰራ።

**ተልኮፈኮፈ** ግ 1.ነካ ነካ ተደርጎ ተተወ፥ በደንብ ሳይሰራ ቀረ። 2. ተልጎመጎመ፥ ተጉተመተመ፥ በግልፅ ሳይናገር ቀረ።

**አልኮፈኮፈ** ግ 1. የማያረካ ስራ ሰራ፥ ነካ ነካ አድርጎ ተወ። 2. አልጎመጎመ፥ አጉተመተመ።

***ለወለወ**

**ለውላዋ (ለውለውቱ)** ቅ ከውካዋ፥ ጦልጧላ፥ ዘዋሪ።

**ለውለው አለ** ግ ወዲያ ወዲህ አለ፥ ተንከወከወ።

**ለወሰ** ግ 1. እንደ ዱቄት ያለን ነገር ፈሳሽነት ካለው ነገር ጋር ቀላቅሎ አቦካ፥ አሸ። 2. በጭቃ፥ በእበት፥ ... አበላሸ፥ አቆሸሸ። *ልብሱን በጭቃ ለውሶ መጣ።* 3. በእግሩ ረጋገጠ፥ አዳከረ (ያደገ እህልን፥ ሳርን)። 4. አጥመለመለ፥ አደቀቀ፥ አዳከመ፥ ሃይል አሳጣ (በሽታ)። 5. መሬት ላይ ጥሎ መታ፥ ረገጠ።

**ለዋሳ** ቅ አቅመ ቢስ፥ ደካማ።

**ልውስ** ቅ 1. ለዋሳ። 2. በወፍራሙ የተቦካ ሊጥ።

**ተለወሰ** ግ 1.ተበላሸ፥ ተለቀለቀ፥ ተጨማለቀ (በቆሻሻ፥ በጭቃ)። 2. በበሽታ ምክንያት ተዳከመ፥ አቅም አጣ፥ ተጥመለመለ።

**ተለዋወሰ** ግ 1. ተበለሻሸ፥ ተጨመላለቀ (በቆሻሻ ነገር)። 2. ተልፈሰፈሰ፥ ዛለ፥ ደከመ፥ አቅም አጣ።

**ለወጠ** ግ 1. የአንድን ነገር ቀድሞ የነበረ ሁኔታ፥ ባህርይ፥ መልክ፥... በሌላ እንዲቀየር፥ እንዲተካ አደረገ። 2. አንድ ነገር ቀድሞ የነበረውን ሁኔታ፥ ባህርይ፥ መልክ፥... በሌላ ቀየረ። *ከመቆየቱ የተነሳ ቀለሙ ለወጠ።* 3. አንድን ነገር ሰጥቶ በምትኩ ሌላ ነገር ወሰደ። *እስክሪብቶውን በእርሳስ ለወጠ።* 4. ቀየረ፥ በሌላ ተካ። *አሮጌውን ልብስ ለውጦ አዲሱን ለበሰ።* 5. ቀየረ፥ ተበላሸ (የምግብ ጣእም፥ ሽታ)። 6. ቀድሞ ከነበረው አሻሻለ። *የኢኮኖሚ ፖሊሲው የህዝቡን ኑሮ ለውጦታል።* 7. የነበረበትን ቦታ ትቶ ወደ ሌላ ቦታ ሄደ። *ሰፈር ለወጠ።*

**___ን በ___ ለወጠ** ከ___ ይልቅ ___ን መረጠ፥ አስበለጠ። *ጓደኛውን በገንዘብ ለወጠ።*

**ለውጥ** ስ 1. አንድን ነገር የመስጠትና በምትኩ ሌላ የመውሰድ ሂደት ወይም ድርጊት። *በነፃ የተሰጠኝ ሳይሆን በለውጥ ያገኘሁት ነው።* 2. አንድን ነገር በመስጠት በምትኩ የተወሰደ ነገር። *ይህ መፅሃፍ የዚያኛው ለውጥ ነው።* 3. አዲስ ሁኔታ፥ የተለየ ነገር፤ ልዩነት። *ቀደም ሲል ከነበረው አሰራር ያሁኑ ብዙ ለውጥ ይታይበታል/በዚህና በዚያኛው መካከል ምንም አይነት ለውጥ የለም።* 4. የአንድ ህብረተሰብ የፖለቲካ ስርአት ወይም የመንግስት መዋቅር በሌላ መተካት።

**ልዋጭ** ስ 1. አንድን ነገር በመስጠት በምትኩ የሚወሰድ ቅያሪ፥ ምትክ። ቅ 2. መቀየሪያ የሚሆን። *ልዋጭ ሸሚዝ የለውም።*

**መለወጫ** ስ መቀየሪያ።

**ለዋወጠ** ግ ቀያየረ።

**መለዋወጫ** ስ ላለቀ ወይም ለተበላሸ እቃ መተኪያ እንዲሆን የተቀመጠ እቃ።

**ልውውጥ** ስ አንድን ነገር የመስጠትና በምትኩ ሌላ የመውሰድ ድርጊት።

**ልውጥ አለ** ግ ቅይር አለ። *እሷ አለመኖሯን ሲያይ ፊቱ ልውጥ አለ።*

**ልውጥውጥ አለ** ግ ተለዋወጠ።

**ተለወጠ** ግ 1. በፊት በነበረው ፋንታ ተተካ። 2. የነበረው ሁኔታ ተቀየረ። *የወጡ ቃና ተለውጧል/ያገሪቱ ሁኔታ እንደድሮው አይደለም፥ ተለውጧል።*

**ተለዋጭ** ቅ ተቀያሪ።

**ተለዋጭ ቀጠሮ** ስ ቀደም ሲል በተያዘው ቀነ ቀጠሮ ፋንታ የተያዘ ሌላ የቀጠሮ ቀን።

**ተለዋወጠ** ግ 1.ተቀያየረ። 2. በንዴት ወይም በድንጋጤ መልኩ ወይም ፊቱ፥ ሁኔታው ከበፊቱ የተለየ ሆነ።

**ተለዋዋጭ** ቅ 1. አንድ ጊዜ አንዱን ሌላ ጊዜ ሌላውን የሚሆን፥ ቶሎቶሎ የሚቀያየር። 2.

ወረተኛቲ ጠባዩ እንደየሁኔታው የሚቀያየር:: 3. ተወራራሽ:: *"ጀንበር" ወይም "ዠንበር" በሚለው ቃል ውስጥ 'ጀ' ና 'ዠ' ተለዋዋጭ ድምፆች ናቸው::*

**አለዋወጠ** ግ አንዱን ባንዱ ወይም አንዱን ወዳንዱ አቀያየረ፥ አዘዋወረ::

**ማለዋወጫ** ስ መቀያየሪያ::

**አላወጠ** ግ 1.ቀየረ፡ ለወጠ:: *ባለቤት የወደደው አህያ ፈረስ ያላውጣል::* 2. የአንዱን ወደ ሌላ አዛወረ፥ ቀያየረ::

**አስለወጠ** ግ አስቀየረ፡ ሌላ አስደረገ:: *የመኪናውን ጎማ አስለወጠ::*

**ለዋ** ግ ጅው አድርጎ ጠጣ::

**ለውዝ** ስ እንደ ድንች በመሬት ውስጥ የሚያፈራና እየተቆላ የሚበላ ፍሬ፤ ኦቾሎኒ::

**ለውጥ "ለወጠ"** ስር ተመ.::

**ለዘለዘ** ግ ጠባ፥ መጠመጠ::

**ለዘበ** ግ 1. ለሰለሰ፥ ሻካራነቱን ተወ:: 2. ለፋ(ለቆዳ):: 3. ገራም ሆነ::

**ለዘብ** ስ በበአል ቀን በቅኔ ማህሌትና በኡደት ጊዜ (ታቦት ሲነግስ) ከፅናፅልና ከከበሮ ድምፅ ጋር በመጎዳኘት እየተመላለሰ የሚባል የወረብ ዜማ፤ ወረብ::

**ለዘቡ ተባለ** ግ ተወረበ::

**ለዘብተኛ** ቅ 1. ስህተት ሲፈፀም እያየ በቸልታ፥ በይሉኝታ፥ በግዴለሽነት የሚያልፍ:: 2. ወግ አጥባቂ፥ አክራሪ ያልሆነ:: 3. በአንድ የፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ የፓርቲውን ደንብና ስርአት የማያከብርና የማያስከብር ፥ ቸልተኛ::

**ለዘብተኝነት** ስ ለዘብተኛ የሆነ የፖለቲካ አቋም::

**ለዘብታ** ስ እርጋታ፥ ቀስታ::

**ልዝብ** ቅ 1. ልስልስ:: 2- ገራም::

**ልዝብ ሰይጣን** ስ ሲያዩት ደግ፥ ገራገር፥ የዋህ የሚመስል ግብሩ ግን ሰይጣናዊ፥ ተንኮለኛ የሆነ ሰው::

**ተለዘበ** ግ ተወረበ፥ ለዘቡ ተባለ::

**አለዘበ** ግ 1. አለሰለሰ:: 2. አለፋ(ቆዳን):: 3. አገረመ፥ ገራ፥ አለሰለሰ (ጠባይን):: 4.ወረበ:: 5. በደንብ መላልሶ አጠና (ቅኔን፥ ዜማን)::

**ለዘዘ** ግ 1. ደረቅ የነበረው እንደ መርጠብ ወይም እንደ መራስ አለ፥ ለተተ:: 2. ተሰለቸ፥ ቸከ፥ ተጠላ::

**ለዛዛ** ቅ 1. እርጥበት ያለው ወይም በደንብ ያልደረቀ:: 2. ሞዛዛ፥ ቸካካ::

**ተላዘዘ** ግ 1. ለዛዛ ሆነ:: 2. ተሟዘዘ::

**አለዘዘ** ግ መጠነኛ እርጥበት እንዲኖረው አደረገ፥ አራሰ::

**ለዛ** ስ ውበት፥ ማማር፥ ማራኪነት (የአነጋገር፥ የመልክ፥...)::

**ለዛ ሙጥጥ** ቅ ለዛ የሌለው፥ ቢናገር የማያምርበት፤ ችኮ::

**ለዛ ቢስ** ቅ ውበት፥ ማራኪነት የሌለው (የአነጋገር፥ የመልክ፥ ...)::

**ለየ** ግ 1.መረጠ፥ ነጠለ፥ ከፈለ፥ ለብቻ አደረገ:: 2. ከለለ፥ ጋረደ:: *መኝታ ቤቱን በመጋረጃ ለየ::* 3. አደላ::*ከልጅ ልጅ ቢለዩ ላመትም አይቆዩ::* 4. አራቀ፥ አገለለ:: *የሚጠቅም ነገር ሲኖር ሁልጊዜ እሱን ይለዩታል::* 5. አስታወሰ፥ አወቀ::*ከውጭ አገር የመጣውን ወንድሙን መጀመሪያ ሲያየው መለየት አቃተው::* 6. ታወቀ፥ ግልፅ ሆነ ወይም አሳወቀ፥ ግልፅ አደረገ:: *አቋሙ ለየ /አቋሙን ለየ::*

**ለየለት** 1. ቁርጡ ታወቀ፥ ተረጋገጠ:: 2. ጨርሶ አበደ::

**አይለየን** (ምር.) አሁን አብረን እንዳለን አብሮ ያቆየን::

**የለየለት** ዋና፥ ቀንደኛ:: *የለየለት ሌባ ነው::*

**ይለይለት** 1. ቁርጡ ይታወቅ:: 2. የመጣው ይምጣ፥ የሆነው ይሁን::

**ይለይልን** ይዋጣልን፥ አሸናፊው ይታወቅ::

**ልዩ** ቅ 1. ከሌላ ወይም ከበፊቱ ጋር የማይመሳሰል፥ የተለየ:: *ከወንድሞቹ መሃል የሱ መልክ ልዩ ነው::* 2. ከተለመደው፥ ከመደበኛው የተለየ፤ ብልጫ ያለው:: *ለፈፀሙት ጀብዱ ልዩ ሽልማት ተሰጣቸው::*

**ልዩ ልዩ** ቅ የተለያዩ::

**ልዩ ቅናሽ** ስ በአንድ ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ በእቃዎች ላይ የሚደረግ የዋጋ ቅናሽ::

**ልዩ ፀሃፊ** ስ አንድ ከፍተኛ ባለስልጣን የሚመለከታቸውን ጉዳዮች የሚመዘግብና የሚያስፈፅም የፅህፈት ቤቱንም ስራ የሚያከናውን ፀሃፊ::

**ልዩነት** ስ 1.አንዱ ከሌላው የሚለይበት ሁኔታ፥ አለመመሳሰል:: 2.አለመስማማት፥ አለመግባባት:: 3. በሁለት ነገሮች መካከል የሚታይ የመጠን ብልጫ ወይም ጉድለት::

**መለዮ** ስ 1. የወታደር ቆብ:: 2. አንዱ ከሌላው ተለይቶ የሚታወቅበት፤ መለያ::

**መለዮ ለባሽ** ስ መደበኛ ወታደር::

**ለያየ** ግ 1. ነጣጠለ፥ ለየብቻ አደረገ:: 2. አላቀቀ፥ ገላገለ:: 3. ከፋፈለ:: 4. አቃቃረ፥ አቆራረጠ::

**ተለየ** ግ 1. ተነጠለ፥ ብቻውን ሆነ፥ ተገለለ:: 2. ተከፈለ፥ ተከለለ:: 3. ታወቀ፥ ተጣራ፥ ግልፅ ሆነ:: 4. ከሌሎች ልዩ ሆነ፥ ሌሎችን አልመስል

አለ::

**በተለይ** ተው.ግ. 1.በይበልጥ፥ ከሌሎች ይልቅ:: *ከልጆቹ መሃል በተለይ እሷን ይወዳል::* 2. ከሌላው የበለጠ:: *የሷ ቀንጆና በተለይ ነው::* 3. ለብቻ:: *የሱ ድርሻ በተለይ ይቀመጥለት::*

**የተለየ** ቅ 1.ከሌላው የማይመሳሰል:: *የተለየ ሃሳብ ካለ ማቅረብ ይቻላል::* 2. ከሌላው የባሰ፥ የበለጠ:: *የዛሬው ብርድ የተለየ ነው::*

**መለያ** ስ ከሌላው ተለይቶ የሚታወቁበት ምልክት::

**መለያ ቁጥር** ስ አንድ ነገር መሰሉ ከሆነው ከሌላው ነገር ተለይቶ የሚታወቅበት ቁጥር::

**ተለያየ** ግ 1. ተነጣጠለ:: 2. ተራራቀ(በሃሳብ፥ በቦታ፥...):: 3. ተፋታ (ከትዳር ጓደኛ):: 4.ተላቀቀ::

**በተለያየ መንገድ** በተለያየ አቅጣጫ፥ አንፃር፥ አኳያ::

**መለያያ** ስ 1. የአካል አንጓ፤ መጋጠሚያ:: 2. መስነባበቻ:: *የመለያያ ግብዣ ተደርጎ ነበር::* 3. መገንጠያ (ለመንገድ)::

**አለያየ** ግ 1. ለየብቻ አደረገ፥ ለየየ:: 2. አላቀቀ፥ ገላገለ:: 3. አቆራረጠ፥ አቃቃረ:: 4. አፋታ(ከትዳር)::

**ለይስሙላ** "ሰማ[1]" ስር ተመ:

**ለደለደ** ግ ቀጭን የነበረው ፈሳሽ ወፈረ፥ ተምለገለገ (ተልባ፥ አብሽ፥...)::

**ልድልድ** ቅ የለደለደ፥ የወፈረ::

**አለደለደ** ግ 1. ለደለደ:: 2.አወፈረ (ፈሳሽ ነገርን)::

**ለደሰ** ግ ለጠፈ፥ ቀባ::

**ለደፈ** ግ 1. አላግባብ ተፋ፥ ለጠፈ (ምራቅን):: 2. ተገቢ ባልሆነ መንገድ ለጠፈ፥ ቀባ (ጭቃን፥ ቆሻሻን፥...):: 3.የሚያስቀይም ወይም የሚያስከፋ ነገር ተናገረ::

**ለድፍ** ቅ አፉ እንዳመጣለት ተገቢ ያልሆነ ነገር የሚናገር::

**ተለደፈ** ግ ተለጠፈ፥ ተላከከ::

**ለገለገ** ግ ጠባ፥ መጠመጠ፥ መገመገ::

**ለገመ** ግ 1.አለመጠ፥ ጠመመ:: 2. አቄመ (ቀስል)::

**ልግም** ስ ክፋት፥ ጥመት::

**ልገመኛ** ቅ አልምጥ::

**ለገሰ** ግ ቸረ፥ ሰጠ፥ ናኘ::

**ለጋስ** ቅ ቸር::

**ለጋሽ** ቅ 1. ቸር:: 2. ሰጪ፤ ችሮታ አድራጊ

**ልግስና** ስ ችሮታ::

**ተለገሰ** ግ 1.ችሮታ አገኘ፥ ተቀበለ:: 2. ችሮታ ተገኘ፥ ተሰጠ::

**ለገበ** ግ የተቀደደ ልብስን ጣፈ::

**ለገተ** ግ 1.ደቀነ:: 2. ዘጋ፥ ወተፈ፥ ደፈነ::

**ለገቻ** ስ ፉክክር፥ ውድድር::

***ለገዘገዘ**

**ልግዝግዝ (ለገዘጋዛ)** ቅ ገቸጋታ፥ ነገር የማይቆርጥ::

**ልግዝግዝ አለ** ግ ተልገዘገዘ::

**ተልገዘገዘ** ግ ተንገታገተ፥ ነገር በቶሎ የማይቆርጥ ሆነ::

**አልገዘገዘ** ግ አንገታገተ፥ ነገር በቶሎ አልቆርጥ አለ::

**ለገደ** ግ 1. ወተፈ፥ ደፈነ፥ መረገ:: 2. ዘጋ፥ ገደበ፥ ጋረደ፥ አገደ፥ ከለለ::

***ለገደ**

**ለግድ** ስ ለግጥ፥ ፌዝ::

**ለግደኛ** ቅ አላጋጭ፥ አሿፊ::

**ተላገደ** ግ አሾፈ፥ አላገጠ፥ ተዘባበተ::

***ለገገ**

**ልጋግ** ስ ከአፍ ውስጥ እየተሳበና እየተዝረበረበ የሚወጣ ለሃጭ::

**ልጋጋም** ቅ (ስድብ) 1. ለሃጫም:: 2. (ዘይ.፥ስድብ) ከስታራነት፥ ቆፍጣናነት የሌለው::

**ተላገገ** ግ ተለፋደደ::

**አለገገ** ግ ለሃጩን አዝረበረበ::

***ለገጠ**

**ለግጥ** ስ ፌዝ፥ ቀልድ፥ ቧልት::

**ለግጠኛ** ቅ ፌዘኛ፥ ቀልደኛ፥ ቧልተኛ::

**ልግጫ** ስ ፌዝ፥ ቀልድ፥ ቧልት::

**ተላገጠ** ግ ተቃለለ፥ ተሞኘ::

**አላገጠ** ግ 1.አፌዘ፥ ቀለደ፥ አሾፈ:: 2. አሞኘ፥ አቃለለ::

**አላጋጭ** ቅ አሿፊ፥ የሚያፌዝ::

**ለገጭ** ስ የከብት የታችኛው መንጋጋ::

**ለገጫም** ቅ ግንጭላም፥ አገጩ የረዘመ::

**ለጋ** ቅ 1. ቀንበጥ፥ ለምለም:: 2. ያልበሰለ፥ ጮርቃ:: 3.(ዘይ.) ልጅ እግር፥ ወጣት::

**ለጋ ቅቤ** ስ ያልቆየና ያልበሰለ ወይም ያልከመጠጠ ቅቤ::

**ለጋ ደመና** ስ ቀለል ያለ አዲስ ደመና::

**ለጋ ጎበዝ** ስ ልጅ እግር፥ ወጣት፥ ሶታ::

**ለጋ ጨረቃ** ስ አካሏ ሙሉ በሙሉ የማይታይ ገና አዲስ የወጣች ጨረቃ::

**ለጋ[1]** ግ 1.ሩርን ወይም ጥንግን በእጅ ወርወር

አድርጎ መሬት ሳታርፍ በዱላ መታ፥ ቀላ:: 2. ኳሷን በረዥሙ መታ (የእግር ኳስ):: 3. መታ:: *በዱላ ለጋው::* 4. ገፋ፥ ገፈተረ:: *ከቆምኩበት ለግቶኝ ሄደ::*

**ተላጋ** ግ ተጋጨ፥ ተላተመ::

**አላጋ** ግ አጋጨ፥ አላተመ::

**ለጋ**[2] ግ ዥው አድርጎ ጠጣ::

**ለግላጋ** ቅ ቁመቱ ዘለግ ያለ ወጣት::

**ለጎመ** ግ 1. በበቅሎ ወይም በፈረስ አፍ ውስጥ ልጓም አስገባ:: 2. እንዳይበላ የከብትን አፍ በገመድ ወይም በጠፍር አሰረ፥ ሸበበ:: 3. ጥይት አጎረሰ (ጠመንጃን፥ ሽጉጥን):: 4. ስፌትን (አገልግል፥ ቁና፥ መሶብ፥...) በቆዳ ለበደ፥ ለበጠ፥ ሸፈነ፥ ከፈፈ:: 5. እንዳይናገር አፉን በጨርቅ ጠቀጠቀ::

**ልጉም [አፍ]** ቅ መናገር ሲገባው የማይናገር፥ ሃሳቡን የማይገልፅ፥ ዝምታ የሚያበዛ::

**ልጉም አለ** ግ ዝም አለ፤ አልናገር አለ::

**ልጓም** ስ የኮርቻ በቅሎና ፈረስ በጉዞ ላይ እያሉ እንዳይበሉና እንዳይጠጡ የሚከላከል፥ ፍጥነታቸውንና አቅጣጫቸውን ለመቆጣጠር የሚያስችል በአፋቸው ውስጥ የሚጠለቅ ዛብ ያለው ብረት::

**ልጓም ለቀቀ** 1. ፈረሱ የቻለውን ያህል እንዲጋልብ በልጓም መቆጣጠሩን ተወ:: 2. (ዘይ.) ያለገደብ፥ እንደልቡ ሆነ::

**ልጓም አላላ** ቁጥጥሩን ቀነሰ::

**ልጓም ጣሰ** በልጓም አልገታ አለ::

**ልጉምጉም** ቅ ፈታ አድርጎ የማይናገር::

**ተለጎመ** ግ 1. ስፌት (መሶብ፥ አገልግል፥...) በቆዳ ተለበደ:: 2.(ጠመንጃ፥ ሽጉጥ) ጥይት ጎረሰ:: 3. አልናገር አለ፥ ዝም አለ:: 4. የመናገር ነፃነት አጣ፥ እንዳይናገር ተከለከለ::

**ተልጎመጎመ** ግ ፈታ አድርጎ አልናገር አለ::

**አለጎመ** ግ 1. ዝም አለ፥ አልናገር አለ:: 2-. አላመጠ::

**አልጉም** ቅ 1. ሃሳቡን ግልፅ አድርጎ አፍታቶ የማይናገር:: 2. አልምጥ::

**አልጎመጎመ** ግ 1. መናገር የፈለገውን ነገር ግልፅ ወይም ፈታ አድርጎ አልናገር አለ፤ 2.አጉተመተመ::

**ለጎደ** ግ 1. ለጠፈ፥ ለደፈ (ጭቃን፥ ምራቅን፥ ንፍጥን):: 2. ላከከ (ጥፋትን)::

**ተለጎደ** ግ ተለጠፈ፥ ተለደፈ::

**ለጎጠ** ግ 1. ላላ አድርጎ ወተፈ፥ አገባ:: 2.ጎረሰ፥ አፉ ውስጥ አደረገ (ጡትን፥ ጣትን)::

**ልጓጥ** ስ በጋማ ከብት አፍ ላይ የሚደረግ የእንጨት ልጓም::

**ለጠለጠ** ግ 1. የቅባት እህልን ቅባት እስኪወጣው ድረስ ወቀጠ:: 2. እስኪልም ድረስ ወቅጦ ጠፈጠፈ (ለምሳሌ ትንባሆን):: 3. ደጋግሞ በሃይል መታ፥ ደበደበ::

**ልጥልጥ** ቅ 1. እስኪልም ድረስ ተወቅጦ የተጠፈጠፈ (ኑግ፥ ሰሊጥ፥...):: 2.የኖራ፥ የሰም፥...ጥፍጥፍ:: 3. (ዘይ.) ወዘናው የሚያምር፥ ወዛም፤ በሚገባ የተቀለበ፥ የተመቸው::

**ተለጠለጠ** ግ 1. ወፈረ፥ አማረበት:: 2. በብዛት ተከማቸ፥ ተገጠገጠ፥ ተተከለ (ህዝብ፥ ቤት፥ ድንኳን)::

**አለጠለጠ** ግ ወፈረ፥ ተመቸው::

**ለጠሰ** ግ አስተኛ፥ አጋደመ (ፀጉርን፥ ሰብልን፥ ...)::

**ተለጠሰ** ግ ተኛ፥ ተጋደመ (ፀጉር፥ ሰብል፥ ...)::

**ለጠቀ** ግ 1. ቀጠለ፥ ተከተለ:: 2. (ዘይ.) ለሰቀ፥ ልክክ አለ::

**ልጥቅ አለ** ግ 1- ተለጠቀ፥ ተጣበቀ::2- (ዘይ.) ተስማምቶ፥ ልክክ ብሎ ኖረ::

**ተለጠቀ** ግ 1.ተላከከ፥ ተጣበቀ::

**ተለጣጠቀ** ግ 1.ተጣበቀ፥ ተያያዘ:: 2. ተከታተለ::

**ተላጠቀ** ዝ.ከ.

**አለጣጠቀ** ግ አጣበቀ፥ አያያዘ::

**አላጠቀ** ዝ.ከ.

**ለጠበ** ግ በለጠብ ከደነ::

**ለጠብ(ልጣብ)** ስ መክደኛ::

**ለጠጠ**[1] ግ ሳበ፥ ወጠረ::

**ልጥጥ** ቅ ጅንን፥ ኩሩ::

**ተለጠጠ** ግ 1. ተሳበ፥ ተጎተተ (ለምሳሌ ላስቲክ):: 2. ኩራ፥ ተጀነነ::

**ለጠጠ**[2] ግ 1. ከሙኑ የተረፈውን ድር ቀንሶ አወጣ:: 2. ላጠ፥ ቀረፈ::

**ልጣጭ** ስ 1. ተቀርፎ ወይም ተልጦ የሚነሳ የብርቱካን፥ የሎሚ፥ የሙዝ፥...ልባስ ወይም ሽፋን:: 2. መኑ ከሚችለው በላይ በመሆኑ ተቀንሶ የቀረ ትርፍ ድር::

**ለጠጠ**[3] ግ መታ::

**ለጠጦ** ስ ረዘም ብሎ ቀጠን ያለ በትር::

**ለጠፈ** ግ 1.በግድግዳ፥ በሰሌዳ፥...ላይ አጣበቀ (ስእልን፥ ወረቀትን፥...):: 2. መረገ:: 3. ለደፈ (ምራቅን፥ ንፍጥን፥...):: 4. አመካኘ፥ አላከከ:: *የራሱን ጥፋት በእኔ ላይ ለጠፈ::*

**ለጣፊ** ቅ 1. ነገር ለቃቃሚ፥ አሾክሿኪ:: 2. ራሱን የማይችል፥ ጥግ ፈላጊ፥ በሰው የሚመካ::

**ልጥፍ** ስ ገና ያልተለሰነ የጭቃ ቤት ምርግ::

**ልጥፍ አለ** ግ ተጠጋ፥ ጥብቅ አለ።

**ተለጠፈ** ግ 1. ተላከከ፥ ተጣበቀ። 2. ተጠጋ፥ በጣም ቀረበ። *ግድግዳ ላይ ተለጥፎ ያዳምጥ ነበር።*

**ተለጣፊ** ቅ ራሱን ችሎ ሳይሆን ሌላውን ተጠግቶ የቆመ፥ የተሰራ። *ተለጣፊ ቤት /ተለጣፊ ሱቅ።*

**ለጥ**

**ለጥ አለ** ግ 1. ተጋደመ፥ ለሽ አለ። 2. ለረዥም ሰአት ተኛ፥ እንቅልፍ ወሰደው። 3. እንዲፈፅም የሚጠበቅበትን ተግባር ሳያከናውን ዝም ብሎ ቆየ።

**ለጥ ብሎ እጅ ነሳ** በጣም አጎንብሶ ሰላምታ ሰጠ።

**ለጥ ያለ ሜዳ** አባጣ ጎርባጣ የሌለው፥ ወለል ያለ ሜዳ።

**ለጥ ሰጥ አለ** 1. ያለምንም ተቃውሞ አሜን ብሎ ተገዛ። 2. ስርአት ያዘ።

**ለጥ ሰጥ አደረገ** 1. ያለምንም ተቃውሞ አሜን ብሎ እንዲገዛ አደረገ። 2. ስነ ስርአት እንዲከበር አደረገ።

**ለፈለፈ** ግ 1. ብዙ ተናገረ፥ አወራ፥ ቀባጠረ። 2. ደጋግሞ አሳሰበ፥ ወተወተ። *እኔማ ላይሆንም ብዬ ለፍልፌ ነበር፥ የሚሰማኝ አጣሁ እንጂ።*

**ለፍላፊ** ቅ (ስድብ) ቀባጣሪ፣ ማውራት የማይሰለቸው።

**ተለፋለፈ** ግ 1. በመጯጯህ ተነጋገረ። 2. ተጨቃጨቀ፥ ተነታረከ (በመጯጯህ)።

**አለፋለፈ** ግ አነታረከ፥ አጨቃጨቀ።

**አስለፈለፈ** ግ 1. እንዲናገር፥ ምስጢር እንዲያወጣ አደረገ። 2. አናገረ። *ሳይሰሙኝ ምን አስለፈለፈኝ።*

***ለፈሰፈሰ**

**ልፍስፍስ (ለፈስፋሳ)** ቅ 1. አቅመቢስ፥ ደካማ። 2. ሃሞተ ቢስ።

**ልፍስፍስ አለ** ግ ተልፈሰፈሰ።

**ልፍስፍስ አደረገ** ግ አልፈሰፈሰ።

**ተልፈሰፈሰ** ግ 1. ደከመ፥ አቅም አጣ። 2. ሃሞተ ቢስ ሆነ፥ ወኔ አጣ።

**አልፈሰፈሰ** ግ 1. አዳከመ፥ አቅም አሳጣ። 2. ሃሞተ ቢስ ወይም ወኔ ቢስ አደረገ።

**ለፈተተ** ግ ለዘዘ።

**ልፍትት (ለፍታታ)** ቅ ለዛዛ።

**ለፈደደ** ግ በእርጥበት ምክንያት በቀላሉ አልታረሰ፥ አልወጋ አለ (መሬት)።

**ለፈዳም (ለፈዲያም)** ቅ (ስድብ) ዘብዛባ፥ አነጋገሩ የማይጥም።

**ለፍዳዳ (ለፈደድ)** ቅ (ስድብ) 1.ሲናገር ቃላት የሚጎትት፥ አቀላጥፎ የማይናገር (የህፃናትን ንግግር አይጨምርም)። 2.ጨምላቃ። 3. ነዝናዛ፥ ጨቅጫቃ።

**ተለፋደደ** ግ የማይጥም ነገር ተናገረ፥ ተጨማለቀ።

**ለፈጨቀ** ግ ጨቀየ፥ ተጨማለቀ፡፡

**ለፍጫቃ** ቅ 1. ጨምላቃ። 2. ለፍዳዳ። 3. ነዝናዛ፥ ጨቅጫቃ።

**ልፍጭቅ አለ** ግ ጭምልቅ አለ።

**ተለፋጨቀ** ግ 1. ተጨማለቀ። 2. ተለፋደደ፡ 3. ተነዛነዘ፥ ተጨቃጨቀ።

**አለፋጨቀ** ግ 1. አጨማለቀ። 2- ሲበላ አፋን አጮሀ።

**ለፈፈ** ግ ሰው እንዲሰማ ጮሆ ተናገረ፥ አወጀ።

**ተለፈፈ** ግ ታወጀ፥ ተነገረ።

**ለፋ** ግ 1. ደከመ፥ ጣረ፥ ጋረ፥ ኳተነ፥ ማሰነ። 2.ታሽቶ ወይም ተረግጦ ለሰለሰ፥ ለዘበ፥ ለተተ (ቆዳ)። 3. ለረዥም ጊዜ ከማገልገሉ የተነሳ ተጎዳ፥ አረጀ።

**ለፍቶ መና** 1. ጥሮ ግሮ የማያልፍለት፥ የማይሳካለት። 2. የልፋት፥ የድካም ዋጋ የማይገኝበት።

**ለፍቶ አዳሪ** ስ ጥሮ ግሮ፥ በሚያገኘው የሚኖር፣ ሰርቶ አዳሪ።

**ልፊያ** ስ 1. የቀልድ ትግል ወይም ድብድብ።

**ልፋት** ስ 1.ድካም፥ ጥረት፥ ግረት። 2. ውጤት የሌለው ፍሬቢስ ድካም።

**ልፍ** ቅ የተለፋ (ቆዳ)።

**ተለፋ** ግ ለፋ፥ ለሰለሰ፥ ለዘበ (ቆዳ)።

**ተላፋ** ግ የቀልድ ታገለ ወይም ተደባደበ።

**አለፋ** ግ 1. አደከመ፥ አኳተነ፥ አማሰነ። 2. አለሰለሰ፥ አለዘበ (ለምሳሌ ቆዳን)። 3. ብዙ ጊዜ ተገለገለበት (ልብስን፥ ጫማን፥...)።

**አልፊ** ቅ አድካሚ።

**አስለፋ** ግ አደከመ።

**ለፎ** ስ ፈረሰኛ ያልሆነ የጥንት እግረኛ ወታደር።

**ሉ** የ"ለ" ፊደል ካእብ ዘር።

**ሉህ (ሉክ)** ስ 1. ያልተፃፈበት ሌጣ ወረቀት፥ ብራና። 2-. የተላገ ወይም የለዘበ ሳንቃ፥ ሰሌዳ።



**ሉል** ስ 1. ብልጭልጭና ለስላሳ የሆነ ከባህር የሚገኝ የከበረ ድንጋይ፣ የእንቁ አይነት። 2. ንጉስ

ሉል 3ኛ ፍቺ

በሚነግስ ጊዜ በእጁ የሚይዘው ክብ ሆኖ የተሰራ የአለም ተምሳሌት:: 3. በኳስ ቅርፅ የተሰራ የአለም ካርታ::

**ሉቃሳም (ልቋሳም)** ቅ (ስድብ) 1. ችጋራም 2. ደካማ፥ ልፍስፍስ::

**ሉባ** ቅ ቀልጣፋ፥ ንቁ፥ ጎበዝ::

**ሉባንጃ (ልባንጃ)** ስ ጥሩ ሽታ ያለው የእጣን አይነት::

**ሉተራን** ስ ከፕሮቴስታንት ሃይማኖት አንዱ የሆነውና በማርቲን ሉተር ስም የተሰየመው ሃይማኖት ወይም የሃይማኖቱ ተከታይ::

**ሉአላዊ** ቅ ነፃ የሆነ፥ ምሉእ ስልጣን ያለው (ሃገር፥ መንግሥት)::

**ሉአላዊነት** ስ ምሉእ የሆነ መብት፥ ነፃነትና የስልጣን የበላይነት::

**ሉካንዳ (ልኳንዳ)** ስ የስጋ መሸጫ ቤት::

**ሉክ** ስ የ"**ሉህ**"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

**ሉጢ** ቅ (ስድብ) 1. አንድ ቦታ ረግቶ የማይቀመጥ፥ ከውካዋ:: 2. ነገር አመላላሽ::

**ሉጫ (ላሁጫ)** ስ ከርዳዳ ያልሆነ፥ ለስላሳ ፀጉር::

**ሊ** የ"**ለ**" ፊደል ሳልስ ዘር`

**ሊ _** "**ል-**"ን ተመ.

**ሊሎ** ስ 1. የአሞራ አይነት:: 2. ከወረቀት ወይም ከስስ ጨርቅ የሚሰራና ከጫፉ ላይ በረዥም ክር አስረው በመያዝ ወደ ሰማይ ሲለቁት የሚንሳፈፍ የልጆች መጫወቻ::

**ሊሬ** ስ የጣሊያን ገንዘብ ስም::

**ሊስት** ስ የሰው፥ የእቃ፥...ስም ዝርዝር ወይም ዝርዝሩ የተፃፈበት ወረቀት::

**ሊስትሮ** ስ 1. ጫማ ጠራጊ:: 2. ጫማ ጠራጊ ቀለምና ቡርሽ የሚያስቀምጥበትና ጫማ አስጠራጊውም እግሩን የሚያሳርፍበት ትንሽ ሳጥን::

**ሊሻን** "**ኒሻን**"ን ተመ.

**ሊሾ** ስ በአሸዋና በሲሚንቶ በልሙጡ የተለቀለቀ ወለል ወይም ግድግዳ::

**ሊቅ** (ብ.ቁ.**ሊቃውንት**) ስ 1. በትምህርት የበሰለ፥ የተራቀቀ፥ ምሁር፥ አዋቂ:: 2. እንደ ሃይማኖተ አበው፥ አፈወርቅ፥ ቄርሎስ፥ ኤጲፋንዮስ፥ ቅዳሴ፥ አቡሻህር የመሳሰሉ ሃይማኖት ነክ መፃህፍት የሚጠሩበት ስም::

**ከሊቅ እስከ ደቂቅ** ከትልቅ እስከ ትንሽ፥ ከልጅ እስከ አዋቂ፥ ሁሉም ሰው::

**ሊቀ ሊቃውንት** ቅ ከሊቃውንት በላይ የላቀ እውቀት ያለው::

**ሊቀ መላእክት** ቅ የመላእክት አለቃ የሆነ::

**ሊቀመንበር** ስ 1. የአንድ ኮሚቴ፥ማህበር፥ ቦርድ፥...መሪ:: 2. የአንድ ጉባኤ ወይም ስብሰባ መሪ::

**ሊቀመኳስ** ስ እንደ ንጉስ የሚለብስና በንጉስ አጠገብ የሚቆም የንጉስ ባለሟል::

**ሊቀ አርድእት** ስ በቤተ ክህነት ትምህርት ቤት የተማሪዎች አለቃ::

**ሊቀ ካህናት** ስ የካህናት አለቃ::

**ሊቀ ዲያቆን (ሊቀ ዲያቆናት)** ስ የዲያቆናት አለቃ::

**ሊቀ ጉባኤ** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) የጉባኤ፥ የስብሰባ መሪ፥ አለቃ::

**ሊቀ ጠበብት** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) በቤተ ክርስቲያን ከአለቃ በታች ያለ ማእረግ::

**ሊቀ ጳጳሳት** (ብ.ቁ.**ሊቃነ ጳጳሳት**) ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ማእረጉ ከጳጳሳት በላይ ከፓትርያርክ በታች የሆነ መንፈሳዊ አባት::

**ሊባ** ስ በሰሜንና በምእራብ መካከል ያለ የአለም ማእዘን አቅጣጫ::(በተጨማሪ ማእዘን ስር ተመ)::

**ሊብሬ** ስ የመኪና ባለቤትነት መታወቂያ ደብተር::

**ሊትር** ስ 1. አንድ ኪሎ ግራም የሚሆን ውሃ የሚይዘውን ያህል ቦታ ሊይዝ የሚችል ፈሳሽ:: 2.ከላይ የተጠቀሰው የፈሳሽ መጠን መለኪያ::

**ሊትሮ** ስ አንድ ሊትር ፈሳሽ ሊይዝ የሚችል ጠርሙስ::

**ሊቼንሳ** ስ የንግድ ወይም የመንጃ ፈቃድ::

**ሊጋባ** ስ ወደ ቤተ መንግስት የሚገቡና ከቤተ መንግስት የሚወጡ ሰዎችን እንዲቆጣጠር ይሾም የነበረ የአጋፋሪዎችና የከልካዮች አለቃ መጠሪያ::

**ሊጥ** ስ 1.በውሃ የራሰና የተለወሰ ዱቄት፥ ቡኮ:: 2. በደንብ ያልበሰለ (ለምሳሌ ዳቦ)::

**ሊጡ ተነሳ** ኩፍ አለ፥ ቦካ::

**ሊጦን** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) በቤተክርስቲያን ቄሶች በየእለቱ ተራ አስገብተው የሚያዜሙትና የሚደግሙት የምስጋና ፀሎት::

**ሊፍት** ስ ዘመናዊ በሆኑና ብዙ ፎቅ ባላቸው ህንፃዎች ላይ ሰዎች ለመውጣትና ለመውረድ የሚገለገሉበት በኤሌክትሪክ የሚሰራ መሳሪያ፤ አሳንሱር::

**ሊፕስቲክ** ስ ሴቶች ከንፈራቸውን የሚቀቡት ቀለም::

**ላ** የ "**ለ**" ፊደል ራብእ ዘር::

**ላ** - "**ል-**"ን ተመ.

**ላሁጫ** "**ሉጫ**"ን ተመ.

**ላህይ** ስ 1. ውበት፥ ደምግባት፥ ወዘና። 2. የድምፅ ቃና።

**ላሊበላ** ስ 1. ሳይነጋ በሌሊት በየሰዉ ቤት እየዞረ ወይም ተዝካርና ሰርግ ባለበት እየሄደ በዜማና በግጥም የሚለምን፣ ሃሚና፣ ኣባጎንዳ፣ ኣባውዴ፣ ደብራሆም። 2. (ዘይ፥ስድብ) ለፍላፊ፥ ምላሰኛ።

**ላላ** ግ 1. የታሰረው ወይም ጠብቆ የነበረው እንደመርገብ፥ እንደመፈታት ኣለ። 2. ቀጠን ኣለ (ሊጥ)። 3. ከመብሰል ወይም ከመበስበስ የተነሳ ሉክሉክ፥ ትምክ ትምክ ኣለ። 4. ደከመ፥ ዛለ፥ ሃይልና ጥንካሬ ኣጣ። 5. ለቀቅ፥ ቀለል ኣለ (ቁጥጥር፥ ህግ፥ እስር፥...)።

**ሳሳቴ** ስ ለስላሳ የሆነ ትንሽ ዳቦ፥ ህብስት።

**ልል** ቅ 1. ያልጠበቀ፥ የረገበ። 2. በኣካል ወይም በባህርይ ጠንካራ ያልሆነ።

**ኣሳላ** ግ 1. ጠብቆ የነበረውን ወይም፥ የተወጠረውን ለቀቅ ኣደረገ፥ ኣረገበ። 2. ቁጥጥሩን ኣቀለለ፥ ለቀቅ ኣደረገ።

**ላመ** ግ 1.የተፈጨው ወይም የተወቀጠው ወይም የተደቆሰው፥... በጣም ደቀቀ። 2. ለረዥም ጊዜ ከመለበሱ የተነሳ ሳሳ፥ ብን ኣለ።

**ልም** ቅ 1.የላመ፥ የደቀቀ። 2. ልስልስ። 3.ጥንካሬ የሌለው (ሰውነት)።

**ኣላመ** ግ በመውቀጥ ወይም በመፍጨት ወይም በመሰለቅ፥...በጣም ኣደቀቀ።

**ላመል** **"ኣመል"** ስር **"ለኣመል"**ን ተመ.

***ላመጠ**

**ልማጭ** ስ ታኝኮ የተተፋ የኣገዳ ምጣጭ፥ እኛኪ፥ ብላቶ።

**ኣላመጠ** ግ 1. የጎረሰውን (ምግብ) ኣኘከ። 2. እንደመቆርጠም እያደረገ ኣመመ። 3. (ዘይ.) ሰውን በክፉ ኣነሳ፣ አማ።

**ላመ ፈጅ** ስ ብዙ ስጋ መያዝ የሚችል ትልቅ ድስት፥ ሰታቴ፣ መካከለኛ ጎላ።

**ላሜዳ** **"ላይዳ"**ን ተመ.

**ላም** ስ 1. መውለድ የጀመረች የቀንድ ከብት።(ስእሉን የቤት እንስሳ ስር ተመ.)። 2. (ዘይ.) ገር፥ የዋህ። 3.(ስድብ) ሞኝ።

**ላም ኣለኝ በሰማይ** የማይገኝ ነገር፣ በሩቅ፥ በምኞት ብቻ ያለ።

**የላም ልጅ** ስ ወተት፥ እርጎ፥ ኣይብ።

**የላም ጨው** ስ 1.ላም በምትታለብበት ጊዜ ሳታስቸግር ወተት እንድትሰጥ የሚያልሷት ኣሞሌ ጨው፣ መላሾ። 2. ሲበሉት ጨው ጨው የሚል በፍሬው ላይ እሾህ ያለበት ቀላ ያለ የእፅዋት ኣይነት።

**ላም ላጊ** ስ መጠኑ ከድመት ኣነስ የሚልና ላም የሚጠባ ኣውሬ።

**ላም ኣንገት** ፈረ።

**ላምባ** ስ ለኩራዝ የሚያገለግል ነዳጅ፥ ጋዝ ፥ ናፍታ።

**ላምባዲና** ስ የእጅ ባትሪ።

**ላምዛን** ስ ኣነባበሮ።

**ላምፉ** **(ላንፉ)** ስ 1. የመቃ፥ የኣገዳ፥ የበቆሎ፥...ቅጠል። 2. (ዘይ.፥ ስድብ) ኣቅመቢስ፥ ደካማ።

**ላሰ** ግ 1. በምላሱ ጠረገ፥ ኣበሰ። 2. የሚበላን ወይም የሚጠጣን ነገር በምላሱ ወሰደ፥ ተመገበ። *ድመቷ ወተቱን ላሰችው።* 3. ጥርግ ኣደረገ፥ ኣሟጠጠ፥ ጨረሰ (ስራን፥ መብልን፥...)። 4. ፈጀ፥ ኣቃጠለ፥ ለመጠጠ (እሳት)። 5. ሰረቀ፥ መነተፈ። *ገንዘቤን ከኪሴ ላሰኝ።*

***መላሾ*** ስ 1. ከብት የሚልሰው ኣሞሌ ጨው። 2. ጉቦ ወይም መማለጃ።

**ምላስ** ስ 1.ለመናገር፥ ለመብላት፥ ለመቅመስ፥ ለመላስ የሚያገለግል በኣፍ ውስጥ የሚገኝ የሰውነት ክፍል።(ስእሉን ኣፍ ስር ተመ.)። 2. በቅርፁ፥ በእንቅስቃሴው፥... ምላስን የሚመስል ነገር (ለምሳሌ የሚዛን ክብደት ጠቋሚ፥ የእሳት ነበልባል)። 3. (ዘይ.) ልፍለፋ። *ሰውየው ምላስ ያበዛል።*

**ምላሱ ጥቁር ነው** የተናገረው መጥፎ ትንቢት ወይም እርግማን ይደርሳል።

**ምላሱን ኣስረዘመ** ለነገር ቸኮለ፥ ቀደም ቀደም ኣለ፥ ኣፉን ኣሞጠሞጠ፥ ብዙ ተናገረ።

**ምላሱን ኣውለበለበ** ብዙ ለፈለፈ፥ተናገረ።

**ምላስ ለቀቀበት** ልፍለፋ ኣበዛ።

**ምላስ ዱልዱም** ቅ ኣንደበቱ ፈታ ብሎ ቶሎ ቶሎ መናገር የማይችል።

**ምላሰኛ** **(ምላሳም)** ቅ 1.ለፍላፊ፥ ተናጋሪ፥ ቀባጣሪ። 2. ነገረኛ፡

**ምላስና ሰንበር** ስ ከላም ወይም ከበሬ ምላስና ሰንበር የሚዘጋጅ ምግብ።

**ተላላሰ** ግ 1. የፍቅር፥ የመዋደድ መሳሳም ተሳሳመ። 2. ባከነ፥ ተባነነ (ዱቄት) 3. (ዘይ.) ከልብ ያልመነጨ ምስጋና እርስ በርስ ተመሰጋገነ፥ ተወዳደሰ።

**ኣላሰ** ግ 1. ኣሞሌ ጨውን ለከብት መገበ። 2. በጥፌ ኣሎለ፥ ኣጠናፈረ። 3. ጠጅ ወይም ጠላ ውስጥ ማርን፥ ቅራሪ ወይም ጠላ ውስጥ ድፍድፍን ጨመረ። 4. (ዘይ.) ትንሽ ገንዘብ ሰጠ። *ስጥቅመ ትንሽ ኣልሶኛል።*

**ማላሻ** ስ በበሰለ ወይም በቀጠነ ጠጅ ወይም ጠላ ውስጥ የሚጨመር ማር ወይም ድፍድፍ።

**ላሰሰ** ግ ኣረምን፥ እህልን፥ ሳርን፥...በብዛት

ጨርሶ ነቀለ።

**ልሳሽ** ስ በአንድ ክረምት አንድ ማሳ ላይ ተዘርቶ የነበረው ሰብል እንደ ታጨደ ብሩን እየነቀሉ ወዲያው የሚዘሩት የጓያ ወይም የሽምብራ ዘር።

**ላስቲክ** ስ 1. ሲስቡት የሚለጠጥና ሲለቁት የቀድሞ ቅርፁን የሚይዝ ጎማነት ያለው ነገር። 2. እንደ ጨርቅ በስሱ የተዘጋጀና ለጠረጴዛ ልብስነት፥ ለእቃ መያዣ፥... የሚያገለግል ፕላስቲክ። 3. የተለያዩ ነገሮችን (ብር፥ የተጠቀለለ ነገር፥...) አስሮ ለመያዝ የሚያገለግል ቅርፁ ክብ የሆነ ተለጣጭ ቀጭን ጎማ።

**ላስቲክ ጫማ** ስ ከጎማ ወይም ፕላስቲክነት ካለው ነገር የሚሰራ ጫማ።

**ላሸ** ግ 1. አልይዝ አለ፥ ላላ፥ ሟለጠ። 2. ተከላተፈ፥ ተሳሰረ (አንደበት)።

**ላሸቀ** ግ 1. ከመተሻሸት፥ ከመፈጋፈግ የተነሳ ለፋ፥ ለሰለሰ (ቆዳ)። 2. ላላ፥ ጥብቀት አጣ። 3. ሟለጠ ለምሳሌ ወፍጮ፥...። 4.በሰበሰ፥ ተጨማለቀ። 5. ከነበረው ደረጃ ወረደ፥ ዝቅ አለ (በአስተሳሰብ፥ በችሎታ)።

**ላሽ** ስ ፀጉርን የሚመልጥ በሽታ።

**ላቀ** ግ ከፍ አለ፥ በለጠ።

**ላቂያ** ስ ብልጫ።

**ይልቅ(ይልቅስ፥ይልቁንስ፥ ይልቁንም)** ተው.ግ. በይበልጥ። *ትምህርቱን ከማቋረጥ ይልቅ ቢቀጥል ይሻለዋል/በቃል ከተነገረ ይልቅ በፅሁፍ የሰፈረ ነዋሪነት አለው/ እሱ ችኩል ነው ይልቅስ እሷ አስተዋይ ነች።/ ይልቁንስ እሱ ቢመጣ ጥሩ ነበር / ችግሩ አልተቃለለም ይልቁንም እየተባባሰ ሄደ።*

**ላቅ ያለ(የላቀ)** ቅ 1.ከፍ ያለ። *ላቅ ያለ ገንዘብ አገኘ።* 2. የሞቀ፥ የደመቀ።*ላቅ ያለ አቀባበል ተደረገላቸው።*

**አላቀ** ግ 1. ከፍ አደረገ። 2. አስበለጠ። *ከኔ እሱን አልቃ ወደ እሱ ሄደች።*

**ላቆጠ** ግ 1. በካ፥ ተለወሰ። 2. ተጨማለቀ፥ ጨቀየ።

**ልቁጥ** ቅ የተለወሰ፥ የተበካ።

**ልቁጥ በርበሬ** ስ ተፈጭቶ በውሃ የታሸ ወይም የተለወሰ በርበሬ፣ ድልህ።

**አላቆጠ** ግ 1. ለወሰ፥ አቦካ። 2. አጨማለቀ።

***ላበ**

**ላብ (ላበት)** ስ ከመሮጥ፥ ብዙ ከመስራት፥ ከሙቀት፥ ከህመም፥... የተነሳ ከሰውነት ቆዳ ውስጥ የሚወጣ ፈሳሽ።

**ላብ ላብ አለው** የፍርሃት፥ የጭንቀት ስሜት ተሰማው።

**ላብ አጠመቀው** ከድንጋጤ፥ ከድካም፥... የተነሳ በጣም አላበው።

**ላብ አደር** ስ የምርት መገልገያ መሳሪያዎች ባለቤት ያልሆነ፥ ለህልውናውም ሲል የስራ ሃይሉን ለካፒታሊስቱ በመሸጥ በዘመናዊ ፋብሪካዎችና ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ተቀጥሮ በሚያገኘው ምንዳ የሚተዳደር ሰራተኛ፣ ወዛደር።

**ላቦት(ላበት)** ስ ከፈሳሽ ወይም እርጥበት ካለው ነገር ላይ በሙቀት ምክንያት የሚነሳ ተን፥ እንፋሎት።

**አላበ** ግ 1. ከሙቀት፥ ከድንጋጤ፥...የተነሳ ከሰውነት ላብ ወጣ። 2. ከድንጋጤ፥ ከጭንቀት የተነሳ የፍርሃት ስሜት ተሰማ፣ ፍርሃት ፍርሃት አለ።

**ላባ¹** ስ በዶሮ፥ በአሞራ፥ በወፍ፥...ቆዳ ላይ የሚበቅል እንደ ፀጉር ያለ የአካል ሽፋን።



ላባ

**ላባ ቀረሽ** ቅ ጨርሶ ሊያብድ ትንሽ የቀረው (ሰው)።

**ላባ ኳስ** ስ (ስፖ.) ክብ በሆነ ቡሽ ላይ የተሰካኩ ላባዎች ያሉት የባድሚንተን መጫወቻ።



ላባ ኳስ

**ላባ²** ስ ጠላትን ወይም ሌባን ለመከላከል በግንብ ወይም በካብ አጥር ላይ የሚተከል ሹል እንጨት ወይም ብረት ወይም የጠርሙስ ስባሪ።

**ላቦራቶሪ** ስ 1.ደም፥ ሽንት፥ አይነምድር፥ ... የሚመረመርበት ክፍል ወይም ሙከራዎች የሚካሄዱበት ስፍራ፣ ቤተ ሙከራ።

**ላቦት** "*ላበ" ስር ተመ.

**ላተነ** ግ እየተማሰለ ተዋሃደ፣ ተገነፈ።

**አላተነ** ግ እያማሰለ አዋሃደ፣ አገነፈ።

**ላት¹** ስ 1. በተፈጥሮው ስብ የሆነ የበግ ጅራት 2. የካራ ወይም የጎራዴ እጀታ።

**ላት²** ስ ጥራጥሬን ለመያዝ ወይም ለመለካት የሚያስችል ከመዳፍ በላይ ያለ መሃል እጅ።

*ሳንድ ላት ባቀላ::*

**-ላት** "-ለት"ን ተመ.

**-ላቸው** ዝ.ከ.

**-ላችሁ** ዝ.ከ.

**ላንሲታ(ላንሴታ)** ስ የከብደትን ልክ ወይም መጠን የሚያሳይ የሚዛን ምላስ፥ ውልብልቢት::(ስእሉን ሚዛን ስር ተመ.)::

**ላንቁሶ** ስ 1. ልጡ ሲላጥ ዝልግልግና ማላጋ የሆነ፥ እየተሽነሸነም ለአጥርና ለግድግዳ መማገሪያ የሚያገለግል ረዥምና ወፍራም ሃረግ:: 2. ሃይልና ጥንካሬ የሌለው፥ አቅመቢስ ሰው::

**ላንቃ** ስ በመሃል ምላስ ትይዩ ያለው የአፍ ውስጥ የላይኛው ክፍል፥ ጣሪያ::(ስእሉን አፍ ስር ተመ.)::

**ላንቃ ካባ** "ካባ ላንቃ"ን ተመ.

**ላንፋ** "ላምፋ"ን ተመ.

**ላእላይ**

**ላእላይ መዋቅር** ስ በማርክሳዊ ሌኒናዊ ፍልስፍና አመለካከት መሰረት፥ በህብረተሰብ ውስጥ በሚገኙ የኢኮኖሚ ግንኙነቶች ላይ ተመስርተው፥ የህብረተሰቡን የፖለቲካ፥ የህግ፥ የሃይማኖት፥ የፍልስፍና፥... ንቃተ ህሊና የሚያንፀባርቁ ሃሳቦች፥ ድርጅቶችና ተቋሞች::

**ላከ** ግ 1.እቃን፥ መልእክትን፥...በሰው ወይም በሌላ ነገር ሰደደ፥ አስተላለፈ፥ አቀበለ:: 2. መልእክት እንዲያደርስለት ወይም ጉዳዩን እንዲሞላለት አንዱ ሰው ሌላውን ሰው እንዲሄድ አደረገ:: 3. ሳያኝክ ወይም ሳያላምጥ ዋጠ::

**ላኪ** ስ 1.ሸቀጥን ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ነጋዴ ወይም ድርጅት:: 2. የደብዳቤው ወይም የመልእክቱ ባለቤት:: *በደብዳቤው ላይ የላኪው ስም አልተፃፈም::*

**ልኡካን** (ነጠ.ቁ.**ልኡክ**) በፊደል ተራው ተመ.

**መልአክ** በፊደል ተራው ተመ.

**መልእክት (መልክት፥ መላክት)** ስ በደብዳቤ፥ በቃል፥... ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው የሚላክ ነገር፥ ጉዳይ::

**መልእክተኛ (መላክተኛ)** ስ አንድን መልእክት ለማድረስ ወይም አንድን ጉዳይ ለማስፈፀም ወይም ለመፈፀም የሚላክ ሰው::

**ተላከ** ግ 1. መልእክት ለማድረስ፥ ጉዳይ ለመፈፀም ወይም ለማስፈፀም ታዞ ሄደ:: 2. ተሰደደ፥ እንዲሄድ ተደረገ (መልእክት፥እቃ..)::

**ተላከበት** ግ መልእክት እንዲነገረው፥ እንዲደርሰው ተደረገ::

**ተልእኮ** በፊደል ተራው ተመ.

**ተላላከ** ግ1.ወደ ተለያዩ ቦታዎች እየተላከ መልእክት አደረሰ፥ የታዘዘውን ፈፀመ:: 2. ደብዳቤ ተፃፃፈ፤ በደብዳቤ ወይም በሰው አማካይነት ሃሳብ ተለዋወጠ::

**የመላላክ ትምህርት** "የተልእኮ ትምህርት"ን ተመ.

**ተላላኪ** ስ በመስሪያ ቤት ውስጥ መልእክት የማድረስን፥ የመላላክን ስራ የሚሰራ ሰራተኛ::

**ላከከ (ለከከ)** ግ 1. ቀባ፥ ለጠፈ:: 2. አጣበቀ:: 3. በሌላ አመካኘ፥ አሳበበ (ጥፋትን):: 4. አጋባ፥ አስተላለፈ (በሽታን)::

**ልክክ አለ** ግ 1. ልክ መጣ፥ በትክክል ገጠመ:: 2. ተጠጋ፥ ተጣበቀ:: 3. ተስማማ፥ ለመደ፥ አብሮ ኖረ::

**ልክክ አደረገ** ግ በደንብ አድርጎ፥ በሚገባ ተመገበ:: *ምሳውን ልክክ አደረገ::*

**ተላከከ** ግ 1. ተጣበቀ፥ አልለቅ አለ:: 2. ተመካኘ፥ ተሳበበ:: 3. ተጠጋ፥ አልለይ አለ::

**አላከከ** ግ አመካኘ፥ አሳበበ::

***ላወሰ**

**ላወስ አለ** ግ ተላወሰ::

**ተላወሰ** ግ 1. ተንቀሳቀሰ፥ ተነቃነቀ:: 2. ወዲያ ወዲህ አለ፥ ሄደ::

**አላወሰ** ግ አንቀሳቀሰ፥ አነቃነቀ::

**አያላውስም** 1.አያንቀሳቅስም፥ አያነቃንቅም:: 2. ጊዜ፥ ፋታ አይሰጥም::

**ላውንድሪ** ስ የልብስ ንፅህና መስጫ ድርጅት ወይም መሳሪያ::

**ላዙና** ስ በአንዳንድ የቀንድ ከብቶች የሃሞት ከረጢት ውስጥ የሚገኝ ወርቃማ መልክ ያለው ጠጠር::

**ላዛ** ቅ ለስላሳ፥ ሉጫ (ፀጉር)::

**ላዛኛ** ስ ጠፍጣፋ ከሆነ ፓስታ የሚዘጋጅ የምግብ አይነት::

**ላይ** መዋ. 1. ከአካባቢው ከፍታማ የሆነ ቦታ:: *የስራ ሳስኪያጁ ቢሮ የሚገኘው ላይ ነው::* 2. የአንድ ነገር ውጫዊ አካል፥ ገፅታ፥ ክፍል:: *የውስጡን እንጀ እንጂ ላዩስ ጥሩ ነው::* 3. የአንድ ነገር አካል አናታዊ ገፅታ፥ ክፍል:: *መፅሃፉ ጠረጴዛው ላይ ተቀምጧል::* 4. በአንድ አካል ላይ ወይም ውስጥ መጣበቅን፥ መለጠፍን፥ መታሰርን፥ መገኘትን፥... የሚያመለክት:: *ግድግዳው ላይ ያለው ስእል /ልብሱ ላይ ቆሻሻ አለ/* እጁ ላይ ያለው ሰአት */ወረቀት ላይ ፃፈ/* ፊቱ ላይ ብጉር ወጣበት */አውቶቡስ ላይ ተሳፈረ::* 5. አንድ ነገር የሚካሄድበት ጊዜ ወይም ሰአት:: *በርጉ ላይ ተገኝቷል/ስብሰባ ላይ አልነበረም /ስራ ላይ ቀልድ የለም/ በመሄድ ላይ ነው::* 6. የተወሰነ ቦታን፥ ጊዜን የሚጠቁም:: *መንገድ ላይ*

*ይጫወታሉ/ሁለት ስለት ላይ እመጣለሁ/ ሰኔ ላይ ይዘንባል*:: 7. አንድን ነገር አስመልክቶ ለመናገር ወይም አቅጣጫን፥ አንፃርን፥ አኳያን ለመጠቆም የሚያገለግል:: *ጠላት ላይ ዘመተ /እዚህ ላይ አንድ ችግር አለ/በእሱ ላይ እምነት አለኝ /ሰውየው ላይ ሳቀበት/ በግዚ ላይ ግብር ተጨመረ /ትንባሆ ላይ ቀረጥ ተጨመረ*:: 8. አንድ ነገር ከስንት ቦታ እንደተከፈለ የሚያሳይ:: *ዳቦውን አራት ላይ ከፈለው::*

**ላይ ላዩን** 1. አፋፍ አፋፉን፥ *ጋራ ጋራውን*:: 2. ጠለቅ ሳይል፥ ነካ ነካ፥ ገረፍ ገረፍ፥ ውጪ ውጪውን:: 3. ከአንገት በላይ፥ ለይምሰል:: *ላይ ላዩን ይስቃል::*

**ላይ ታች አለ** 1.ሽቅብ ቁልቁል አለ፥ ወጣ ወረደ፥ ለፋ:: 2.ዘባበደ::

**ላይ ታች አለው** ትውከትና ተቅማጥ አጣደፈው::

**ላይና ታች ረገጠ** 1. ተወላገደ፥ መስመሩን ለቀቀ:: 2. ዘባበደ፥ ቀባጠረ::

**በላዩ ላይ** በተደራቢ:: *በላዩ ላይ ሌላ ወዳጅ ያዘች::*

**በላይ** በማስበለጥ:: *ከሁሉም በላይ እሱን እወደዋለሁ::*

**በላይ በላዩ** ወዲያው ወዲያው፥ ያለማቋረጥ፥ በአናት በአናቱ:: *በላይ በላዩ ወለደች/ ጠጁን በላይ በላዩ ማለት::*

**ከላይ እስከ ታች** ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ፤ ከትንሽ እስከ ትልቅ፤ በጠቅላላው፥ በሙሉ::

**ከላይ እንደተመለከተው** በፊት፥ ቀደም ብሎ እንደተመለከተው::

**ከላይ ከላዩ** 1. ከአፍ ካፉ፥ ሳይደራረብ:: 2. ዋና ዋናውን፥ ከአናት ከአናቱ ::

**ከላይ የወረደ** ከእግዚአብሄር የመጣ፥ የታዘዘ (ብዙውን ጊዜ ለክፉ ነገር)::

**ወደ ላይ አለው** አስታወከው፥ አስመለሰው::

**የበላይ** አለቃ፥ ሹም፥ ባለስልጣን::

**የበላይ ባለስልጣን** ዝ.ከ.

**ላይ ቤት** ስ 1. ገነት፥ መንግስተ ሰማያት:: 2. (ቤ.ክህ.) በጎንደር የሚገኝ የአቋቋም፥ የትርጓሜ መፃህፍት ትምህርት ቤት ወይም የትምህርት ጉባኤ፤ በአቋቋም በዜማና በመፃህፍት አተረጓጎም ከታች ቤት የሚለይበት የራሱ የሆነ ስልትና ባህል ያለው የትምህርት ተቋም::

**ላይኛው** ቅ በላይ በኩል ያለው::

**የላይኛው ጌታ** ስ እግዚአብሄር::

**ላይተር** ስ ሲጋራ ለመለኮስ ወይም እሳት ለማያያዝ የሚያገለግል፥ ጋዝ እየተሞላ እሳት መፍጠር የሚችል መሣሪያ፤ መለኮሻ::

**ላይዳ (ላሜዳ)** ስ እንደ አካፋ ሆኖ ከእንጨት የተሰራና በውድማ ላይ በነፋስ አማካይነት ፍሬን ከእብቅና ከገለባ ለመለየት የሚያገለግል የግብርና መሳሪያ::




ላይዳ

**ላይዳ አለ** አውድማ ላይ የተወቃን እህል በላይዳ ወደ ላይ በመበተንና ለነፋስ በመስጠት ፍሬን ከገለባ ለየ::

**ላዳን** ስ ከስንደዶ ወይም ከሸንበቆ፥... የሚሰራ የእህል መስፈሪያ፥ መለኪያ (መጠኑ እንደአካባቢው ይለያያል)::

**ላገ**[1] ግ ትክክል እንዲሆን፥ እንዲለሰልስ፥ እንዲለዝብ አድርጎ ፋቀ፥ ጠረበ (እንጨትን)::

**መላጊያ** ስ ለእንጨት መፋቂያ፥ ማስተካከያ የሚያገለግል በመካከሉ ስል ብረት (ምላጭ) ያለበት የአናጢዎች መሳሪያ::



መላጊያ

**ላገ**[2] ግ 1. ጠባ፥ መገመገ፥ መጠመጠ:: 2. አለበ:: 3. ራበ፥ ሞረሞረ:: *ራብ ይዞ ይልገኛል::*

**ላገ**[3] ግ አማሰለ፥አዋሃደ፥ አስማማ (ለገንፎ)::

**ላጊ** ስ የጤፍን ፍሬ ከነገለባው በልቶ አገዳውን ባዶ የሚያስቀር ተባይ::

**ላጠ**[1] ግ 1.የአንድን አካል ቆዳ፥ ሽፋን፥...አነሳ፥ መለጠ፥ ገፈፈ፥ ገሸለጠ:: 2. ፈጀ፥ አቃጠለ፥ ለመጠጠ:: 3. ገረፈ፥ መታ:: 4. አሽሟጠጠ፥ ሸረደደ፥ አማ፥ ስም አጠፋ:: *በነገር ላጠው::*

**ልጣጭ** ስ የሽንኩርት፥ የብርቱካን፥ የሎሚ፥...ቅርፊት ወይም ሽፋን::

**ልጥ** ስ በዛፍ፥ በተክል፥... ቅርፊት ውስጥ የሚገኝ የእንጨት ሽፋን::

**ልጠ** ስ የተፈተገ ስንዴ እብቅ፥ ገለባ፥ አሰር::

**ልጠ ጉርዶ** ስ ከተፈተገ ስንዴ የሚወጣ አሰርና እንቅጥቃጭ::

**ልጠ ጉርዶ አወጣ** ፈተገ፥ አነፈሰ፥ አበጠረ::

**ተላጠ** ግ 1. ተመለጠ፥ ተገፈፈ፥ ተቀረፈ። 2. ተገረፈ፥ ተመታ።

**ተላላጠ** ግ 1.ተገሸላለጠ፥ ተገጣጠበ፥ በጣም ተላጠ። 2. ፊት ለፊት ተሰዳደበ ወይም በአሽሙር ተሸራደደ።

**መላላጫ** ስ ከዶሮ ክንፍ በታች ከግራና ቀኝ የሚወጣ የስጋ ብልት።(ስእሉን የዶሮ ብልት ስር ተመ.)።

**ላጠ**2 ግ 1.በፍጥነት አወጣ፥ መዘዘ (ሽጉጥን፥ ጎራዴን፥ ገንዘብን፥...)። 2. ሰረቀ። *ሌባ ገንዘቡን ከኪሱ ላጠው።*

**ላጥ ላጥ አለ** ግ ፈጠን ፈጠን ብሎ ሄደ፤ መንቀር መንቀር አለ።

**ላጥ አደረገ** ግ 1.በፍጥነት አከናወነ፥ ፈፀመ። 2. ዘረጥ አደረገ (ፈስን)።

**ላጥ ላጥ አደረገ** ግ በፍጥነት አከናወነ (ስራን፥ ተግባርን፥...)።

**ተላጠ** ግ 1.ፈረጠጠ፥ ሸሸ። 2. ሄደ፥ ነጎደ።

**ላጠ**3 ስ 1. ሻረ፥ ከስልጣን አወረደ። 2. ሻረ፥ ፍርድን ለወጠ።

**ተላጠ** ግ ተሻረ፥ ተለወጠ፥ ቀረ። *ፍርዱ ተላጠ።*

*ላጠ

**ላጤ** ስ 1. ትዳር የሌለው፥ ብቸኛ ሰው። ቅ 2.እፍረተ ቢስ፥ ባለጌ።

**ላጤ መላጤ** ስ ሃብት፥ ንብረት ያላፈራና ቤተሰብ ያልመሰረተ ሰው።

**ላጥ ላጥ አለ** ግ ስራ ፈታ፥ አውደለደለ።

**ላጨ** ግ 1. ስለት ባለው ነገር (ለምሳሌ በምላጭ) ፀጉርን ከአካል ቆዳ ላይ ፍቆ፥ ፈግፍጎ አነሳ፤ መለጠ። 2. አታለለ፥ ሸነገለ።

**ልጩ** ቅ ፀጉሩን የተላጨ።

**ምላጭ** ስ 1. ፀጉርን ለመላጨት የሚያገለግል አነስተኛና ስስ የሆነ ስለታም ብረት። 2. ጠመንጃ፥ ሽጉጥ፥... ለመተኮስ የምትሳብ ቆልማማ ብረት። 3. (ዘይ.) በአነጋገሩ ቀልጣፋ የሆነ፥ ብልጣ ብልጥ።

**ምላጭ አፍ (አፈ ምላጭ)** ቅ አፈ ጮሌ፥ ብልጥ፥ ሰውን በንግግር ማታለል የሚችል።

**ተላጨ** ግ ስለት ባለው ነገር ፀጉሩ ተነሳ፥ ልጩ ሆነ።

**ላጲስ** ስ በእርሳስ ወይም በቀለም የተፃፈ ፅሁፍን ፥ንድፍን ከወረቀት ላይ ፈግፍጎ ለማጥፋት የሚረዳ ጎማነት ያለው የፅህፈት መሳሪያ።

**ላፈ** ግ 1. አቃጠለ፥ ፈጀ፥ ላጥ አደረገ። 2. መነተፈ፥ ሞጨለፈ፥ ነጠቀ። 3.በፍጥነት አከናወነ (ስራን፥ መብልን፥...)። 4.ቆረጠ። *ቢላዋ እጁን ላፈው።* 5. ቅርፊትን ከልጥ ለየ፥ ላጠ፥ ቀረፈ። 6.መታ። *በጥፊ ላፈው።*

**ላፍ ላፍ አደረገ** ግ በፍጥነት አከናወነ (ስራን፥ መብልን፥...)።

**ተላፈ** ግ ተላጠ፥ ተገሸለጠ።

**ላፌፈ** ግ ላጠ፥ ሞለፈፈ።

**ልፋፊ** ስ ተልጦ የተነሳ ቅርፊት፥ ግልፋፊ።

**ሌ** የ "ለ" ፊደል ሃምስ ዘር።

**-ሌለ** ከሌላ ምእላድ ጋር እየተጣመረ የሚነገርና "-አልኖረ፥ -አልተገኘ" የሚል ፍች የሚሰጥ መድረሻ ምእላድ። *ከሌለ፥ ስለሌለ፥ በሌለ፥ እንደሌለ፥...።*

**ሌሊት(ሌት)** ስ 1. ፀሃይ ከምትጠልቅበት ጊዜ ጀምሮ እስከምትወጣበት ድረስ ያለው ጊዜ። 2. ጠዋት፥ ማለዳ፥ ንጋት ላይ።

**ሌት ተቀን** ተው.ግ. ሌትና ቀን፥ ዘወትር፥ ያለማቋረጥ፥ ያለ እረፍት።

**የሌሊት ልብስ** ስ እንደ ብርድ ልብስ፥ አንሶላ፥ ፒጃማ፥...ያለ ሌሊት የሚለበስ ልብስ።

**የሌሊት ወፍ** ስ ሌሊት የምትበር እንደ ወፍ ክንፍ፥ እንደ አይጥ ጥርስና ጆሮ ያላት የምታጠባ ወፍ።(ስእሉን ወፍ ስር ተመ.)።

**የሌሊት ዘበኛ** ስ ሌሊት ሌሊት የሚጠብቅ ዘበኛ።

**ሌላ** ቅ 1. ከበፊቱ የተለየ። *ይህ የቅድሙ አይደለም፥ ሌላ ነው።* 2. ሁለተኛ፥ ተጨማሪ። *ይህን ሳትጨርስ ሌላ አይገኝም።* 3.ከታወቀው፥ ከተለመደው፥ ከሚገመተው ሳይሆን ከተለየ። *ሲትዮዋ ከሌላ ወለደች።*

**ሌላ ሌላ አለ** ጣእሙ፥ ቃናው ቀየረ፥ ለወጠ።

**ሌላ ነው** ግሩም፥ ድንቅ ነው። *አዲስ የተገዛው ልብስ ሌላ ነው።*

**ሌላ ጊዜ** አሁን ሳይሆን በሌላ ሰአት፥ ወቅት።

**ሌላው ቀርቶ** ቢያንስ ቢያንስ፥ በትንሹ።

**በሌላ መንገድ** በሌላ ዘዴ፤ በተጨማሪ። *ሂሳቡን በሌላ መንገድ ቢሰራውም ውጤቱ ተመሳሳይ ነው/መፅሃፍ የማንበብ ልምድ ጊዜን ሊባክን በታ ከማባከን ይቆጥባል፤ በሌላ መንገድ ደግሞ የእውቀት አድማስንም ያሰፋል።*

**በሌላ በኩል** ባንፃሩ። ደመወዝ ተጨምሯል፤ በሌላ በኩል ግን ኑሮ ተወዷል /በአንድ በኩል ይጋገራል፤ በሌላ በኩል ይበላል።

**በሌላ አባባል/አነጋገር/አገላለፅ** ይህም ማለት። *ከተለያዩ ሰዎች ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት ማድረግ ለአደጋ ያጋልጣል፤* በሌላ አባባል አንድ ለአንድ መወሰን ይበጃል ማለት ነው።

**የሌላ እንዳይመስል** ከሚገመተው ወይም

ሊሆን ከሚገባው ውጪ እንዳይመስል።

**ከ __ ሌላ** ከ __ በተጨማሪ። *ከዚህ ሌላ ምን ትፈልጋለህ።*

**ሌማት** ስ ከአክርማ ወይም ከስንደዶ፥... የሚሰራና ለእንጀራ ማስቀመጫነት የሚያገለግል መሶብ።

**ሌባ**[1] ስ 1. የሌላን ሰው ንብረት ሰርቆ የወሰደ ሰው። ቅ 2. የራሱ ያልሆነውን ነገር ሰርቆ የሚወስድ። 3. (ዘይ.) ውሸታም፥ አጭበርባሪ፥ አታላይ።

**ሌባ ሚዛን** ስ ትክክለኛ ያልሆነ ሚዛን፤ የአንድን ነገር የክብደት መጠን ያለአግባብ ከፍ ወይም ዝቅ አድርጎ እንዲያሳይ የተደረገ ሚዛን።

**ሌባ ሻይ** ስ ሌባን አድኖ ለመያዝ ይረዳል ተብሎ የሚታመንበትን መድሃኒት ከጠጣ በኋላ ወገቡን በመቀነት ተይዞ ሌባን የሚያድን የቀድሞ ጊዜ ሌባ አሳሽ።

**ሌባ ውጋት** ስ ድንገተኛ የሆነ የውጋት በሽታ፥ ህመም።

**ሌባ ዝናም** ስ ሳይታሰብ ድንገት መጥቶ ሰብል የሚያጠፋ ዝናም።

**ሌባ ጣት** ስ ከእጅ አውራ ጣት ቀጥሎ ያለው አመልካች ጣት።(ስእሉን እጅ ስር ተመ.)።

**የሌባ ተቀባይ** ስ ሌባ እየሰረቀ የሚያመጣውን የሚገዛ ወይም እየተቀበለ የሚያስቀምጥ ሰው።

**ሌባ**[2] ስ በሚሰነጠቅ ወይም በሚፈለጥ እንጨት መካከል በመሆን አንደኛውን ስንጣቂ ከሁለተኛው ጋር የሚያያይዝና እንዳይለያይም የሚያውክ የእንጨት ስንጣሪ።

**ሌባ ጎማ** ስ ከጫፉ ቆልመም ያለ፥ በተለይ የተሽከርካሪዎችን ጎማ ከቸርኬው ለመለየት የሚያገለግል ከብረት የተሰራ መሳሪያ።

**ሌቤቻይ (ሌቤቻ)** ስ በሚጫኑ የጋማ ከብቶች ጀርባ ስር የሚገባ ጨርቅ ወይም ቆዳ የተጠመጠመበት የመጫኛው ክፍል፤ ውዴላ።

**ሌተና ኮሎኔል** ስ በሻለቃና በኮሎኔል መካከል ያለ የወታደር ማእረግ።

**ሌተና ጀኔራል** ስ ከሜጀር ጄኔራል በላይ ያለ የወታደር ከፍተኛ ማእረግ።

**ሌት "ሌሊት"**ን ተመ.

**ሌቸዌ** ስ በተለይ በባሮና አኮቦ ወንዝ አካባቢ የሚገኝ፥ ረዥምና ከርዳዳ ፀጉር ያለው፥ መልኩ በጠቅላላ ጠቆር ያለ ቡናማ የሆነ ሳረ በል እንስሳ። ሴቷ ሌቸዌ ቀንድ የላትም።(ስእሉን የዱር እንስሳት ስር ተመ.)።

**ሌንቦ** ስ ለንቦጭ።

**ሌዛ ሃረግ** ስ እየተሰነጣጠቀ ለቤት መማገሪያ የሚያገለግል ቅጠለ ሰፋፊ የሆነ ሃረግ።

**ሌጣ** ቅ 1. ነጠላ፥ ብቸኛ። *እገሌ ሚስት የለውም፤ ሌጣ ነው።* 2. ምንም የሌለው፥ ምንም ያልያዘ፥ ባዶ። *ላራስ ልትጠይቅ ሌጣ እጇን መጣች*። 3. የምታጠባው፥ የምታዝለው ወይም በሆዷ የተረገዘ ልጅ የሌላት (ሴት)። 4. ያልተጫነ (ፈረስ፥ በቅሎ፥...)።

**ሌጣ ምድር** ስ አትክልት፥ እፅዋት፥... ያልበቀሉበት ባዶ ወይም ገላጣ ስፍራ።

**ሌጣ ሰማይ** ስ ደመና፥ ጭጋግ ወይም ጉም የሌለበት የጠራ ሰማይ።

**ሌጣ ሰው** ስ ቤተሰብ የሌለው ብቸኛ ሰው።

**ሌጣ ቀን** ስ በአል የሌለበት የስራ ቀን።

**ሌጣ ወረቀት** ስ ያልተፃፈበት፥ ባዶ ወረቀት።

**ሌጦ** ስ ያልተለፋ የበግ ወይም የፍየል ቆዳ።

**ል** የ "ለ" ፊደል ሳድስ ዘር።

**ል-** መ.(ከ"**ይ**" ከ "**እ**" ድምፆች በፊት ሲመጣ "ሊ-"፥ "ላ-" ይሆናል) ምኞትን፥ ምክንያትን ወይም ሌላ ድርጊትን በሚጠቁሙ ግሶች መነሻ እየገባ ግሱ እንዲያስር የሚያደርግ ምእላድ። *ልመጣ እፈልጋለሁ /ላየው ጓጉቻለሁ/ ሊሄድ ቸኩሏል።*

**-ልህ "-ለት"**ን ተመ.

**ልል "ላላ"**ስር ተመ.

**ልመደው** ስ የሁለት አሞሌ ጨው ያህል መጠን ያለው አንድ ትልቅ አሞሌ ጨው።

**ልሙጥ "*ለመጠ"** ስር ተመ.

**ልማም "ለመመ"** ስር ተመ.

**ልም "ላመ"** ስር ተመ.

**ልምሻ(ልምሾ)** ስ ሽባ የሚያደርግ በሽታ፤ ፖሊዮ።

**ልምቡጥ "ልንቡጥ"**ን ተመ.

**ልም አይን** ቅ አይኑ ደካማ የሆነ (ሰው)።

**ልም እቃ** ስ ምራን እንዲሁም የመርገጥና የማነቆ ጠፍር በጥቅሉ የሚጠሩበት ስም።

**ልምጭ**[1] ስ ቅርፊቱ ጥቁር አረንጓዴ የሆነና ለጥርስ መፋቂያነት የሚጠቀሙበት የእፅዋት አይነት።

**ልምጭ**[2] ስ **"ለመጠ[1]"** ስር ተመ.

**ልሳን** ስ 1. አንደበት፥ የመነጋገሪያ ህዋስ። 2. ቋንቋ። 3. ዛቢያው የሚገባበት የዶማ ወይም የመጥረቢያ ጉሮሮ። 4. ማንኛውም የፖለቲካ፥ የሃይማኖት፥...ድርጅት አስተያየቱን፥ ፍላጎቱን፥ እምነቱን የሚገልፅበት ጋዜጣ፥ መፅሄት። 5. የሰይፍ ስለት።

**ልሳኑ ተዘጋ** መናገር አቃተው፥ ተሳነው።

**ልሳነ ምድር** ስ ሾጠጥ ብሎ ወደ ባህር የገባ

መሬት::

**ልሳን ባህር** ስ ሾጠጥ ብሎ ወደ የብስ የገባ ባህር::

**ልሳን ብዙ** ቅ 1. ብዙ ወይም የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚጠቀም:: 2. ብዙ ወይም የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚያተራጉም ወይም በብዙ ቋንቋዎች የተዘጋጀ (ለምሳሌ ልሳነ ብዙ መዝገበ ቃላት)::

**ልሳን እሳት** ስ የእሳት ነበልባል ጫፍ::

**ልሳን ክልኤ** ቅ 1. ሁለት ቋንቋ ብቻ የሚናገር:: 2. ሁለት ቋንቋዎችን የሚያተራጉም ወይም በሁለት ቋንቋዎች የተዘጋጀ (ለምሳሌ ልሳነ ክልኤ መዝገበ ቃላት)::

**ልሳን ዋህድ** ቅ 1. አንድ ቋንቋ ብቻ የሚናገር:: 2. ባንድ ቋንቋ ብቻ የተዘጋጀ (ለምሳሌ ልሳነ ዋህድ መዝገበ ቃላት)::

**ልሻ** ስ ለስላሳ የአረህ ወይም የገደል ሳር::

**ልሻ ፀጉር** ስ ለስላሳ+ ሉጫ ፀጉር::

**-ልሽ** "-ለት"ን ተመ.

**ልቃቂት** "ለቀቀ" ስር ተመ.

**ልቅ** ዝ.ከ.

**ልቅሞሽ** "ለቀመ" ስር ተመ.

**ልቅና** "ኣለቃ" ስር "እልቅና"ን ተመ.

**ልቆ** "*ለቃ" ስር ተመ.


**ልቋሳም** "ሉቃሳም"ን ተመ.

**ልቡና** "ልብ" ስር "ልቦና" ን ተመ.

**ልባብ** ስ ከጠፍር የተሰራ፥ ፈረስና በቅሎ ራስ ላይ የሚጠለቅ የፊት ላይ ጌጥ::

**ልባንጃ** "ሉባንጃ"ን ተመ.

**ልብ** ስ 1. በሰውነት ውስጥ የደምን ዝውውር የሚያከናውን ውስጠ ክፍት የሆነ የሰውነት ክፍል:: 2. እንደ አእምሮ ሁሉ የስሜት፥ የሃሳብ+... መፍለቂያ እንደሆነ ተደርጎ የሚወሰድ አካል::. 3. የዳቦ ቡጥ ወይም የእንጨት፥ የፍሬ+...መሃለኛው ክፍል:: 4. ከኣገናዛቢ ምእላዶች ጋር እየሆነ ሃሳብ፥ ስሜት፥... የሚል ፍቺ የሚሰጥ (ለምሳሌ ልቤ ተሸበረ/ልቡ ተጨነቀ)::5. (ዘይ.) ድፍረት፥ወኔ::



ልብ

**ልቡ ሄደ** በሃሳብ ተዋጠ፤ ሃሳቡ ወደሌላ ሄደ::

**ልቡ መታ** 1. የልቡ ምት ፍጥነት ጨመረ፥ ከተገቢው መጠን ወይም ሁኔታ ውጪ ሆነ:: 2. ደነገጠ+ ፍርሃት ተሰማው::

**ልቡ ሞተ** ደከመ፥ ሰነፈ፥ ወኔ አጣ::

**ልቡ ረጋ** ከሃሳብ፥ ከጭንቀት፥... ነፃ ሆነ::

**ልቡ ራራ** ርህራሄ ተሰማው፥ አዘነ::

**ልቡ ራሰ** ያሰበው ወይም የተመኘው ሆነለት፥ ተሳካለት፤ ደስ አለው፥ ረካ::

**ልቡ ሰባ** ትእቢት ያዘው፥ አልታዘዝ አለ::

**ልቡ ሳሳ** 1. በነገር ተሰላቸ:: 2. በበሽታ፥ በመጠጥ፥... የተነሳ አቅም አነሰው::

**ልቡ ሸፈተ** ያሰበውን ነገር ለማድረግ ተነሳሳ፤ ሃሳቡ ወደ ሌላ ሄደ::

**ልቡ ሻከረ** "ሆድ" ስር "ሆዱ ሻከረ"ን ተመ.

**ልቡ ቀረ** ቅር አለው፥ ሆዱ አልቆርጥ አለ፥ ሃሳቡ ቀደም ሲል ወደነበረበት ቦታ ተመለሰ::

**ልቡ ቆመ** ያሰበውን ነገር ለማድረግ ቸኮለ፥ ጓጓ፥ ተነሳሳ::

**ልቡ ቆረጠ** 1. አንድን ነገር ለማድረግ ወሰነ:: 2- እርግፍ አድርጎ ተወ::

**ልቡ ቆሰለ** 1. በጣም ተናደደ፥ በገነ:: 2. በጭቅጭቅ፥ በነገር፥... ብዛት ደከመ ወይም ሰለቸ::

**ልቡ ባከነ** ሃሳቡ ወዲያና ወዲህ ተበታተነ፥ አንድ ነገር ላይ አልረጋ አለ::

**ልቡ ተመለሰ** ተረጋጋ::

**ልቡ ተሰበረ** በጣም አዘነ::

**ልቡ ተቃጠለ** ተናደደ::

**ልቡ ተተረተረ/ትርትር አለ** በጣም ደነገጠ::

**ልቡ ተነሳ** ተቻኮለ፥ አቆበቆበ (አንድ ነገር ለማድረግ፥...)::

**ልቡ ተንጠለጠለ** 1. ያሰበውን ለማድረግ ወይም ለማግኘት በጉጉት ጠበቀ:: 2. ቸኮለ::

**ልቡ ተከፈለ** 1. ከሁለት ሃሳቦች አንዱን ለይቶ መወሰን ወይም መምረጥ አቃተው፤ አመነታ:: 2. ለአንድ ነገር ሙሉ ትኩረት መስጠት አቃተው::

**ልቡ ተደፈነ** ትእቢተኛ፥ ጥጋበኛ፥ አልታዘዝ ባይ ሆነ::

**ልቡ ትልቅ ነው** 1. ሃሳቡ፥ ምኞቱ ትልቅ ነው:: 2. ሃሳቡ፥ምኞቱ ከቅሙ በላይ ነው::

**ልቡ ነፈረ** "ሆድ" ስር "ሆዱ ነፈረ"ን ተመ.

**ልቡ አረፈ** ተረጋጋ::

**ልቡ አበጠ** ተበተ፥ ጥጋብ ተሰማው::

**ልቡ አይገኝም/አይታወቅም** ምስጢሩ፥ ምኞቱ፥ ሃሳቡ አይታወቅም::

**ልቡ አይጠራም** "ሆድ" ስር "ሆዱ አይጠራም"ን ተመ.

**ልቡ ከዳው** ወኔ፥ ድፍረት አጣ::

**ልቡ ወለቀ** ደከመ፥ ሰለቸ::

**ልብ አውልቅ** ቅ 1. ነገር የማይደጋግም፥ ችኩ፥ ነዝናዛ፥ አሰልቺ:: 2. የተነገረውን የማይሰማ፥ ምክር የማይቀበል::

**ልቡ ደረቀ** በመፍጨፍጨፍ፥ በመለፍለፍ ደከመ::

**ልቡ ደነደነ** ኮራ፥ ታበየ::

**ልቡ ገባ** ተፅናና፥ ተረጋጋ::

**ልቡ ጠራ** "ሆድ" ስር "ሆዱ ጠራ"ን ተመ.

**ልቡ ጠፋ** ዘነጋ፥ ረሳ::

**ልቡ ፈሰሰ** 1. በጣም ደከመው፥ ዛለ:: 2. ሰነፈ::

**ልቡ ስንጥቅ አለ** ድንግጥ አለ::

**ልቡን መታው** አቅለሸለሸው፥ አጥወለወለው::

**ልቡን ምን በላው/ወሰደው** እንዴት ረሳ፥ እንዴት ዘነጋ::

**ልቡን ሰወረው** አእምሮውን ሳተ::

**ልቡን ሰጠው** "ሆድ" ስር "ሆዱን ሰጠው"ን ተመ.

**ልቡን ቆረቆረው** "ሆድ" ስር "ሆዱን ቆረቆረው"ን ተመ.

**ልቡን ነሳው** 1.አበደ፥ አእምሮውን ሳተ:: 2. በአጋጠመው ጥሩ ወይም መጥፎ ሁኔታ ተረጋግቶ ማሰብ አቃተው::

**ልቤ አልደነገጠለትም** አልሳበኝም፥ አልማረከኝም::

**ልቤን ይቆላኛል** ከምግብ አለመስማማት የተነሳ ያጥወለውለኛል፥ የህመም ስሜት ይሰማኛል::

**ልብ ለልብ** ሃሳብ ለሃሳብ:: *ልብ ለልብ ይተዋወቃሉ::*

**ልብ ሰረቀ** 1. ስሜትን ሳበ፥ ማረከ፥ አማለለ:: 2. የሌላውን ልብ አስከዳ፥ አስሸፈተ፥ የሃሳቡ ደጋፊና ተባባሪ አደረገ::

**ልብ ሰቀለ** አጓጓ (ፍፃሜውን፥ መጨረሻውን፥ ውጤቱን፥ ቁርጡን፥... ለማወቅ)::

**ልብ ሰጠ** 1. አደፋፈረ:: 2. ማንነቱን፥ ጠባዩን፥ ምስጢሩን፥... ገለጠ፥ አሳወቀ::

**ልብ በላ** አሳዘነ::

**ልብ ነሳ** 1. አንገበገበ፥ አቃጠለ፥ አሰቃየ:: 2. ጨቀጨቀ፥ ነዘነዘ::

**ልብ ነካ** 1. አሳዘነ:: 2. መሰጠ፥ ስሜትን ነካ:: 3. አመመ፥ አልስማማ አለ (ምግብ፥ መጠጥ)::

**ልብ አለ** አስተዋለ፥ አትኩሮ ተመለከተ፥ አጤነ::

**ልብ አደረገ** አስተዋለ፥ አጤነ::

**ልብ አድርግ** 1. እማኝ ወይም ምስክር ስለምትሆን ሁኔታውን ተመልከት:: 2. ተጠንቀቅ::

**ልብ አገኘ** 1. ጎበዝ፥ ደፋር ሆነ:: 2. ብርቱ፥ ታታሪ ሆነ:: 3. ማስተዋል፥ ማመዛዘን ቻለ::

**ልብ አጠፋ** 1. ስሜትን ያዘ፥ ማረከ:: 2. አስረሳ፥ አስዘነጋ:: 3. አደከመ::

**ልብ ወረደው** በጣም ደከመው::

**ልብ ይሰልባል** ያደክማል:: *ፀሃዩ ልብ ይሰልባል::*

**ልብ ይጠይቃል** ወኔ፥ ድፍረት ይጠይቃል::

**ልብ ገዛ** 1. ሰከነ፥ ራሱን ተቆጣጠረ:: 2. ጠንቃቃ ሆነ::

**በልቡ ተኝቷል** በደረቱ ተኝቷል::

**በልቡ አሰበ** "ሆድ" ስር "በሆዱ አሰበ"ን ተመ.

**በልቡ ያዘ** በአእምሮው መዘገበ፥ አስተዋለ::

**በልቡ አደር /አዳሪ** እንዳሻው የሚሆን፥ ተቆጣጣሪ የሌለው::

**እንደልብ ሆነ /ተገኘ** በብዛት ተገኘ::

**ከልቡ ሆነ** ተረጋጋ::

**ከልቡ መከረ** አንድን ነገር ለማድረግ፥ ለመወሰን፥ ...አወጣ አወረደ ወይም አሰላሰለ::

**ከልቡ አልጣፈውም** 1. ከቁም ነገር አልቆጠረውም፥ ናቀው፤ ነገሬም አላለው:: 2. ዘነጋው::

**ከልብ** 1. ከምር፥ የእውነት:: *ከልቤ ነው የምነግርህ*:: 2. በሙሉ ስሜት ወይም ፍላጎት:: *ከልብ የተሰራ ስራ ያስታውቃል::*

**ከልብ የመነጨ** ከእውነተኛ ስሜት ወይም ፍላጎት የመጣ::

**የልቡ ሆነለት** ያሰበው፥ የተመኘው ተሳካለት ወይም ተፈፀመለት::

**የልቡ ደረሰ** ያሰበው ወይም የፈለገው ተፈፀመ፥ ተሳካ::

**የልቡን ሰራ** የፈለገውን ወይም ያሰበውን አደረገ::

**የልቡን ተናገረ** 1. የፈለገውን ተናገረ። 2. በልቡ አምቆ ወይም ደብቆ የያዘውን አውጥቶ ተናገረ።

**የልብ ልብ ሰጠው** አደፋፈረው።

**ልበ ሙሉ** ቅ 1. ደፋር፥ ጎበዝ። 2. በራሱ የሚተማመን።

**በልበ ሙሉነት** በእርግጠኛነት።

**ልበ ሙት** ቅ ሰነፍ፥ ደካማ፥ ወኔ ቢስ።

**ልበ ሰፊ** "ሆድ" ስር "ሆደ ሰፊ"ን ተመ.

**ልበ ቀላ** ቅ 1. ከተቀጠቀጠ በሂላ የሚሰር በሬ፥ በግ፥ ፍየል። 2. ካረጀ ወይም ከመኮለስ በሂላ የፍትወት ፍላጎት የሚያድርበት (ሰው)።

**ልበ ቅን** ቅ ደግ፥ ትሁት፥ የዋህ።

**ልበ ቆራጥ** ቅ የማያወላውል፥ የማያመነታ።

**ልበ ቢስ** ቅ ዝንጉ፥ ቀልበ ቢስ።

**ልበ ብሩህ/ብር** ቅ ብልህ፥ አዋቂ፥ ሁሉ ነገር ቶሎ የሚገባው።

**ልበ ተራራ** ቅ ከአቅሙ በላይ የሚመኝ ወይም የሚያስብ።

**ልበ እውር** ቅ ብልህነት የሌለው፤ ደደብ።

**ልበ ክፍት** ቅ ብሩህ አእምሮ ያለው።

**ልበ ደንዳና** ቅ ብዙ የማይጨነቅ፥ ግድ የሌለው፥ ሃሳብ የለሽ።

**ልበ ድንጉጥ** ቅ ሩህሩህ፥ የሰው ችግር ቶሎ የሚሰማው።

**ልበ ድንጋይ** ቅ ጨካኝ፥ የሰው ችግር የማይሰማው።

**ልበ ድፍን** ቅ 1. ትእቢተኛ፥ ጥጋበኛ፥ አልታዘዝ ባይ። 2. ፍርሃት የማይሰማው። 3. ደደብ፥ ትምህርት ወይም እውቀት የማይገባው።

**ልበ ገር** ቅ "ሆድ" ስር "ሆደ ገር" ን ተመ.

**ልብ ራስ** ስ 1. መሃል ራስ፥ አናት። 2. ደረት አካባቢ ያለው የልብ ትርታ የሚሰማበት ቦታ።

**ልብ አልባ** ቅ ዝንጉ፥ የሚረሳ።

**ልብ አውልቅ/አድርቅ/አቅልጥ** ቅ 1. ነገር የሚደጋግም፥ ችኮ፥ ነዝናዛ። 2. የተነገረውን የማይሰማ፥ ምክር የማይቀበል።

**ልብ ወለድ (ልቦለድ)** ስ 1. እውነት ያልሆነ የፈጠራ ወሬ፥ በእውነት ያልተፈፀመ። 2. እንደ ረዥም ልቦለድ፥ አጭር ልቦለድ ያለ የፈጠራ ስራ ውጤት የሆነ ስነ ፅሁፍ።

**ልብ የለሽ** ቅ ዝንጉ፥ ልበ ቢስ።

**ልብ ድካም** ስ ልብ ተግባሩን በሚገባ ካለመፈፀሙ የተነሳ የሚመጣ የልብ ህመም።

**የልብ ቁርጠት** ስ ሆድ ቁርጠት።

**የልብ ትርታ** ስ 1. ልብ ደምን በሰውነት ውስጥ ለማሰራጨት በደቂቃ 70 ያህል ጊዜ የሚያደርገው ምት ወይም ንዝረት። 2. ፍላጎት። *የአንድ አገር መሪ የህዝቡን የልብ ትርታ አዳምጦ ፍላጎቱን ማሟላት ይኖርበታል።*

**የልብ ወዳጅ** ስ ምስጢር የሚያካፍሉት፥ በጣም የሚያቀርቡትና የሚወዱት ሰው።

**የልብ ውጋት** ቅ አሰልቺ፥ ነዝናዛ፥ ጨቅጫቃ።

**ልባም** ቅ 1. አስተዋይ፥ የማይዘነጋ። 2. ባለሙያ።

**ልባዊ** ቅ ከሙሉ ፍላጎት ወይም ስሜት የመነጨ።

**ልቦና (ልቡና)** ስ ህሊና ወይም አእምሮ።

**ልብላቢ** ስ ከተፈጨ እህል ውስጥ በወንፊት ተለይቶ የሚወጣ የአሰርና የዱቄት ድብልቅ የሆነ እንቅጥቃጭ፥ ጥርግራጊ።

**ልብም** ስ የመገበሪያ ዱቄት የሚቀመጥበት የሸክላ እቃ።

**ልብ አልባ[1] (ልባልባ፥ ልባልማ)** ስ በሃርና በወርቅ የተጠለፈና ጌጥ ያለው የቀድሞ ጊዜ የሴት ሱሪ።

**ልብ አልባ[2]** ስ "ልብ" ስር ተመ.

**ልቦለድ** "ልብ" ስር "ልብ ወለድ"ን ተመ.

**ልቦና** "ልብ" ስር ተመ.

**ልቴም** ስ የፈንጣጣ ጠባሳ።

**ልት** ስ እንጨቱ ጥንካሬ የሌለው፥ የደረቀ ቁስል ያለሰልሳል የሚባልና ሰዎች ለሆድ መድሃኒት ነው እያሉ እየቀቀሉ የሚበሉት ማላጋነት ያለው የእፅዋት አይነት።

**-ልን** "-ለት"ን ተመ.

**ልንቡጥ (ልምቡጥ)** ስ ያልተገረዘ የወንድ ብልት፤ ወሸላ።

**-ልኝ** "-ለት" ን ተመ.

**ልኡል (ብ.ቁ.ልኡላን)** ቅ 1. ከፍ ያለ፥ ከሁሉ በላይ የሆነ። *ልኡል እግዚአብሄር።* 2. የነገስታት ልጆችና ተወላጆች ለሆኑ ታላላቅ መሳፍንት የሚሰጥ የማእረግ ስም።

**ልኡካን (ነ.ቁ. ልኡክ)** ስ 1. አንድን ጉዳይ ለማስፈፀም በመንግስት ወይም በድርጅት ተወክለው የተላኩ መልእክተኞች። 2. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) የእለቱ ተረኛ ቀዳሾች።

**ልእልት (ብ.ቁ.ልእልታት)** ቅ የልኡላን ሚስቶች ወይም የነገስታት ሴት ልጆች የሚጠሩበት የማእረግ ስም።

**ልከኛ** "ለካ[1]" ስር ተመ.

**ልክ** ዝ.ከ.

**ልክፍት** "ለከፈ" ስር ተመ.

**ልኳንዳ** "ሉካንዳ"ን ተመ.

**ልደታ** ስ የየወሩ የመጀመሪያ ቀን፣ መባቻ:: (ልደታ የሚለውን ስያሜ ያገኘው ማርያም የተወለደችበትን ግንቦት 1 ቀንን መነሻ በማድረግ ነው::)

**ልደት** ስ 1. ታህሳስ 29 (በዘመነ ዮሃንስ ታህሳስ 28) ቀን የሚከበር ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት ቀን፣ ገና:: 2. ማንኛውም ሰው የተወለደበት ቀን:: *ዛሬ ልደቴ ነው::*

**ልጃልቅስ (ልጅ አልቅስ)** ስ ተዘርቶ ቶሎ ለችግር የሚደርስ የገብስ አይነት::

**ልጃገረድ** ስ ለአቅመ ሄዋን የደረሰች፣ በድንግልናዋ ያለችና ያላገባች ሴት::

**ልጅ** ስ 1. ህፃን፣ ጨቅላ፣ በቅርብ ጊዜ የተወለደ:: 2. በእድሜ ያልገፋ፣ ወጣት:: 3. ያልሸመገለ:: *ሊያቴ ገና ልጅ ነው::* 4. ተወላጅ:: *እሱ የአዲስ አበባ ልጅ ነው::* 5. የተወለደ፣ ከአብራክ የወጣ:: *ስንት ልጆች አሉህ?* 6. የመሳፍንትና የመኳንንት ወንዶች ልጆች የሚጠሩበት የማእረግ ስም :: *ልጅ እያሱ::*

**ልጅ በልጅ ሆነ** ብዙ ልጆች ወለደ::

**ልጅ ነው** ያልበሰለ፣ ለጋ ነው::

**ልጅ እንደ እናቷ ሆነች** ክብረ ንፅህናዋ ተገሰሰ::

**ልጅነቱን ያልጨረሰ** እድሜው ትልቅ ሆኖ ባህርዩ ወይም ግብሩ የልጅ አይነት የሆነ::

**ልጅ እግር** ስ ወጣት::

**የልጅ ልጅ አየ** አያት ሆነ::

**ልጅ አልቅስ** "ልጃልቅስ"ን ተመ.

**ልጉም** "ለጎመ" ስር ተመ.

**ልጋግ** ስ ለሃጭ::

**ልጋጋም** ቅ (ስድብ) ለሃጫም::

**ልጣብ** "ለጠበ" ስር "ለጠብ"ን ተመ.

**ልጣጭ** "ላጠ" ስር ተመ.

**ልጥ** ዝ.ከ.

**ልጦ** ዝ.ከ.

**ልጨኛ** ቅ ትን፣ ለሰው በጎ ነገር የሚሰራ፣ ውለታ የሚውል፣ ቀምነገረኛ::

**ልጭ** "ላጨ" ስር ተመ.

**ልፊ (ልፌ)** ስ ጥፍረ መጥምጥ::

**ልፉጭ** ስ ስብነት የሌለው፣ የሚያሙለጨልጭና ሊበላ የማይችል ስጋ::

**ልፉጫም** ቅ (ዘይ.፣ስድብ) የማይረባ፣ ሃሞተ ቢስ::

**ልፋፈ ፅድቅ** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ስርየተ ሃጢአትና ፅድቅ ያስገኛል በሚል እምነት አንዳንድ ሰዎች በቁመታቸው ልክ በብራና አስፅፈው የሚይዙትና የሚፀልዩበት ከሞቱም በሂላ አብሯቸው እንዲቀበር የሚደረግ ፅሁፍ::

**ልፋፌ** "ላፈፈ" ስር ተመ.

**ልፌ** "ልፊ"ን ተመ.

**ሉ** የ"ለ" ፊደል ሳብእ ዘር::

**ሉሌ** ስ አሽከር፣ አገልጋይ፣ ምንደኛ::

**ሉል** ስ እንጨትነቱ ክብደት ያለውና በወይና ደጋ የሚበቅል ትልቅ ዛፍ::

**ሉመለመ** ግ ትምክ ትምክ አለ፣ ላላ፣ ሉከሉከ::

**ሎሚ** ስ 1. እንደ ብርቱካን ያለ ሆኖ መጠኑ አነስተኛ የሆነና ኮምጣጣነት ያለው የሚመጠጥ ወይም የሚበላ የፍራፍሬ አይነት:: ሎሚውን የሚያፈራው ተክልም ሎሚ ይባላል:: 2. እንደ ሎሚ ክብ የሆነ ተንቀሳቃሽ የጉልበት አጥንት፣ ሎሚታ::

**የሎሚ እሸት** ስ መጠኑና አይነቱ እንደጠሰኝ ሆኖ ሽታውና መአዛው የሚጣፍጥ የእፅዋት አይነት::

**ሎሚታ** ስ 1. የ"ሎሚ"ን 2ኛ ፍቺ ተመ. 2- በጎራዴ ሰገባ ጫፍ ላይ የሚሰካና ከወርቅ፣ ከብር፣ ... የሚሰራ የሎሚ ቅርፅ ያለው ጌጥ::

**ሎምቢ** ስ የአሳ አይነት::

**ሎተሪ** ስ 1. የሎተሪ ትኬት:: 2. ተከታታይ ቁጥሮች የተሰጧቸው ብዙ ትኬቶች ለሰዎች ከተሸጡ በሂላ፣ እጣ በመጣል አሸናፊ ለሆነው ቁጥር የተወሰነለትን ገንዘብ፣ እቃ፣... በመስጠት የሚካሄድ ተግባር::

**ሎተሪ ቆረጠ** የሎተሪ ትኬት ገዛ::

**ሎተሪ ወጣለት** 1. የሎተሪ እጣ ደረሰው:: 2. ያላሰበውን ጥሩ ነገር አገኘ::

**ሎተሪ አዟሪ** ስ የሎተሪ ትኬቶችን እያዞረ የሚሸጥ (ሰው)::

**የሎተሪ ትኬት** ስ የራሱ የሆነ መለያ ቁጥር ያለውና እጣ (ገንዘብ ወይም ሌላ ነገር) ሊያስገኝ የሚችል በገንዘብ የሚገዛ ትኬት::

**ሎቲ** ስ 1. በቀድሞ ጊዜ አንበሳ ወይም ዝሆን ወይም አውራሪስ፣ ... የገደለ ጆሮው ላይ የሚያንጠለጥለው ከወርቅ ወይም ከብር ወይም ከነሃስ፣... የሚሰራ ቀለበት:: 2. እንደ ቀለበት ሆኖ ከወርቅ ወይም ከብር፣...የሚሰራ የሴቶች የጆሮ ጌጥ::

**ሉከሉከ (ለከለከ)** ግ ከመብሰል፣ ከመበስበስ፣...የተነሳ ጥንካሬውን አጣ፣ ትምክ ትምክ አለ፣ ላላ (ፍራፍሬ፣ እባጭ፣...)::

**ሎጋ** ስ 1. ቅርፁ ሰፋ ያለ፣ ረዥምና

ጠንካራ የሆነ ጦር፡፡ ቅ 2. (ዘይ.) ቁመናው የሚያምር ረዥም፥ መለሉ (ወጣት)፡፡

**ሉጋው ሽቦ** 1. ባህላዊ የዘፈን አይነት፤ ሆታ፡፡ 2. በሉጋው ሽቦ የሆታ ግጥም ውስጥ በዜማ እየተመላለሰ የሚባል የግጥሙ አዝማች፡፡

**ሉጤ** ቅ ሳይጠሩት ወይም ሳይፈልጉት ከተፍ የሚል፤ ቀላዋጭ፡፡

**ሉጥ ሉጥ አለ** ግ መንደር ለመንደር ዞረ፥ ተንከወከወ፡፡

**ሉጥኋጣ** ቅ ሳይጠሩት ወይም ሳይፈልጉት ከተፍ የሚል፤ ቀላዋጭ፡፡

**ሉፊሳ** ስ 1.ፀጉሩ ረዥም የሆነ የበግ ወይም የፍየል ቆዳ፡፡ 2. ፀጉሩ ረዥም ከሆነ የበግ ወይም የፍየል ቆዳ የሚሰራ ደበሎ፤ ግላስ፤ ጎፈር፡፡

- **ሉፍ**

**ሉፌ** ቅ መንደር ለመንደር የሚዞር፤ አውደልዳይ፡፡

**ሉፍ ሉፍ አለ** ግ መንደር ለመንደር ዞረ፤ አውደለደለ፡፡

**ኋ** የ"ለ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር፡፡